# ሒሳብ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል


**አዘጋጆች:-**

የሱፍ የሻው

**አርታኢአን:-**

ገብረየስ ኃይለጊዮርጊስ
ባይሳ ሰርቤሳ

**ገምጋሚዎች:-**

ዳኛው አስማረ

ክፍሌ ይልማ



ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

# ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው:: የኘሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው::

የኢትዮጵያ ፌዲራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትቭ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው::

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የተማሪ መጽሀፍና የመምህር መምሪያ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፍቸውን ሰጥተዋል:: በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::

© በኢትዮጵያ ፌዲራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

1ኛ እትም፣ 2004 ዓ.ም

ISBN 978-99944-2-225-8

**የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 5613**
**ዱባይ፣**
**የተባበሩት የአረብ ኤሜሬት**

**ከኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 100767**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል::

ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል::

የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዲራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል::

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል:: ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን::

# ማውጫ

ገፅ

## ምዕራፍ 1:- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችና ቅደም ተከተላቸው

1.1 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ክለሳ ........ 1
1.2 እስከ 1000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች የማስላት ክለሳ ........ 6
1.3 የ100 እና የ1000 ብዜቶች እስከ 10,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ........ 14
1.4 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ........ 16
1.5 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ........ 19

የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ ........ 24
የማጠቃለያ መልመጃ ........ 25

## ምዕራፍ 2:- ልኬት

2.1 ርዝመትን በሚሊ ሜትር፣ በሳንቲ ሜትር፤ በሜትር እና በኪሎ ሜትር መለካት ........ 26
2.2 ይዘትን በሚሊ ሊትር /ሚ.ሊ/ እና በሊትር /ሊ/ መለካት ........ 32
2.3 ክብደትን በግራም (ግ)፣ በኪሎ ግራም (ኪ.ግ) እና በኩንታል መለካት ........ 35

የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ........ 37
የማጠቃለያ መልመጃ ........ 38

## ምዕራፍ 3:- ክፍልፋዮች

3.1 የሙሉ ነገር 3 ክፍልፋዮች ክለሳ ........ 40
3.2 ከ$\frac{1}{2}$ እስከ $\frac{1}{10}$ ያሉ አሀዳዊ ክፍልፋዮች ........ 41
3.3 የሙሉ ቁጥሮች ግማሽ እና ሩብ ........ 44
3.4 ቀላል ክፍልፋዮችን ማወዳደር ........ 46

የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ ........ 48
የማጠቃለያ መልመጃ ........ 48

## ምዕራፍ 4:- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ

4.1 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር ........ 51
4.2 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ ........ 58
4.3 መደመርና መቀነስ የያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች ........ 65

የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ........ 68
የማጠቃለያ መልመጃ ........ 68

## ምዕራፍ 5:- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛትና ማካፈል

5.1 የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት ........ 70
5.2 የ1000 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት ........ 72

5.3 የማባዛት ውጤታቸው ከ10,000 ያልበለጡ የሙሉ ቁጥሮችና የባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች ብዜት ..... 73
5.4 እስከ 10,000 ያሉ የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮችና በ10 ማካፈል ..... 80
5.5 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች እና በ10 በቀሪና ያለቀሪ ማካፈል ..... 83

የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ ..... 87
የማጠቃለያ መልመጃ ..... 88

ምዕራፍ 6:- መስመሮችና ቀላል ምስሎች

6.1 ተቋራጭ፣ ትይዩና ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮች ..... 90
6.2 ተቋራጭ፣ ትይዩና ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮችን መሳል ..... 92
6.3 ሬክታንግል፣ ካሬ፣ ፓራሌሎግራምና ትራፒዚየም ..... 95
6.4 ክብ ..... 98

የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ ..... 100
የማጠቃለያ መልመጃ ..... 101

ምዕራፍ 7:- ገንዘብ

7.1 የገንዘብ ኖቶችን መዘርዘር (መቀየር) ..... 102
7.2 የኢትዮጵያን የገንዘብ ምንዛሪ የያዙ የቃላት ኘሮብሌሞች ..... 105

የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ..... 106
የማጠቃለያ መልመጃ ..... 107

ምዕራፍ 8:- ጊዜ

8.1 የሰዓት አነባበብ ..... 108
8.2 ሠዓትና ደቂቃ ..... 110
8.3 ቀን፣ ሳምንት፣ ወርና አመት ..... 112
8.4 ቀላል የቀን መቁጠሪያ ..... 114

የምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያ ..... 115
የማጠቃለያ መልመጃ ..... 115

ምዕራፍ 9:- መረጃ አያያዝ

9.1 ቀላል የምስል ግራፎች ..... 117
9.2 ግራፎችን መተርጐም ..... 119

የምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ ..... 121
የማጠቃለያ መልመጃ ..... 121

# ምዕራፍ አንድ

# እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችና ቅደም ተከተላቸው

**የመማር ማስተማር ውጤቶች፡-**

- እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መፃፍ፣ ማንበብ፣ ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፡፡
- እስከ 1000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች አራቱን መሠረታዊ የሂሳብ ስሌቶች ተጠቅመው ማስላት፡፡
- እስከ 10,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች የ100 ና የ1000 ብዜቶችን መፃፍና ማንበብ፡፡
- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መፃፍና ማንበብ፡፡
- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፡፡

## 1.1 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ክለሳ

በሁለተኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርታችሁ እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ተምራችኋል፡፡ የተማራችሁትን ለማስታወስ ይረዳ ዘንድ ከዚህ በታች የቀረበውን ሻሽ ቦርድ ተመልከቱና በተግባር 1.1 የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡



## ተግባር 1.1

በቦርዱ ላይ ሶስት የተለያዩ መደቦች አሉ። በመጀመሪያው መደብ አንድ ሆሄ፣ በሁለተኛው መደብ ባለ ሁለት ሆሄና በሦስተኛው መደብ ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በፍላሽ ካርድ ተፅፈው ተቀምጠዋል። በዚህ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. ስንት ባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች አሉ?
2. ትንሹ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማን ነው?
3. ትልቁ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማን ነው?
4. ትንሹ ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማን ነው?
5. ትልቁ ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማን ነው?

## የቡድን ስራ

ጥንድ ጥንድ በመሆን እስከ 1000 ያሉ አምስት ሙሉ ቁጥሮች ሰብስቡና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተጠያየቁ።

**ማስታወሻ**

- **ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች የቁጥር ምልክቶችን አንድ ጊዜ በመጻፍ የሚገለፁ ናቸው። ለምሳሌ *0፣ 1፣ 2፣ 7፣ 9***
- **ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች ሁለት የቁጥር ምልክቶችን (አንድን ምልክት ደግሞ በመፃፍም ሊሆን ይችላል) በአንድ ጊዜ በመፃፍ የሚገለፁ ናቸው። ለምሳሌ፡- *11፣ 25፣ 43፣ 99***
- **ባለሦስት ሆሄ ቁጥሮች ሦስት የቁጥር ምልክቶችን (ደጋግሞ በመፃፍ ሊሆን ይችላል) በአንድ ጊዜ በመፃፍ የሚገለፁ ናቸው። ለምሳሌ፡- *123፣ 555፣ 633፣ 999***

## መልመጃ ሀ

1. ከዚህ በታች በፊደል የተፃፉትን ቁጥሮች በአሀዝ ፃፏቸው።

   ሀ. አራት መቶ አምስት
   ሐ. ሰባት መቶ ሰባት
   ለ. አምስት መቶ አርባ አምስት
   መ. ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በፊደል ፃፏቸው።

   ሀ. 333 ለ. 585 ሐ. 606 መ. 998

### ሀ. እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

ስለማወዳደሪያ ምልክቶች ማለትም ስለ >፣ = እና < አጠቃቀም በ2ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ተምራችኋል። በዚህ ክፍል ደግሞ እነዚህን ምልክቶች በመጠቀም እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር ትማራላችሁ።

## ተግባር 1.2

ከዚህ በታች የቀረቡትን ሦስት ጥያቄዎች በደብተራችሁ ገልብጡና በክፍት ቦታው ላይ ትክክለኛውን የማወዳደሪያ ምልክት >፣ = ወይም < በማስቀመጥ መልሱ።

ሀ. 6 ________ 2



ለ. 2 ________ 2



ሐ. 3 ________ 4

### ምሳሌ 1.1

543 > 457 ምክንያቱም 5 > 4 (ሁለቱን ሙሉ ቁጥሮች ከግራ በመጀመር ስናወዳድር)

898 < 982 ምክንያቱም 8 < 9 (ሁለቱን ሙሉ ቁጥሮች ከግራ በመጀመር ስናወዳድር)

**ማስታወሻ**

- ሁለት ሙሉ ቁጥሮች አንድ አይነት የሆሄያት ብዛት ካላቸው የሁለቱን ቁጥሮች ሆሄያት ከግራ በመጀመር በየቤታቸው ማወዳደር። ከሁለቱ ቁጥሮች የሚበልጥ ሆሄ ያለው ይበልጣል።
- ሁለት ሙሉ ቁጥሮች የተለያዩ የሆሄያት ብዛት ካላቸው ብዙ ሆሄ ያለው ሙሉ ቁጥር ይበልጣል።

## መልመጃ ለ

1. በክፍት ቦታዎች ላይ የ>፣ = ወይም < ምልክትን በመጠቀም ቁጥሮቹን አወዳድሩ።

   ሀ. 321 ____ 321 ለ. 747 ____ 685 ሐ. 809 ____ 890

2. ከሚከተሉት ቁጥሮች መካከል ትልቁ ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር የትኛው ነው?
   ሀ. 747 ለ. 809 ሐ. 690

## ለ. እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

በሁለተኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ተምራችኋል፡፡ የተማራችሁትን ለማጠናከር እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ በዚህ ክፍልም ትማራላችሁ፡፡

### ምሳሌ 1.2

የሚከተሉት አራት ተማሪዎች በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ሀና የ3ኛ ክፍል፣ አጥናፉ የ4ኛ ክፍል፣ ሀያት የ 5ኛ ክፍል እና ሽኩር የ 6ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ አራቱ ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸው ከግራ ወደ ቀኝ በቅደም ተከተል መቆማቸውን አስተውሉ፡፡



ተማሪ ሀና 3ኛ ክፍል | ተማሪ አጥናፉ 4ኛ ክፍል | ተማሪ ሀያት 5ኛ ክፍል | ተማሪ ሽኩር 6ኛ ክፍል

### ተግባር 1.3

አስማረችና አናጋው የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ አስማረች በአራት ትምህርቶች በአንደኛ ሴሚስተር ከመቶ ያገኘችው ውጤት፡- አማርኛ 85፣ እንግሊዝኛ 80፣ ሂሳብ 82 እና ሳይንስ 90 ነበር፡፡ አናጋው ደግሞ በአራቱ ትምህርቶች ያገኘው ውጤት፡- አማርኛ 80፣ እንግሊዝኛ 89፣ ሂሳብ 83 እና ሳይንስ 84 ነበር፡፡ የፈተና ውጤቶቹን ተጠቅማችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. የአስማረችን ውጤት ከዝቅተኛው በመጀመር በቅደም ተከተል በደብተራችሁ ገልብጡና ፃፉ፡፡
_______________፣ _________________፣ _________________ እና ______________፡፡

ለ. የአናጋውን ውጤት ከከፍተኛው በመጀመር በቅደም ተከተል በደብተራችሁ ገልብጡና ፃፉ፡፡
_______________፣ _________________፣ _________________ እና ______________፡፡

### ምሳሌ 1.3

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቁጥሮች
321፣ 78፣ 744፣ 59፣ 863፣ 908
ሀ. ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡
ለ. ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡

**መፍትሔ:-**

ሀ. ከትንሹ ወደ ትልቁ ሲፃፍ:- 59፣ 78፣ 321፣ 744፣ 863፣ 908 ይሆናል።

ለ. ከትልቁ ወደ ትንሹ ሲፃፍ:- 908፣ 863፣ 744፣ 321፣ 78፣ 59 ይሆናል።

### ቀዳማይና ተከታይ ሙሉ ቁጥሮች

**ምሳሌ 1.4** አበበ የ3ኛ ክፍል ተማሪ ነው።

2ኛ ክፍል　　3ኛ ክፍል　　4ኛ ክፍል

ከ3ኛ ክፍል ቀድሞ የሚገኘው ክፍል 2ኛ ክፍል ሲሆን ከ3ኛ ክፍል ቀጥሎ የሚገኘው ክፍል ደግሞ 4ኛ ክፍል ነው።

## የቡድን ስራ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩባቸው እና በተሰጠው ክፍት ቦታ ውስጥ ቀዳማይ ወይንም ተከታይ በማለት መልሱ።**

1. "ሀ" ከዜሮ የሚበልጥ ሙሉ ቁጥር ቢሆን "ሀ-1" የ "ሀ" ________ ሙሉ ቁጥር ይሆናል።
2. "ለ" ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ቢሆን "ለ+1" የ "ለ" ________ ሙሉ ቁጥር ይሆናል።

**ምሳሌ 1.5**

ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ሙሉ ቁጥሮች ቀዳማይና ተከታይ ሙሉ ቁጥሮችን ፃፉ። 10፣ 304፣ 500፣ 708፣ 998

**መፍትሔ:-** የሙሉ ቁጥሮቹን ቀዳማይና ተከታይ ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ ያሳያል።

| የቁጥሩ ቀዳማይ | የተሰጠ ሙሉ ቁጥር | የቁጥሩ ተከታይ |
|---|---|---|
| 9 | 10 | 11 |
| 303 | 304 | 305 |
| 499 | 500 | 501 |
| 707 | 708 | 709 |
| 997 | 998 | 999 |

## መልመጃ ሐ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ፃፉ።
   347፣ 83፣ 452፣ 674፣ 596፣ 877
2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ፃፉ።
   745፣ 623፣ 88፣ 33፣ 856፣ 944

3. በ745 እና በ754 መካከል ስንት ሙሉ ቁጥሮች አሉ? ቁጥሮቹንም በቅደም ተከተል ፃፏቸው፡፡
4. ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ሙሉ ቁጥሮች ለእያንዳንዳቸው ቀዳማይና ተከታይ ሙሉ ቁጥሮችን ፃፉ፡፡

| ሀ. 310 | ለ. 509 | ሐ. 777 | መ. 911 |
|---|---|---|---|
| ቀዳማይ______ | ቀዳማይ______ | ቀዳማይ____ | ቀዳማይ______ |
| ተከታይ______ | ተከታይ______ | ተከታይ____ | ተከታይ______ |

## 1.2 እስከ 1000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች የማስላት ክለሳ

### ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር ያለአለኝታና በአለኝታ መደመር በሁለተኛ ክፍል የሂሣብ ትምህርታችሁ ተምራችኋል፡፡ በሶስተኛ ክፍል የሂሣብ ትምህርትም ይህንኑ አጠናክራችሁ ትማራላችሁ፡፡

**ምሳሌ 1.6**

የሚከተለውን የመኪና ስሌት ምስል ተጠቅማችሁ ድምራቸውን በምሳሌው መሰረት አስሉ፡፡




**መፍትሔ:-** የመኪና ስሌት በግራ በኩል የሚገቡትን ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ከ 26 ጋር በመደመር መልሱን በቀኝ በኩል ይፅፋል፡፡ ስለዚህ

30 + 26 = 56፣ 40 + 26 = 66 እና 70 + 26 = 96

**ተግባር 1.4**



1. በአንድ ቅርጫት ውስጥ 37 እንቁላሎች በሌላ ቅርጫት ውስጥ ደግሞ 22 እንቁላሎች አሉ፡፡ በሁለቱ ቅርጫት ውስጥ ያሉ እንቁላሎች በአንድ ላይ ስንት ይሆናሉ?
2. ጀማል 38 የቡና ዛፎች አሉት፡፡ ከድጃ ደግሞ 12 የቡና ዛፎች አሏት፡፡ ጀማል እና ከድጃ በጋራ ስንት የቡና ዛፎች አሏቸው?

**ማስታወሻ:-**

1. ሁለት ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ያለአለኝታ ስንደምር መጀመሪያ በአንድ ቤት ያሉትን መደመር፡፡ ቀጥሎ በአስር ቤት ያሉትን ደምረን ውጤቱን ማስቀመጥ፡፡
2. ሁለት ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በአለኝታ ስንደምር መጀመሪያ በአንድ ቤት ያሉትን መደመር፡፡ ውጤቱ 10 እና በላይ ከሆነ በአንድ ቤት ያለውን ፅፈን 1 አለኝ በማለት እንፅፋለን፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በአስር ቤት ያሉትን ሙሉ ቁጥሮችና በአለኝታ የወሰድነውን ደምረን ውጤቱን ማስቀመጥ፡፡

## ምሳሌ 1.7

የሚከተሉትን ቁጥሮች ደምሩ፡፡

ሀ. 72 + 26 ለ. 40 + 50 ሐ. 53 + 39

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 72 + 26 = 98 ወይም $\begin{array}{r} 72 \\ +26 \\ \hline 98 \end{array}$ ለ. 40 + 50 = 90 ወይም $\begin{array}{r} 40 \\ +50 \\ \hline 90 \end{array}$

ሐ. 53 + 39 = 92 ወይም $\begin{array}{r} 53 \\ +39 \\ \hline 92 \end{array}$ 1 አለኝ

## መልመጃ መ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ደምሩ፡፡
   ሀ. 20 + 60 ሐ. 43 + 36 ሠ. 52 + 28
   ለ. 35 + 50 መ. 71 + 25 ረ. 24 + 49
2. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ 27 ሴት እና 25 ወንድ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች አሉ፡፡ በአጠቃላይ ስንት የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች አሉ?
3. አበጋዝ 38 ዘመናዊና 26 ባህላዊ የንብ ቀፎዎች አሉት፡፡ አበጋዝ በጠቅላላው ስንት የንብ ቀፎዎች አሉት?
4. አሰገደች በ50 ብር ዘይት በ40 ብር ደግሞ ስኳር ገዛች፡፡ አሰገደች ዘይትና ስኳር ለመግዛት በጠቅላላ ስንት ብር አወጣች?

ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርት ተምራችኋል፡፡ የተማራችሁትን ለማጠናከር በዚህ የክፍል ደረጃ ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች ላይ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን መቀነስ ትማራላችሁ፡፡

**ምሳሌ 1.8** የሚከተለውን የስሌት መኪና ምስል አቀናነስ ተጠቀማችሁ አስሉ፡፡




**መፍትሔ፡-**

የስሌት መኪና በግራ በኩል ከሚገኙት ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ 25ን በመቀነስ መልሱን በቀኝ በኩል ይፅፋል፡፡ ስለዚህ

45 – 25 = 20፣ 66 – 25 = 41 እና 80 – 25 = 55

## ከባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

### ተግባር 1.5

1. ዘውዱ 37 የቡና ችግኞች ነበረው:: 15ቱን ችግኞች ቢሸጥ ስንት ችግኞች ይቀረዋል?



ችግኝ

2. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት 86 ነው:: ከዚህ ውስጥ የሴት ተማሪዎች ብዛት 44 ቢሆን የወንድ ተማሪዎች ብዛት ስንት ይሆናል?
3. አንድ የህብረት ስራ ማህበር 93 በሬዎችን አድልቧል:: ማህበሩ 75 በሬዎችን ቢሸጥ ስንት ያልተሸጡ በሬዎች ይቀሩታል?

**ምሳሌ 1.9:-** በቁጥር ቤት የተዘጋጀ አባከስን በመጠቀም ከ35 ላይ 23ን መቀነስ::

**መፍትሔ:-**

35 በቁጥር ቤት አባከስ ሲገለፅ




መጀመሪያ በአንድ ቤት ካሉት አምስት ቆርኪዎች ሦስቱን ማውጣት




ቀጥሎ በ 10 ቤት ካሉት 3 ቆርኪዎች ሁለቱን ማውጣት






በመጨረሻ አባከሱ ላይ የቀሩ ቆርኪዎች የሚወክሉት ቁጥር 12 ነው፡፡

ስለዚህ 35 – 23 = 12

**ምሳሌ 1.10** የሚከተሉትን ቁጥሮች ቀንሱ፡፡

ሀ. 56 – 45 ለ. 84 – 26

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 56 – 45 = 11 ወይም $\begin{array}{r} 56 \\ -45 \\ \hline 11 \end{array}$ ለ. 84 – 26 = 58 ወይም $\begin{array}{r} 84 \\ -26 \\ \hline 58 \end{array}$

**ማስታወሻ**

ከባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ላይ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ሲቀነስ፡-

1. የዋናው የአንድ ቤት ሆሄ ከተቀናሹ የአንድ ቤት ሆሄ የሚበልጥ ከሆነ በየቤታቸው ቀንሶ ውጤቱን ማስቀመጥ፡፡
2. የዋናው የአንድ ቤት ሆሄ ከተቀናሹ የአንድ ቤት ሆሄ የሚያንስ ከሆነ፡- ከአስር ቤት ሆሄ አንድ አስር በመበደርና ከአንድ ቤት ሆሄ ጋር በመደመር በቤት በቤቱ መቀነስ፡፡

## መልመጃ ሠ

1. የሚከተሉትን ቀንሱ፡፡

   ሀ. 67 - 46 ሐ. 81 - 58

   ለ. 48 - 27 መ. 87 - 59
2. 78 ኩንታል ጤፍ ከ66 ኩንታል ጤፍ በስንት ኩንታል ይበልጣል?
3. አህመድ በኪሱ የያዘው ብር አዳነ ከያዘው ብር በ15 ይበልጣል፡፡ አዳነ የያዘው ብር 30 ቢሆን ሱልጣን የያዘው ብር ስንት ይሆናል?

## እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት

ከዚህ በፊት በሁለተኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርታችሁ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና 9 ማባዛት ትከልሳላችሁ፡፡

**ምሳሌ 1.11** የሚከተለውን የስሌት መኪና ምስል አበዛዝ ተጠቅማችሁ በምሳሌው መሰረት አስሉ፡፡




**መፍትሔ፡-** የስሌቱ መኪና በግራ በኩል ያሉትን ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በ 6 በማባዛት መልሱን በቀኝ በኩል ይፅፋል፡፡ ስለዚህ

$10 \times 6 = 60$፣ $20 \times 6 = 120$ እና $40 \times 6 = 240$

## ተግባር 1.6

1. ከዚህ በታች ያሉትን የአበባ ምድቦች ተመልከቱና ቀጥሎ የተሰጡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡





ሀ. አበባዎችን የያዙ ምድቦች ስንት ናቸው?

ለ. በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ስንት አበባዎች አሉ?

ሐ. በጠቅላላ በሁሉም ምድቦች ስንት አበባዎች አሉ?

2. ከዚህ በታች የተቀመጡትን የጠጠር ምድቦች ተመልከቱና ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡



ሀ. ጠጠሮችን የያዙ ምድቦች ስንት ናቸው?

ለ. በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ስንት ጠጠሮች አሉ?

ሐ. በጠቅላላ በሁሉም ምድቦች ስንት ጠጠሮች አሉ?

**ማስታወሻ**

ሁሉም ተደማሪዎች አንድ አይነት ከሆኑ ማባዛት የመደመር አጭር አሰራር ነው፡፡

**ምሳሌ 1.12**

ሀ. 11 + 11 + 11 የሚለውን 11 x 3 ወይም 3 x 11 ብለን መፃፍ እንችላለን፡፡

ለ. 14 + 14 + 14 + 14 + 14 የሚለውን 14 x 5 ወይም 5 x 14 ብለን መፃፍ እንችላለን፡፡

## መልመጃ ረ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች አባዙ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. 45 x 2 | ሐ. 65 x 4 | ሠ. 77 x 6 | ሰ. 85 x 8 |
| ለ. 53 x 3 | መ. 74 x 5 | ረ. 83 x 7 | ሸ. 92 x 9 |

2. እያንዳንዳቸው 45 ሎሚዎችን የያዙ 6 ቅርጫቶች ቢኖሩ በጠቅላላው ስንት ሎሚዎች ይኖራሉ?
3. አበራ አንዱን ደብተር በ5 ብር ቢገዛ፤ 12ቱን ደብተሮች በስንት ብር ይገዛቸዋል?

## እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማካፈል

በሁለተኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል ተምራችኋል፡፡ በሦስተኛ ክፍልም ይህንኑ አጠናክራችሁ ትማራላችሁ፡፡

**ምሳሌ 1.13**

የሚከተለውን የስሌት መኪና ምስል የማካፈል አሰራር ተጠቅማችሁ በምሳሌው መሰረት አስሉ




**መፍትሔ፡-**

የስሌት መኪና በግራ በኩል ያሉትን ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ለ 4 በማካፈል በቀኝ በኩል መልሱን ይፅፋል፡፡ ስለዚህ

20 ÷ 4 = 5

40 ÷ 4 = 10

60 ÷ 4 = 15

## ተግባር 1.7

1. በአንድ ምድብ ውስጥ 16 ጠጠሮች አሉ፡፡



እነዚህ 16 ጠጠሮች በሚከተለው አይነት መንገድ ተመድበዋል፡፡ ምድቦቹን በመመልከት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡



ሀ. ስንት ምድቦች አሉ?

ለ. በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ስንት ጠጠሮች አሉ?

2. የአንድ ኪሎ ግራም ሙዝ ዋጋ 6 ብር ነው፡፡ በ72 ብር ስንት ኪሎ ግራም ሙዝ መግዛት ይቻላል?

## መልመጃ ሰ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 24 ÷ 6 =_______ ሐ. 80 ÷ 8 =________

ለ. 35 ÷ 7 =________ መ. 90 ÷ 9 =________

2. አራት ሰራተኞች የቀን ስራ ሰርተው ያገኙትን 88 ብር እኩል ቢካፈሉ የአንዱ ሰራተኛ ድርሻ ስንት ብር ይሆናል?
3. መሠረት 96 ገፅ ያለውን መፅሀፍ ማንበብ ጀመረች፡፡ በቀን 8 ገፅ ብታነብ መፅሐፉን በስንት ቀን አንብባ ትጨርሳለች?

### በመሠረታዊ የሂሳብ ስሌቶች መካከል ያለ ዝምድና

### 1. መደመርና መቀነስ

## ምሳሌ 1.14

**የሚከተሉት ስሌቶች ትክክል መሆናቸውን አረጋግጡ፡፡**

ሀ. 46 + 25 = 71 ሐ. 66 – 19 = 47

ለ. 53 + 37 = 80 መ. 75 – 28 = 57

**መፍትሔ:-**

ሀ. 46 + 25 = 71 ትክክል ነው። ምክንያቱም 71 – 46 = 25 እውነት ነው።
ለ. 53 + 37 = 80 ትክክል አይደለም። ምክንያቱም 80 – 53 = 37 ሀሰት ስለሆነ።
ሐ. 66 - 19 = 47 ትክክል ነው። ምክንያቱም 66 = 47 + 19 እውነት ስለሆነ።
መ. 75 - 28 = 57 ትክክል አይደለም። ምክንያቱም 57 + 28 = 75 ሀሰት ስለሆነ።

**ማስታወሻ**

ሀ. የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ድምር ሀ + ለ = ሐ ቢሆን ሐ - ሀ = ለ ወይም ሐ - ለ = ሀ ሁልጊዜ እውነት ነው።
ለ. የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ልዩነት መ - ረ = ሠ ቢሆን መ = ሠ + ረ ሁልጊዜ እውነት ነው።

## 2. ማብዛትና ማካፈል

**ምሳሌ1.15**

የሚከተሉት ስሌቶች ትክክል መሆናቸውን አረጋግጡ።

ሀ. 14 × 6 = 74 ለ. 84 ÷ 6 = 14

**መፍትሔ:-**

ሀ. 14 × 6 = 74 ትክክል አይደለም። ምክንያቱም 74 ÷ 6 ≠ 14 ስለሆነ።
ለ. 84 ÷ 6 = 14 ትክክል ነው። ምክንያቱም 84 = 14 × 6 እውነት ስለሆነ።

**ማስታወሻ**

ሀ. "ሀ" እና "ለ" ከዜሮ የተለዩ ሁለት ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑ እና ሀ × ለ = ሐ ከሆነ ሐ÷ሀ = ለ ወይም ሐ÷ለ = ሀ ሁልጊዜ እውነት ነው።
ለ. "መ" እና "በ" ሙሉ ቁጥሮች ሆነው (በ ከዜሮ የሚበልጥ ሙሉ ቁጥር ቢሆን) መ ÷ በ = ቀ እውነት ከሆነ መ = ቀ × በ ሁልጊዜ እውነት ነው።

## መልመጃ ሸ

1. የሚከተሉት ስሌቶች ትክክል መሆናቸውንና አለመሆናቸውን አረጋግጡ።
   ሀ. 56 + 34 = 90 ሐ. 24 x 5 = 100
   ለ. 78 – 29 = 59 መ. 96 ÷ 8 = 14
2. 90 ደብተሮች ለ5 ልጆች እኩል ቢከፋፈል የአንዱ ልጅ ድርሻ ስንት ደብተሮች ይሆናል?

## 1.3 የ100 እና የ1000 ብዜቶች እስከ 10,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች

ሙሉ ቁጥሮችን በ10 ማባዛት በ2ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ እስከ 1000 የሚደርሱ ሙሉ ቁጥሮችን በ100 ማባዛት ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 1.8

የሚከተሉትን ሰንጠረዦች በደብተራችሁ ላይ ገልብጡና ጥንድ ጥንድ በመሆን የጎደለውን ቁጥር ፃፉ፡፡

| × | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 100 | 0 | 100 | | | | 500 | | | | | 1000 |

| × | 10 | 20 | 30 | 40 | 50 | 60 | 70 | 80 | 90 | 100 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 100 | | 2000 | | | | 6000 | | | | 10,000 |

**ማስታወሻ**

- የመጨረሻ ሆሄያቸው ዜሮ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ሁሉ የአስር ብዜት ናቸው፡፡
- የመጨረሻ ሁለት ሆሄያቸው ዜሮ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ሁሉ የ100 ብዜቶች ናቸው፡፡
- ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በ "0" ሲባዛ ውጤቱ 0 ነው፡፡

### ምሳሌ 1.16

ከሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ የ100 ብዜት የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. 50 ለ. 600 ሐ. 705

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 50 የ100 ብዜት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የ50 የመጨረሻ ሁለቱ ሆሄዎች ዜሮ አይደሉም፡፡
ለ. 600 የ100 ብዜት ነው፡፡ ምክንያቱም የ600 የመጨረሻዎቹ ሁለት ሆሄዎች ዜሮ በመሆናቸው፡፡
ሐ. 705 የ100 ብዜት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የ705 የመጨረሻዎቹ ሁለት ሆሄያት ዜሮ ባለመሆናቸው፡፡

### መልመጃ ቀ

1. ከሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ የ100 ብዜት የሆኑት የትኞቹ ናቸው?
   ሀ. 850 ለ. 1000 ሐ. 100 መ. 1090
2. ትንሹ የ100 ብዜት ሙሉ ቁጥር ስንት ነው?
3. በ2500 እና በ3200 መካከል የሚገኙትን የ100 ብዜት ሙሉ ቁጥሮች ዘርዝሩ፡፡

*4. 888 የ100 ብዜት አይደለም:: ለምን? አብራሩ::*
*5. 900 የ100 ብዜት ነው:: ለምን? አብራሩ::*
*6. 8890 የ1000 ብዜት አይደለም:: ለምን? አብራሩ::*
*7. 9000 የ1000 ብዜት ነው:: ለምን? አብራሩ::*

ሙሉ ቁጥሮችን በ100 ማባዛት ተምራችኋል:: አንድን ሙሉ ቁጥር በ100 ማባዛት ማለት ከቁጥሩ በስተቀኝ ሁለት ዜሮዎችን በመፃፍ መግለፅ ማለት ነው:: አሁን ደግሞ ሙሉ ቁጥሮችን በ1000 ማባዛት ትማራላችሁ::

## ተግባር 1.9

የሚከተለውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ አሟልታችሁ ፃፉ:: ደብተራችሁን ከጓደኛችሁ ጋር በመቀያየር የሠራችሁትን መልስ በውይይት አረጋግጡ::

| x | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1000 | 0 | | 2000 | | | | | 7000 | | | 10,000 |

**ማስታወሻ**

**የመጨረሻ ሦስት ሆሄያቸው ዜሮ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች የ1000 ብዜት ናቸው::**

## ምሳሌ 1.17

ሀ. 8000 የ1000 ብዜት ነው:: ምክንያቱም 8000 = 8 × 1000 የመጨረሻ ሦስት ሆሄዎች ዜሮ ስለሆኑ::

ለ. 6700 የ1000 ብዜት አይደለም:: ምክንያቱም የ6700 የመጨረሻ ሦስት ሆሄዎች ዜሮ ስላልሆኑ::

## መልመጃ በ

1. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ::
   ሀ. 0 የ1000 ብዜት ነው::
   ለ. 1000 የ1000 ብዜት ነው::
   ሐ. 900 የ1000 ብዜት ነው::
   መ. ሁሉም የ100 ብዜቶች የ1000 ብዜቶች ናቸው::
   ሠ. ሁሉም የ1000 ብዜቶች የ100 ብዜቶች ናቸው::

2. አንድ ጠንካራ ገበሬ 20 በጎችን አድልቧል፡፡ ሁሉም በጐች ተመሣሣይ ዋጋ ቢኖራቸው እና የአንዱ በግ ዋጋ 500 ብር ቢሆን የ20 በጎች ዋጋ ስንት ብር ይሆናል?
3. በ1000 እና በ10,000 መካከል ያሉትን የ1000 ብዜቶች ዘርዝሩ፡፡
4. የ1000 ብዜት የሆነ የ3000 ተከታይ ሙሉ ቁጥርን ፃፉ፡፡
5. የ1000 ብዜት የሆነ የ7000 ቀዳማይ ሙሉ ቁጥርን ፃፉ፡፡

## 1.4 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች

### ተግባር 1.10

ከዚህ በታች ያሉትን ምስሎች ተመልከቱና በምሳሌው መሠረት ክፍት ቦታዎችን ሙሉ፡፡

1.




15 = 10 + 5

2.




_________ = ________ + _______

**ማስታወሻ**

አንድን ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ10 ብዜትና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ስንገልፅ በሚከተለው መንገድ ነው፡፡ ከቁጥሩ በስተቀኝ የ "=" አስቀምጠን በ10 ቤት የሚገኘውን በ10 ማባዛትና በአንድ ቤት የሚገኘውን መደመር፡፡

### ምሳሌ 1.18

**የሚከተሉትን ቁጥሮች በ10 ብዜትና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ግለፁ፡፡**

ሀ. 37 ለ. 50 ሐ. 78

**መፍትሔ:-**

ሀ. 37 = 30 + 7

ለ. 50 = 50 + 0

ሐ. 78 = 70 + 8

## መልመጃ ተ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች በ10 ብዜትና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ፃፉ፡፡
   ሀ. 29 ለ. 46 ሐ. 51 መ. 99
2. ወርቅነሽ 12 ኪሎ ሙዝ አላት፡፡ አንዱን ኪሎ ሙዝ በ6 ብር ሂሳብ ሸጠች፡፡ ወርቅነሽ ያላትን ሙዝ በሙሉ ብትሸጥ ስንት ብር ታገኛለች? የምታገኘውን ጠቅላላ ብር በ10 ብዜትና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ግለፁ፡፡

## ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በ100 ብዜት፣ በ10 ብዜትና በባለ አንድ ሆሄ ድምር መግለፅ

**ተግባር 1.11**

በስተቀኝ በኩል በቁጥር ቤት የተዘጋጀውን አባክስ ተመልከቱና ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

ሀ. በአንድ ቤት ስንት ቶርኪዎች አሉ?

ለ. በአስር ቤት ስንት ቶርኪዎች አሉ?

ሐ. በመቶ ቤት ስንት ቶርኪዎች አሉ?

መ. በአባከሱ የተመለከተውን ቁጥር በባለ ሦስት ሆሄ አድርጋችሁ ፃፉ፡፡




**ማስታወሻ:-**

አንድን ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ100 ብዜት፣ በ10 ብዜትና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ለመግለፅ:- ሆሄዎችን በቤት በቤታቸው አባዝተን በመደመር መፃፍ ነው፡፡

**ምሳሌ 1.19**

የሚከተሉትን ቁጥሮች በ100 ብዜት፣ በ10 ብዜት እና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ፃፉ፡፡

ሀ. 486 ለ. 705

**መፍትሔ:-**

ሀ. 486 = 4 × 100 + 8 × 10 + 6 x 1= 400 + 80 + 6

ለ. 705 = 7 × 100 + 0 × 10 + 5 x 1 = 700 + 0 + 5

## መልመጃ ቸ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች በ100 ብዜት፣ በ10 ብዜትና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ፃፉ፡፡
   ሀ. 349 ለ. 606 ሐ. 875
2. በቁጥር ቤት የተከፋፈለ አባከስ አዘጋጁ፡፡ ቆርኪዎችን በመጠቀም ከዚህ በታች የቀረቡትን ቁጥሮች በአባከሱ አመልክቱ፡፡
   ሀ. 743 ለ. 566 ሐ. 489
3. አህመድ በ125 ብር የሒሳብ መፅሐፍቶችን ገዛ፡፡ የእንግሊዝኛና የአካባቢ ሳይንስ መፅሐፍትን ደግሞ በ225 ብር ገዛ፡፡ አህመድ መፅሐፍቱን ለመግዛት በጠቅላላ ያወጣውን ብር በ100 ብዜት፣ በ10 ብዜትና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ፃፉ፡፡

በንዑስ ምዕራፍ አንድ እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች እንዴት እንደሚነበቡና እንደሚፃፉ ተምራችኃል፡፡ አሁን ደግሞ የቁጥር ቤት ዋጋን በመጠቀም እንዴት እንደሚገለፁ ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 1.12

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
   ሀ. 541 ለ. 809 ሐ. 999
2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በፊደል ፃፉ፡፡
   ሀ. 327 ለ. 601 ሐ. 797

**ማስታወሻ**

ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በቁጥር ቤት ዋጋ እንዴት እንደሚገለፅ ለማወቅ 878ን ለምሳሌ እንውሰድ፡-

በአንድ ቤት የሚገኘው ሆሄ 8 ነው፡፡

የቁጥር ቤት ዋጋው $8 \times 1 = 8$ ነው፡፡

በአስር ቤት የሚገኘው ሆሄ 7 ነው፡፡

የቁጥር ቤት ዋጋው $7 \times 10 = 70$ ነው፡፡

በመቶ ቤት የሚገኘው ሆሄ በስተግራ ያለው 8 ነው፡፡

የቁጥር ቤት ዋጋው $8 \times 100 = 800$ ነው፡፡

ስለዚህ የ878 የቁጥር ቤት ዋጋ ሰንጠረዥ በመጠቀም እንደሚከተለው ይፃፋል፡፡

| የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
| 8 | 7 | 8 |

## መልመጃ ነ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ ሰንጠረዥ ተጠቅማችሁ ፃፉ፡፡
   ሀ. 101 ለ. 799 ሐ. 865
2. ደጉ አንድ ሞባይል ስልክ በ686 ብር ገዛ፡፡ ደጉ ሞባይሉን በገዛበት ዋጋ ቁጥር ውስጥ 8 ቁጥር የስንት ቤት ቁጥር ነው?



3. በስተቀኝ ያለውን የቁጥር ቤት ዋጋ ሰንጠረዥ ተጠቅማችሁ የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ፃፉ፡፡
   ሀ. 4630 ለ. 8607 ሐ. 9002

| የሺ ቤት | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|
| | | | |

## 1.5 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

### ተግባር 1.13

1. ሁለት እኩል የሆሄያት ብዛት ያላቸው ሙሉ ቁጥሮች እንዴት እንደሚወዳደሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡
2. ሁለት የተለያዩ የሆሄያት ብዛት ያላቸው ሙሉ ቁጥሮች እንዴት እንደሚወዳደሩ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ፡፡

**ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል እንዴት እንደምናስቀምጥ ታስታውሳላችሁ?**
**ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ለመፃፍ የእያንዳንዱን ቁጥር ሆሄያት ብዛት በማየትና በማወዳደር ይሆናል፡፡**

### ምሳሌ 1.20

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡
   816፣ 97፣ 754፣ 89
2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡
   546፣ 63፣ 929፣ 794፣ 38
3. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ጻፉ፡፡
   8287፣ 9982፣ 3245፣ 2495
4. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ጻፉ፡፡
   2899፣ 9880፣ 1267፣ 8764፣ 5348

**መፍትሔ:-**

1. መጀመሪያ ባለ ሁለት ሆሄያት የሆኑትን ማወዳደር። ቀጥሎ ባለ ሦስት ሆሄያት የሆኑትን ማወዳደር። ስለዚህ ሙሉ ቁጥሮቹ ከትንሽ ወደ ትልቅ ሲፃፉ 89፣ 97፣ 754፣ 816።
2. በ1ኛው አሰራር መሠረት ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል ሲፃፍ:-
   929፣ 794፣ 546፣ 63፣ 38 ይሆናል።
3. በ1ኛው አሰራር መሠረት ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ሲፃፍ:-
   2134፣ 4235፣ 5520፣ 8243
4. በ1ኛው አሰራር መሠረት ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ሲፃፍ:-
   8998፣ 2773፣ 2455፣ 2001

## መልመጃ ኘ

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች መልሶቻችሁን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቁጥሮች ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል ፃፉ።
   ሀ. 666፣ 721፣ 729፣ 698
   ለ. 572፣ 587፣ 553፣ 408፣ 460
2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቁጥሮች ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል ፃፉ።
   ሀ. 833፣ 829፣ 908፣ 86፣ 92
   ለ. 547፣ 665፣ 632፣ 514፣ 677
3. አርሶ አደር ተሰማ ካመረቱት ውስጥ 1 ኩንታል በቆሎ በ198 ብር፣ 1 ኩንታል ገብስ በ247 ብር፣ 1 ኩንታል አተር በ325 ብር፣ 1 ኩንታል ጤፍ በ750 ብር እና 1 ኩንታል ድንች በ97 ብር ሸጡ።
   ሀ. አቶ ተሰማ እያንዳንዱን የምርት ዓይነት ሸጠው ያገኙትን የብር መጠን ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል ፃፉ።
   ለ. እያንዳንዱን የምርት አይነት ሸጠው ያገኙትን የብር መጠን ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል ፃፉ።

## ከአምስት ያላነሱ ባለ ሦስት ሆሄያት ሙሉ ቁጥሮች ቅደም ተከተል

### ተግባር 1.14

1. ሁለት ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች እንዴት እንደሚወዳደሩ ምሳሌዎችን በመመስረት ለጓደኞችሁ አስረዱ።
2. ስድስት እንቁላል ጣይ ደሮዎች ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ እና ረ የሚል ስም ተሰጥቷቸዋል። በአንድ አመት የሚጥሉት እንቁላል በምስሎች ተገልጿል። የሚጥሉትን እንቁላል መጠን ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል አስቀምጡ።

ሀ

120

ለ

200

ሐ

140

መ

170

ሠ

210

ረ

245

**ማስታወሻ**

**ባለ ሦስት ሆሄያት ሙሉ ቁጥሮችን ስታወደድሩና በቅደም ተከተል ስታስቀምጡ፡- የቁጥሮቹን ሆሄያት በቤት በቤታቸው በማወዳደር ይሆናል፡፡**

### ምሳሌ 1.21

**የሚከተሉትን ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡**

369፣ 373፣ 226፣ 598፣ 119፣ 603፣ 480

**መፍትሔ፡-**

*መጀመሪያ በመቶ ቤት፣ ቀጠሎ በአስር ቤት እና በመጨረሻ በአንድ ቤት ያሉትን ሆሄዎች ማወደደር፡፡ በዚህ መሠረት ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ሲፃፉ፡-*

119፣ 226፣ 369፣ 373፣ 480፣ 598 እና 603 ይሆናል፡፡

## መልመጃ ከ

**የሁሉንም ጥያቄዎች መልስ በደብተራችሁ በመፃፍ መልሱ፡፡**

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡
   ሀ. 175፣ 109፣ 357፣ 475፣ 457
   ለ. 523፣ 532፣ 641፣ 614፣ 632፣ 623
2. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡
   ሀ. 296፣ 309፣ 269፣ 320፣ 913፣ 174
   ለ. 745፣ 754፣ 806፣ 860፣ 608፣ 680
3. አቶ አህመድ የጫማ መሸጫ ሱቅ አላቸው፡፡ አቶ አህመድ አንዱን ጥንድ ጫማ በ175 ብር ይሸጣሉ፡፡ ከሰኞ እስከ አርብ የሸጧቸው ጥንድ ጫማዎች ብዛት ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ተገልጿል፡፡ በየቀኑ የሸጡትን ጥንድ ጫማዎች ዋጋ መሰረት በማድረግ ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ፃፍ፡፡

| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሀሙስ | አርብ |
|---|---|---|---|---|
| 1 ጥንድ ጫማ | 2 ጥንድ ጫማ | 4 ጥንድ ጫማ | 3 ጥንድ ጫማ | 5 ጥንድ ጫማ |

**4.የሚከተሉትን ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ፃፉ።**

*ሀ. 6998፣ 7668፣ 9128፣ 3428፣ 2088፣ 1000*

*ለ. 8889፣ 8809፣ 2888፣ 9007፣ 2008፣ 7008*

**5. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ፃፉ።**

*ሀ. 2881፣ 2100፣ 1223፣ 9988፣ 8008፣ 9009*

*ለ. 4231፣ 3285፣ 7889፣ 6389፣ 7445፣ 3422*

## ሁለት ባለ ሦስት ሆሄያት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮች

ብዙ ጊዜ በሁለት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮችን ለተለያዩ አገልግሎቶች እንፈልጋቸዋለን። ለምሳሌ በ 20 እና በ 40 መካከል የሚገኝ የ 10 ብዜት ሙሉ ቁጥር ሲሆን ይችላል። በሁለት ነገሮች መካከል የሚኖርን ነገር በቀላሉ ለማግኘት የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከቱ።

### ምሳሌ 1.22

አቤል፣ ደጉና መልካሙ ወንድማማቾች ናቸው። ከሦስቱም ታናሹ ልጅ አቤል ሲሆን፤ ከሦስቱ ታላቁ ልጅ ደግሞ መልካሙ ነው። በእድሜ ሲወዳደሩ በአቤልና በመልካሙ መካከል የሚገኘው ማነው? በአቤልና በመልካሙ መካከል የሚገኘው ደጉ ነው።

### ተግባር1.15

ከዚህ በታች ያሉትን ምስሎች ተመልከቱና ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎችን መልሱ፡-



ኑሩ　　　አራጋው　　　ሰብለ　　　ማህሌት　　　አህመድ

1. በኑሩና በሰብለ መካከል ያለው ማነው?
2. በኑሩና በአህመድ መካከል ስንት ተማሪዎች አሉ?
3. በኑሩና በአህመድ መካከል ያሉትን ተማሪዎች ስም ዘርዝሩ።

### ምሳሌ 1.23

**ከዚህ በታች በተሰጡ ሙሉ ቁጥሮች መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮችን ዘርዝሩ።**

*ሀ.* በ345 እና በ348　　　　*ለ.* በ782 እና በ789

**መፍትሔ:-** መጀመሪያ ከተሰጡት ሁለት ቁጥሮች ትንሹን መርጦ መፃፍ። ከዚያም እስከ ትልቁ ቁጥር ድረስ ተከታታይ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል መፃፍ። በዚህ መሠረት:-

ሀ. ከትንሹ ቁጥር እስከ ትልቁ በቅደም ተከተል ሲጻፍ 345፣ 346፣ 347፣ 348 በመሆኑ በ345 እና በ348 መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮች 346 እና 347 ናቸው።

ለ. ከትንሹ ቁጥር እስከ ትልቁ በቅደም ተከተል ሲጻፍ 782፣ 783፣ 784፣ 785፣ 786፣ 787፣ 788፣ 789 በመሆኑ በቅደም ተከተል በ782 እና በ789 መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮች 783፣ 784፣ 785፣ 786፣ 787 እና 788 ናቸው።

## መልመጃ ኸ

1. ከዚህ በታች ለቀረቡት የጎደሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቅደም ተከተል በተሰጠው ክፍት ቦታ ፃፉ።
   - ሀ. 116፣ ______፣ ______፣ ______፣ ______፣ 121
   - ለ. 303፣ ______፣ ______፣ ______፣ ______፣ ______፣309
   - ሐ. 866፣ ______፣ ______፣ ______፣ ______፣ ______፣872

2. በሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮችን ፃፉ።
   - ሀ. በ248 እና በ253
   - ለ. በ511 እና በ517
   - ሐ. በ877 እና በ883
   - መ. በ904 እና በ910

### ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን የ $<$ ፣ $>$ እና $=$ ምልክቶችን በመጠቀም ማወዳደር

እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር ቀደም ሲል ተምራችኋል። አሁን ደግሞ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በተመሳሳይ መንገድ ታወዳድራላችሁ።

**ምሳሌ 1.24**

የ $<$ ፣ $>$ ወይም $=$ ምልክቶችን በመጠቀም የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አወዳድሩ።

ሀ. 3046 --------- 3048

ለ. 4127 ---------- 4109

ሐ. 6728 --------- 6728

**መፍትሔ:-** ሁለት አንድ አይነት የሆሄያት ብዛት ያላቸውን ሙሉ ቁጥሮች ስታወዳድሩ በቤት በቤታቸው ማወዳደር ነው። (ከግራ በመጀመር)

ሀ. $3046 < 3048$ ምክንያቱም የሺ፣ የመቶና የአስር ቤት ሆሄያቸው አንድ አይነት ቢሆንም የአንድ ቤት ሆሄያት $6 < 8$ ስለሆነ።

ለ. $4127 > 4109$ ምክንያቱም የሺ እና የመቶ ቤት ዋጋቸው እኩል ቢሆንም የአስር ቤት ሆሄያት $2 > 0$ ስለሆነ።

ሐ. $6728 = 6728$ ምክንያቱም ሁሉም ተዛማጅ የቤት ዋጋዎች እኩል ስለሆኑ።

## መልመጃ ወ

1. የ < ፣ > ወይም = ምልክቶችን በመጠቀም የሚከተሉትን ጥንድ ቁጥሮች አወዳድሩ፡፡
   ሀ. 6814--------- 6911　　ሐ. 8341----------- 7999
   ለ. 9210----------9091　　መ. 6410-------- 3205 × 2
2. ከዚህ በታች የተሰጡ ሙሉ ቁጥሮችን ከትንሹ በመጀመር በቅደም ተከተል ፃፏቸው፡፡
   ሀ. 3625፣ 3780፣ 3781፣ 2914
   ለ. 6341፣ 8200፣ 5896፣ 4791
3. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሙሉ ቁጥሮች ከትልቁ በመጀመር በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡
   ሀ. 8614፣ 8461፣ 8625፣ 8421
   ለ. 9521፣ 9549፣ 8473፣ 9637

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

- ባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች የሚባሉት ከ0 እስከ 9 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው፡፡
- ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ከ10 እስከ 99 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው፡፡ (10፣ 11፣ 12፣ እያለ እስከ 99 ይቀጥላል)፡፡
- ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ከ100 እስከ 999 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው፡፡ (100፣ 101፣ 102 እያለ እስከ 999 ይቀጥላል)፡፡
- ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ከ1000 እስከ 9,999 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው፡፡
- “ሀ” ከዜሮ የሚበልጥ ሙሉ ቁጥር ቢሆን ሀ - 1 የ “ሀ” ቀዳማይ ነው፡፡
- 0 ቀዳማይ የሌለው ሙሉ ቁጥር ነው፡፡
- “ለ” ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ቢሆን ለ +1 የ “ለ” ተከታይ ነው፡፡
- ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን ለማወዳደር የ < ፣ > ወይም = ምልክት እንጠቀማለን፡፡
- የሁለት ሙሉ ቁጥሮች የሆሄያት ብዛት የተለያ ከሆነ፤ ብዙ ሆሄያት ያለው ይበልጣል፡፡

የሁለት ሙሉ ቁጥሮች የሆሄያት ብዛት እኩል ከሆነ፤ የቁጥሮቹን ሆሄያት ከግራ በመጀመር በቤት በቤታቸው ማወዳደር፡፡

የሂሳብ ስሌቶችን ውጤት ለማረጋገጥ የሂሳብ ስሌቶችን ዝምድና እንጠቀማለን፡፡

የመደመርን ውጤት በመቀነስ
የመቀነስን ውጤት በመደመር
የማባዛትን ውጤት በማካፈል
የማካፈልን ውጤት በማባዛት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

የ10 ብዜቶች ቢያንስ የአንድ ቤት ሆሄያቸው ዜሮ ነው፡፡
የ100 ብዜቶች ቢያንስ ሁለት የአንድና የአስር ቤት ሆሄያቸው ዜሮ ነው፡፡
የ1000 ብዜቶች ቢያንስ ሶስቱ የአንድ፣ የአስርና የመቶ ቤት ሆሄያቸው ዜሮ ነው፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡
   ሀ. የ99 ተከታይ ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ነው፡፡
   ለ. የ309 ቀዳማይ 310 ነው፡፡
   ሐ. 507 < 509 < 511 < 495 < 494
   መ. በ420 እና በ430 መካከል 10 ሙሉ ቁጥሮች አሉ፡፡
   ሠ. 6345 = 6000 + 300 + 40 + 5
2. የትልቁ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ተከታይ ስንት ነው?
3. የትንሹ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ቀዳማይ ስንት ነው?
4. ቀዳማይ የሌለው ሙሉ ቁጥር ማነው?
5. በ507 እና በ514 መካከል ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ዘርዝሩ፡፡
6. የጎደለውን ሙሉ
   ሀ. 8404 = _____ x 1000 + _____ x 100 + _____ x 10 + _____ x 1
   ለ. 1768 = _____ x 1000 + _____ x 100 + _____ x 10 + _____ x 1
7. የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ 720 ብር ነው፡፡ የ10 ኩንታል ጤፍ ዋጋ ስንት ይሆናል?
8. በአንድ ት/ቤት ውስጥ 828 ተማሪዎች ይማራሉ፡፡ ለት/ቤቱ አጥር ማሰሪያ እያንዳንዱ ተማሪ አምስት አምስት ብር ቢያዋጣ በጠቅላላ ስንት ብር ይዋጣል?
9. ከዚህ በታች በፊደል የተፃፉትን ቁጥሮች በአሀዝ ፃፏቸው፡፡
   ሀ) አምስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ
   ለ) ስምንት ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ
   ሐ) ስድስት ሺ ዘጠና ስምንት
10. የሚከተሉትን ቁጥሮች በፊደል ፃፏቸው፡፡
    ሀ) 870 ለ) 886 ሐ) 707 መ) 898
11. በክፍት ቦታዎች ላይ የ > ፣ < ወይም = ምልክቶች በመጠቀም ቁጥሮቹን አወዳድሩ፡፡
    ሀ) 876 _______ 288 ሐ) 8800 ___________ 10,008
    ለ) 897 ________10,000 መ) 2380 ___________ 2380
12. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቁጥሮች፤
    ሀ) ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡
    ለ) ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል ፃፍ፡፡
    1. 24፣ 88፣ 76፣ 99
    2. 445፣ 226፣ 766፣ 888፣ 999
    3. 4888፣ 5347፣ 8899፣ 9008፣ 9808

# ምዕራፍ ሁለት

# ልኬት

**የመማር ማስተማር ውጤቶች፡-**

- ርዝመትን ለመለካት የሚ.ሜ፣ ሳ.ሜ እና ሜ ምድብ መስፈሪያዎችን መጠቀም፡፡
- ይዘትን ለመለካት የሚ.ሊ እና ሊ ምድብ መስፈሪያዎችን መጠቀም፡፡
- መጠነ ቁስ / ክብደትን/ ለመለካት የግ እና ኪ.ግ ምድብ መስፈሪያዎችን መጠቀም፡፡
- የርዝመት፣ የይዘትና ክብደት ምድቦችን መቀየር፡፡

## 2.1 ርዝመትን በሚሊ ሜትር፣ በሳንቲ ሜትር፤ በሜትር እና በኪሎ ሜትር መለካት

### ተግባር 2.1

**በግል የሚሰሩ ጥያቄዎች፡፡**

ከዚህ በታች ያሉትን ስዕሎች ተመልከቱና ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡



እስክርቢቶ



እርሳስ



ፋጡማ



ከማል

ሀ. ከእርሳሱና ከእስክርቢቶው ርዝመቱ አጭር የሆነው የትኛው ነው?

ለ. ከፋጡማና ከከማል ማን ይረዝማል?

**ማስታወሻ፡-**

በትንንሽ ክፍሎች የተከፋፈለውን የማስመሪያ ክፍል ተመልከቱ፡፡




- የማስመሪያው የላይኛው ክፍል ርዝመትን በሚሊ ሜትር ለመለካት ያገለግላል፡፡
- ሚሊ ሜትር በአጭሩ ሲፃፍ ሚ.ሜ ተብሎ ነው፡፡
- ርዝመታቸው አነስተኛ የሆኑ ነገሮችን ለመለካት ሚ.ሜ እንጠቀማለን፡፡

## ምሳሌ 2.1

1. ብዙ ገፆች የሌሉት መፅሐፍትንና የጣውላዎችን ውፍረት ለመለካት ሚሊ ሜትርን (ሚ.ሜ) እንጠቀማለን፡፡


ጣውላ


መፅሐፍ

## መልመጃ ሀ

1. በሚሊ ሜትር የተከፋፈለ ማስመሪያ ተጠቅማችሁ የጓደኛችሁን የእጅ ጣቶች ለኩና በደብተራችሁ ፃፉ፡፡
2. ማስመሪያችሁን ተጠቅማችሁ በደብተራችሁ ላይ ርዝመታቸው 5 ሚ.ሜ፣ 7 ሚ.ሜ፣ 8 ሚ.ሜ እና 9 ሚ.ሜ ቀጥታ መስመሮችን አስምሩ፡፡

### የርዝመት መለኪያ ምድቦች ዝምድና

## ተግባር 2.2

**ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚሰራ፡፡**

1. ሚሊ ሜትርን ብቻ በመጠቀም የረዣዥም ነገሮችን ርዝመት መለካት አመች ይመስላችኋል?
2. ርዝመትን ለመለካት ከሚሊ ሜትር ሌላ የምታውቁት የርዝመት መለኪያ ምድብ አለ? የምታውቁት ካለ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ተግባር 2.3

1. በሳንቲ ሜትርና በሜትር መካከል ያለውን ዝምድና እና ልዩነት ተወያዩበት፡፡
2. በሳንቲ ሜትር፣ በሜትርና በኪሎ ሜትር መካከል ያለውን ዝምድና እና ልዩነት ተወያዩበት፡፡
3. ከሳንቲ ሜትር፣ ከሜትርና ከኪሎ ሜትር ትንሽ ርዝመት ያለውን ለመለካት የምትጠቀሙበት የትኛው ነው? ትልቅ ርዝመትስ ለመለካት የምትጠቀሙበት የትኛው ነው? በክፍል ውስጥ ተወያዩበት፡፡

## ምሳሌ 2.2

1. የእርሳስ ርዝመትን፣ የእስክርቢቶ ርዝመትን፣ ወዘተ ለመለካት ሳ.ሜ እንጠቀማለን፡፡
2. የሰው ቁመት፣ የቤት በር ቁመት፣ የጥቁር ሰሌዳ ርዝማኔ፣ወዘተ ለመለካት ሜትር እና ሳንቲ ሜትር እንጠቀማለን፡፡
3. በቤታችሁና በትምህርት ቤታችሁ፣ በአዲስ አበባና በባህርዳር ከተማ ወዘተ መካከል ያለውን ርቀት ለመግለፅ ኪሎ ሜትር እንጠቀማለን፡፡

## መልመጃ ለ

1. ማስመሪያችሁን በመጠቀም ከዚህ በታች በተሰጠው ርዝመት ልክ ቀጥታ መስመሮችን ሳሉ፡፡
   ሀ. 5 ሳ.ሜ ለ. 9 ሳ.ሜ ሐ. 15 ሳ.ሜ መ. 18 ሳ.ሜ

2. ከዚህ በታች ያሉትን ቀጥታ መስመሮች በማስመሪያችሁ ለኩና ርዝመታቸውን ፃፉ፡፡




በቸ= ________ ቀተ= ________ ወረ=________

3. ማስመሪያችሁን ተጠቅማችሁ በሰንጠረዡ የተፃፉትን ርዝመቶች ለክታችሁ ፃፉ፡፡

| የሚለካ | ርዝመት |
|---|---|
| የሒሳብ መጽሐፋችሁን ርዝመት | |
| የክፍላችሁን ዴስክ ቁመት | |
| የጓደኛችሁን ቁመት | |

## የቡድን ስራ

**ለቡድን ስራ የሚያገለግል ገመድ ከቡድን አባላት ረዥሙ (ረዥሟ) ልጅ ልክ አዘጋጁ፡፡ ገመዱን ማስመሪያ ተጠቅማችሁ፡-**

ሀ. 10 ሚ.ሜ ለኩና በእስክርቢቶ ምልክት አድርጉ፡፡ የለካችሁት በሳ.ሜ ስንት ነው?
ለ. 20 ሚ.ሜ ለኩና በእስክርቢቶ ምልክት አድርጉ፡፡ የለካችሁት በሳ.ሜ ስንት ነው?
ሐ.100 ሣ.ሜ ለኩና በእስክርቢቶ ምልክት አድርጉ፡፡ የለካችሁት በሜትር ስንት ነው?

በርዝመት መለኪያ ምድቦች መካከል ያለው ዝምድና በሚከተለው ማስታወሻ ቀርቧል፡፡

### ማስታወሻ

**በርዝመት መለኪያ ምድቦች መካከል ያለ ዝምድና፡-**

10 ሚ.ሜ = 1 ሳ.ሜ
100 ሳ.ሜ = 1 ሜ
1000 ሜ = 1 ኪ.ሜ

## ምሳሌ 2.3

1. 25 ሳ.ሜን ወደ ሚ.ሜ ቀይሩ፡፡
2. 5 ሜን ወደ ሳ.ሜ ቀይሩ፡፡
3. 6 ኪ.ሜን ወደ ሜ ቀይሩ፡፡

### መፍትሄ

1. 25 ሳ.ሜ = 25 x 10 ሚ.ሜ
   = 250 ሚ.ሜ
2. 5 ሜ = 5 x 100 ሳ.ሜ
   = 500 ሳ.ሜ
3. 6 ኪ.ሜ = 6 x 1000 ሜ
   = 6000 ሜ

## መልመጃ ሐ

1. የሚከተሉትን ከሳ.ሜ ወደ ሚ.ሜ ቀይሩ፡፡
   ሀ. 18 ሳ.ሜ ለ. 34 ሳ.ሜ ሐ. 75 ሳ.ሜ መ. 105 ሳ.ሜ
2. የሚከተሉትን ከሜትር ወደ ሳ.ሜ ቀይሩ፡፡
   ሀ. 7 ሜ ለ. 12 ሜ ሐ. 22 ሜ መ. 50 ሜ
3. የሚከተሉትን ከኪ.ሜ ወደ ሜትር ቀይሩ፡፡
   ሀ. 4 ኪ.ሜ ለ. 7 ኪ.ሜ ሐ. 9 ኪ.ሜ

4. የሚከተሉትን ስሩ፡፡
   ሀ. 23 ሳ.ሜ ከ57 ሚ.ሜን ወደ ሚ.ሜ ቀይሩ፡፡
   ለ. 8 ሜ ከ50 ሳ.ሜን ወደ ሳ.ሜ ቀይሩ፡፡
   ሐ. 6 ኪ.ሜ ከ325 ሜን ወደ ሜትር ቀይሩ፡፡

## ወደ ዝቅተኛው የርዝመት መለኪያ ምድብ በመቀየር ርዝመቶችን መደመር

የርዝመት መለኪያ ምድቦች ዝምድናን በተማራችሁበት ወቅት ከከፍተኛው ምድብ ወደ ዝቅተኛው ምድብ መቀየር ችላችኋል፡፡ አሁን ደግሞ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ምድብ በመቀየር ርዝመቶችን መደመር ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 2.4

1. ከአንድ ትልቅ ጣውላ ላይ ርዝመቱ 75 ሳ.ሜ የሆነ ተለክቶ ተቆረጠ፤ የተቆረጠው ጣውላ ርዝመት_______________ ሚ.ሜ ነው፡፡
2. የሚከተሉትን ምስሎች ተመልክታችሁ ቀጥሎ የተሰጡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

እንጨት 1



1 ሜ

እንጨት 2



50 ሳ.ሜ

እንጨት 1 እና እንጨት 2 ተገጣጥመው ሲለኩ _______ ሳ.ሜ ይሆናል፡፡

**ማስታወሻ**

**በሜትርና በሳ.ሜትር የተለኩ ርዝመቶችን በመደመር ወደ ሳ.ሜትር ለመቀየር፡-**
- **በመጀመሪያ በሜትር ያለውን ልኬታ በ100 አባዝቶ ወደ ሳ.ሜትር መቀየር፣**
- **ቀጥሎ የተቀየረውንና በሳ.ሜትር የተሰጠውን ልኬት መደመር፡፡**

### ምሳሌ 2.4

**የሚከተሉትን ርዝመቶች ደምሩ፡፡**

ሀ. 35 ሜ + 65 ሳ.ሜ

ለ. 42 ሜ ከ25 ሳ.ሜ + 55 ሳ.ሜ

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 35 ሜ + 65 ሳ.ሜ = 35 x 100 ሳ.ሜ + 65 ሳ.ሜ
= 3500 ሳ.ሜ + 65 ሳ.ሜ = 3565 ሳ.ሜ

ለ. 42 ሜ ከ25 ሳ.ሜ + 55 ሳ.ሜ = 42 x 100 ሳ.ሜ + 25 ሳ.ሜ + 55 ሳ.ሜ
= 4200 ሳ.ሜ + 80 ሳ.ሜ = 4280 ሳ.ሜ

## መልመጃ መ

1. የሚከተሉትን ደምሩ፡፡
   ሀ. 20 ሜ + 85 ሳ.ሜ
   ለ. 45 ሜ + 90 ሳ.ሜ
   ሐ. 35 ሳ.ሜ + 75 ሜ ከ50 ሳ.ሜ
   መ. 105 ሜ ከ50 ሳ.ሜ + 70 ሳ.ሜ

2. በክፍት ቦታው ውስጥ የ>፣ < ወይም = ምልክቶችን በመጠቀም የሚከተሉትን ርዝመቶች አወዳድሩ፡፡
   ሀ. 4 ሜ ___________ 350 ሳ.ሜ
   ለ. 5 ሜ ___________ 500 ሳ.ሜ
   ሐ. 6 ሜ ___________ 650 ሳ.ሜ

3. አንድ ጉንዳን ከ "ሀ" በመነሳት በ "ለ" እና "ሐ" በኩል አድርጎ "መ" ለመድረስ ስንት ሳ.ሜ ይጓዛል? (በቀኝ በኩል ያለውን ምስል ተመልከቱ)




### ወደ ትንሹ የርዝመት መለኪያ ምድብ በመቀየር የርዝመት ልዩነቶችን መፈለግ

የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ልዩነት እንዴት እንደሚፈለግ ታስታውሳላችሁ? እስኪ የ326 እና የ215 ልዩነት እንዴት እንደሚፈለግ ከጉናችሁ ለተቀመጠ ጓደኛችሁ አስረዱ፡፡ ልዩነቱ እንዴት እንደሚፈለግ ተግባባችሁ? መልካም ነው፡፡ እስኪ የሚከተለውን ተግባር ደግሞ ስሩ፡፡

### ተግባር 2.5

**ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚሰራ፡፡**

1. ከ2 ሜትር ገመድ ላይ 50 ሳ.ሜ ተቆርጦ ተጣለ፡፡ የቀረው ገመድ ስንት ሳ.ሜ ነው?



2 ሜትር ገመድ

2. የአቶ ተሰማ ቁመት 1 ሜትር ከ75 ሳ.ሜ ነው፡፡ የአቶ ተሰማ ልጅ ትዕግስት ቁመት ደግሞ 1 ሜ ከ40 ሳ.ሜ ነው፡፡ የትዕግስት ቁመት ከአባቷ ቁመት በምን ያህል ያንሳል?

> **ማስታወሻ**
> በሜትርና በሳ.ሜትር የተለኩ ነገሮች ልዩነት ሲፈለግ በመጀመሪያ ሜትሩን ወደ ሳ.ሜትር ወይም ሳ.ሜትሩን ወደ ሜትር መቀየር ፤ ቀጥሎ ልዩነቱን መፈለግ።

**ምሳሌ 2.5**

**የሚከተሉትን ርዝመቶች ልዩነቶች ፈልጉ።**

ሀ. 25 ሜ - 11 ሜ

ለ. 12 ሜ - 75 ሳ.ሜ

**መፍትሔ**

ሀ. ሁለቱም በአንድ አይነት ምድብ የተለኩ ስለሆነ፡- የቁጥሮችን ልዩነት ፈልጎ መልሱን መፃፍ። ማለትም፡-

25 ሜ - 11 ሜ= (25-11) ሜ = 14 ሜ

ለ. መጀመሪያ ሜትርን ወደ ሳ.ሜ መቀየር። ቀጥሎ ልዩነቱን መፈለግ። በዚህ መሠረት

12 ሜ - 75 ሳ.ሜ = 12 x 100 ሳ.ሜ - 75 ሳ.ሜ

= 1200 ሳ.ሜ - 75 ሳ.ሜ

= 1125 ሳ.ሜ

## መልመጃ ሠ

1. የሚከተሉትን ልኬቶች ቀንሱ እና መልሳችሁን በሳ.ሜ ፃፉ።

   ሀ. 4 ሜ - 2 ሜ ከ50 ሳ.ሜ

   ለ.. 5 ሜ ከ35 ሳ.ሜ - 3 ሜ ከ10 ሳ.ሜ

   ሐ. 7 ሜ ከ60 ሳ.ሜ - 4 ሜ ከ40 ሳ.ሜ

   መ. 12 ሜ ከ15 ሳ.ሜ - 8 ሜ ከ50 ሳ.ሜ

2. አሰፋ ከቤቱ ተነስቶ ወደ ትምህርት ቤት እየሔደ ነው። የአሰፋ ቤት ከሚማርበት ትምህርት ቤት በ765ሜ ከ60 ሳ.ሜ ይርቃል። አሰፋ የተጓዘው 500 ሜ ከ60ሳ.ሜ ቢሆን ትምህርት ቤቱ ለመድረስ ስንት ሜትር ይቀረዋል?

3. አቶ ሙስጠፋ 6ሜ ከ25 ሳ.ሜ ለሱሪ የሚሆን ጨርቅ አለው። አቶ ሙስጠፋ ካለው ጨርቅ ለሁለት ሱሪዎች 2ሜ ከ50ሳ.ሜ ተጠቀመ። አቶ ሙስጠፋ የቀረው ጨርቅ በሳ.ሜ ስንት ነው?

## 2.2 ይዘትን በሚሊ ሊትር /ሚ.ሊ/ እና በሊትር /ሊ/ መለካት

የተለያዩ የርዝመት መለኪያ ምድቦችን በመጠቀም የተለያዩ ነገሮችን ርዝመት መለካት እንደሚቻል ታውቃላችሁ። የነገሮችን ርዝመት እንደለካነው ሁሉ የፈሳሾችንም መጠን (ይዘቶችን) በተለያዩ የይዘት መለኪያ ምድቦች መለካት እንደሚቻል ትማራላችሁ።

## ተግባር 2.6

**በተናጠል የሚሰሩ።**

1. ከተዘረዘሩት ውስጥ ፈሳሽ ብቻ የሆኑትን ለዩ።


ውሃ


ቡና


ወተት


እንጨት


ድንጋይ

2. በቤታችሁ የተለያዩ ፈሳሾችን ለመያዝ ከምትጠቀሙባቸው እቃዎች ውስጥ የምታስታውሱትን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

እንደ ውሀ፣ ወተት፣ ዘይት፣ ሻይ፣ ለስላሳ፣ወዘተ የመሳሰሉት ፈሳሽ ይባላሉ።
የተለያዩ ፈሳሾችን ለመያዝ ከምንገለገልባቸው እቃዎች ውስጥ የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡-


ጣሳ


ጆግ


ኩባያ


የሻይ ሲኒ

**ማስታወሻ**

1. አንድ የፈሳሽ መያዣ እቃ ሊይዘው የሚችለው ከፍተኛ የፈሳሽ መጠን የዕቃው ይዘት ይባላል።
2. አነስተኛ የፈሳሽ መጠንን ለመለካት የምንጠቀምበት የፈሳሽ መለኪያ ምድብ **ሚሊ ሊትር** ይባላል። ሚሊ ሊትር በአጭሩ ሲፃፍ ሚ.ሊ ተብሎ ነው።

**ምሳሌ 2.6** የውሀ መያዣ ላስቲኮች፣ ክዳኖች እና ሲሪንጅ ሚሊ ሊትርን በመጠቀም ፈሳሽ የሚለኩ እቃዎች ናቸው።





## መልመጃ ረ

በሚሊ ሊትር የተከፋፈለ እቃ ወላጆቻችሁን ጠይቁና (ወይም በሰፈር ፈልጉና) ውሀ በመሙላት ወደ ቡና ሲኒ ገልብጡ፡፡ የቡናው ሲኒ በስንት ሚሊ ሊትር እንደሞላ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## በሚሊ ሊትርና በሊትር መካከል ያለ ዝምድና

ዝቅተኛ የፈሳሽ መጠን ለመለካት ሚሊ ሊትር መጠቀም እንደሚገባ ተምራችኋል፡፡ ከፍተኛ የፈሳሽ መጠን ለመለካት የሚያገለግለውን ምድብ ደግሞ አሁን ትማራላችሁ፡፡

- **ሊትር** የፈሳሽ መጠን ለመለካት የምንጠቀምበት ምድብ ነው፡፡ አንድ ሊትር ለመለካት ከምንጠቀምባቸው እቃዎች መካከል አንድ ሊትር የሚይዝ ጠርሙስ የተለመደ እቃ ነው፡፡



ጠርሙስ

## ተግባር 2.7

**በቡድን የሚሰራ**

1. የተለያዩ የፈሳሽ መጠን ሊይዙ የሚችሉ እቃዎችን ከቤታችሁ አምጡ፡፡ ለምሳሌ የተለያዩ መጠን ያላቸው የውሃ መያዣ ላስቲኮች፣ ጠርሙሶች፣ የውሃ ጣሳ፣ ጡጦ እና የመሳሰሉትን አምጡ፡፡ ከዚያም በቡድን ሆናችሁ እያንዳንዱ እቃ ምን ያህል ሊትር እንደሚይዝ እየለካችሁ አረጋግጡ፡፡
2. 500 ሚ.ሊ. በሚይዝ የውሃ ላስቲክ ውሃ እየሞላችሁ
   ሀ. 1 ሊትር የሚይዝን የውሃ ላስቲክ ሙሉ፡፡ በስንት ሚ.ሊ. ውሃ ተሞላ?
   ለ. 2 ሊትር የሚይዝን የውሃ ላስቲክ ሙሉ፡፡ በስንት ሚ.ሊ. ውሃ ተሞላ?

## ተግባር 2.8

1. በሊትርና በሚሊ ሊትር መካከል ያለውን ዝምድና እና ልዩነት ተወያዩበት፡፡
2. 4 ሊትር ስንት ሚሊ ሊትር ነው?
3. ከሊትርና ከሚሊ ሊትር ትንሽ ፈሳሽ ለመለካት የምትጠቀሙበት የትኛው ነው፡፡

## ምሳሌ 2.7

1. 3 ሊትር ስንት ሚሊ ሊትር ይሆናል?
2. 500 ሚሊ ሊትር ስንት ሊትር ይሆናል?

**መፍትሔ:-** 1. 3 ሊትር = 3 × 1000 ሚሊ. ሊትር
= 3000 ሚሊ. ሊትር

2. 500 ሚሊ. ሊትር = ግማሽ ሊትር

## መልመጃ ሰ

1. የሚከተሉትን ወደ ሚሊ. ሊትር ቀይሩ።
   ሀ. 4 ሊትር ለ. 5 ሊትር ሐ. 7 ሊትር
2. የ < ፣ > ወይም = ምልክት በመምረጥና በተሰጠው ቦታ ላይ በመጻፍ የሚከተሉትን ይዘቶች አወዳድሩ።
   ሀ. 2 ሊትር ________1500 ሚሊ. ሊትር
   ለ. 6000 ሚሊ. ሊትር ________ 6 ሊትር
   ሐ. 10,000 ሚሊ. ሊትር ________ 12 ሊትር

## 2.3 ክብደትን በግራም (ግ)፣ በኪሎግራም (ኪ.ግ) እና በኩንታል መለካት

በቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ የተለያዩ ክብደቶች ያላቸው እቃዎችን አስተውላችሁ ይሆናል። የተለያዩ ክብደቶችን ለመለካት የምንጠቀምባቸውን መሳሪያዎችና ምድቦች በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ትማራላችሁ።

### ተግባር 2.9

**በተናጠል የሚሰራ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

ሀ. ከሂሳብ መፅሐፋችሁ እና ከደብተራችሁ የሚከብደው የትኛው ነው?
ለ. ከሂሳብ መፅሐፋችሁ እና ከ እንግሊዝኛ መፅሐፋችሁ የሚከብደው የትኛው ነው?
ሐ. ከሦስቱ ነገሮች ቀላል ክብደት ያለው የትኛው ነው?

### ሚዛን

ሚዛን የአንድን እቃ ክብደት ለመለካት የሚያገለግል መሳሪያ ነው። በሚዛን አማካኝነት የአንድን እቃ ክብደት ለመለካት በአንድ በኩል እቃውን በሌላ በኩል ደግሞ የታወቀ የክብደት መለኪያ በማስቀመጥ ይሆናል።



**ማስታወሻ**

- ግራም ቀላል ክብደት ያላቸውን ነገሮች ለመለካት የምንጠቀምበት የክብደት መለኪያ ምድብ ነው።
- ኪሎ ግራም ክብደታቸው ከፍ ያሉ እቃዎችን ለመለካት የምንጠቀምበት የክብደት መለኪያ ምድብ ነው።

## መልመጃ ሸ

1. የተለያዩ እቃዎች ክብደት እንዴት እንደሚለካ በአካባቢያችሁ በሚገኙ ሱቆች በመሄድ ወይም ወላጆቻችሁን ጠይቁና ተረዱ፡፡ የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ክፍል ውስጥ አስረዱ፡፡
2. በቡድን ሁናችሁ ትምህርት ቤት ውስጥ በተዘጋጁ ሚዛኖች የተለያዩ እቃዎችን ክብደት ለኩ፡፡ (ለምሳሌ፡- የደብተሮችን፣ የእስክርቢቶችን፣ የትንንሽ ድንጋዮችን፣ወዘተ) የትኞቹ ከባድ፣ የትኞቹ ቀላል እንደሆኑ ለመምህራችሁ አስረዱ፡፡
3. በቡድን 100 ግራም አሸዋ እየመዘናችሁ በወረቀት በመጠቅለል አዘጋጁ (12 ጥቅል ያህል) እንደሁም 500 ግራም አሸዋ እየመዘናችሁ በላስቲክ በመቋጠር አዘጋጁ (4 ላስቲክ ያህል)፡፡ ሚዛኑን ተጠቀማችሁ፡፡

   ሀ. ስንት በወረቀት የተጠቀለሉ 100 ግራም አሸዋ 500 ግራም ይመዝናሉ?

   ለ. ስንት በወረቀት የተጠቀለሉ 100 ግራም አሸዋ 1 ኪ.ግራም ይመዝናሉ?

   ሐ. ስንት በላስቲክ የተቋጠሩ 500 ግራም አሸዋ 1 ኪ.ግራም ይመዝናሉ?

## ተግባር 2.10

የተለያዩ እቃዎች ክብደት በኪሎ ግራም እና በኩንታል ምድቦች እንዴት እንደሚገለፅ ወላጆቻችሁን ወይም በምትኖሩበት አካባቢ የሚገኙ ሌሎች ሰዎችን ጠይቁና ተረዱ፡፡ የተረዳችሁትን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

የተለያዩ የክብደት መለኪያ ምድቦች እንዳሉ ተምራችኋል፡፡ የተወሰኑ የክብደት መለኪያ ምድቦች ዝምድና ከዚህ በታች ባለው ማስታወሻ ቀርበዋል፡፡

**ማስታወሻ፡-** 1 ኪ.ግ = 1000 ግ     1 ኩንታል = 100 ኪ.ግ

**ምሳሌ 2.7**

1. የሚከተሉትን ከኪ.ግ ወደ ግራም ለውጡ፡፡

   ሀ. 5 ኪ.ግ     ለ. 7 ኪ.ግ ከ500 ግ

2. የሚከተሉትን ከኩንታል ወደ ኪ.ግራም ለውጡ፡፡

   ሀ. 2 ኩንታል     ለ. 3 ኩንታል ከ35 ኪ.ግራም

**መፍትሔ**

1. ሀ/ 5 ኪ.ግ = 5 × 1000 ግ = 5000 ግ

   ለ/ 7 ኪ.ግ ከ500 ግ = 7 ኪ.ግ + 500 ግ
   = 7 × 1000 ግ + 500 ግ
   = 7000 ግ + 500 ግ = 7500 ግ

2. ሀ/ 2 ኩንታል = 2 × 100 ኪ.ግ = 200 ኪ.ግ

   ለ/ 3 ኩንታል ከ35 ኪ.ግ = 3 ኩንታል + 35 ኪ.ግ
   = 3 × 100 ኪ.ግ + 35 ኪ.ግ
   = 300 ኪ.ግ + 35 ኪ.ግ = 335 ኪ.ግ

## መልመጃ ቀ

1. የሚከተሉትን ከኪ.ግራም ወደ ግራም ለውጡ፡፡

   ሀ. 3 ኪ.ግ ለ. 8 ኪ.ግ ሐ. 9 ኪ.ግ ከ300 ግ

2. የሚከተሉትን ከኩንታል ወደ ኪ.ግራም ለውጡ፡፡

   ሀ. 4 ኩንታል ለ. 12 ኩንታል ሐ. 10 ኩንታል ከ50 ኪ.ግ

3. የተማሪ ዓለሙ ክብደት 35 ኪ.ግራም ነው፡፡ የሳራ ክብደት ከዓለሙ ክብደት በ2 ኪ.ግራም ይበልጣል፡፡ የሳራ ክብደት ስንት ነው?

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

- ርዝመታቸው አነስተኛ የሆኑ ነገሮችን ርዝመት ለመለካት ሚሊ ሜትር እንጠቀማለን፡፡
- ርዝመታቸው ከፍ ያሉ ነገሮችን ርዝመትና የተለያዩ ቦታዎችን ርቀት ለመለካት ሳ.ሜ፣ ሜትርና ኪ.ሜትር እንጠቀማለን፡፡
- በርዝመት መለኪያ ምድቦች መካከል ያለ ዝምድና

  10 ሚ.ሜ = 1ሳ.ሜ

  100 ሳ.ሜ = 1 ሜ

  1000 ሜ = 1 ኪ.ሜ
- አንድ የፈሳሽ መያዣ እቃ ሊይዘው የሚችለው ከፍተኛ የፈሳሽ መጠን የእቃው ይዘት ይባላል፡፡

- ሚሊ ሊትር አነስተኛ የፈሳሽ መጠንን ለመለካት የምንጠቀምበት ምድብ ነው፡፡
- ሊትር የፈሳሽ መጠንን ለመለካት የምንጠቀምበት ሌላው ምድብ ነው፡፡
- በሊትርና በሚሊ ሊትር መካከል ያለው ዝምድና

  1000 ሚ.ሊ = 1 ሊትር
- ሚዛን የአንድን እቃ ክብደት ለመለካት የምንጠቀምበት መሳሪያ ነው፡፡
- ግራም፣ ኪሎ ግራም እና ኩንታል የአንድን ነገር ክብደት ለመለካት የምንጠቀምባቸው ምድቦች ናቸው፡፡
- በክብደት መለኪያ ምድቦች መካከል ያለ ዝምድና

  1000 ግ = 1ኪ.ግ

  100 ኪ.ግ = 1ኩንታል

# የማጠቃለያ መልመጃ

1. ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች ትክክለኛውን የርዝመት መለኪያ ምድቦች ዝምድና በመጠቀም አስልታችሁ የተሰጡትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ፡፡

   ሀ. 15 ሳ.ሜ = ________ ሚ.ሜ

   ለ. 26 ሜ = ________ ሳ.ሜ

   ሐ. 33ሜ ከ64 ሳ.ሜ = ________ ሳ.ሜ

   መ. 8 ኪ.ሜ = ________ ሜ

   ሠ. 9 ኪ.ሜ ከ75 ሜ = ________ ሜ

2. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች የ<፣ > ወይም = ምልክትን በመጠቀም ዓ.ነገሮችን እውነት አድርጉ፡፡

   ሀ. 25 ሜ + 25 ሳ.ሜ __________ 50 ሳ.ሜ

   ለ. 42 ሜ ከ65 ሳ.ሜ - 75 ሳ.ሜ __________ 42 ሜ

   ሐ. 5 ኪ.ሜ __________ 5000 ሜ

3. የሚከተሉትን ወደ ሚሊ ሊትር ቀይሩ፡፡

   ሀ. 6 ሊትር  ለ. 8 ሊትር  ሐ. 9 ሊትር

4. የሚከተሉትን ወደ ግራም ቀይሩ፡፡

   ሀ. 4 ኪ.ግ  ለ. 6 ኪ.ግ  ሐ. 7 ኪ.ግ

5. የሚከተሉትን ወደ ኪ.ግራም ቀይሩ፡፡

   ሀ. 5 ኩንታል  ለ. 6 ኩንታል  ሐ. 10 ኩንታል

6. አቶ ሰይፉ 25 ሜ ጥቅል ሽቦ አላቸው፡፡ አቶ ሰይፉ የዶሮ ቤት ለማጠር 15 ሜ ሽቦ ተጠቅመዋል፡፡ ያልተጠቀሙበት ሽቦ ስንት ሜትር ነው?

7. አንድ ጠርሙስ በውስጡ ምንም ውሃ ሳይኖረው ክብደቱ 305 ግራም ነው፡፡ ጠርሙሱ በውሃ ሲሞላ 550 ግራም ቢመዝን የውሃው ክብደት ስንት ነው?



ጠርሙስ

8. 15 ኪ.ግ ከ650 ግ ወደ ዝቅተኛው መስፈሪያ ምድብ ለውጡ፡፡

9. የአንድ ግራም ወርቅ ዋጋ 800 ብር ቢሆን 2.025 ግራም ወርቅ ዋጋ ስንት ይሆናል?

10. የተማሪ አቤል ክብደት 30 ኪ.ግራም ነው፡፡ የእህቱ የቤዛ ክብደት ከአቤል ክብደት በ 5 ኪ.ግራም ያንሳል፡፡ የቤዛ ክብደት ስንት ኪ.ግራም ነው?

# ምዕራፍ ሦስት

# ክፍልፋዮች

**የመማር ማስተማር ውጤቶች፡-**

- የሙሉ ነገር 3 ክፍልፋዮች እውቀታቸውን መጠቀም።
- ከ $\frac{1}{2}$ እስከ $\frac{1}{10}$ ያሉትን አሀዳዊ ክፍልፋዮች መለየት።
- አንድ ሙሉ ነገር ለሁለትና ለአራት በማካፈል ክፍልፋዮች መመስረት።
- ቀላል ክፍልፋዮችን ማወዳደር።

## 3.1 የሙሉ ነገር 3 ክፍልፋዮች ክለሳ

በሁለተኛ ክፍል የሂሣብ ትምህርታችሁ ስለተወሰኑ ክፍልፋዮች ስያሜ (አጠራር) ተምራችኋል። ለምሳሌ፡- ስለግማሽ፣ ስለአንድ ሦስተኛ እና ሁለት ሦስተኛ። በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ደግሞ አንድ ሦስተኛና ሁለት ሦስተኛን በስዕል እንዴት እንደሚገለፁ ትማራላችሁ።

### ተግባር 3.1

**ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚሰራ።**

1. ከዚህ በታች የቀረቡትን ምስሎች ተመልከቱና ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።




ሀ. ክቡ ከስንት እኩል ቦታ ተከፍሏል?
ለ. ሬክታንግሉ ከስንት እኩል ቦታ ተከፍሏል?
ሐ. ከሬክታንግሉ ያልተቀቡ ክፍሎች ስንት ናቸው?

## ማስታወሻ

- በተግባ 3.1 የተመለከተው ጎነ-ሦስት ከሦስት እኩል ቦታ ተከፍሎ አንዱ ክፍል ተቀብቷል፡፡ የተቀባው ከሦስቱ ክፍሎች አንዱ ነው፡፡ ይህ ክፍል የዋናው ጎነ ሦስት ምስል አንድ ሦስተኛ አካል ተብሎ ይጠራል፡፡
- ከሦስቱ ክፍሎች ውስጥ ያልተቀቡት ሁለት ናቸው፡፡ ይህም የዋናው ጎነ ሦስት ምስል ሁለት-ሦስተኛ ተብሎ ይጠራል፡፡
- አንድ ሙሉ ነገር እኩል በሆኑ ክፍሎች ከተከፋፈለ እያንዳንዱ ክፍል ክፍልፋይ ይባላል፡፡
- አሀዛዊ አፃፃፍ፡- አንድ-ሦስተኛ በአሀዝ $\frac{1}{3}$ ተብሎ ይፃፋል፡፡

  ሁለት-ሦስተኛ በአሀዝ $\frac{2}{3}$ ተብሎ ይፃፋል፡፡
- አሀዛዊ አፃፃፍ $\frac{2}{3}$ የሚከተሉት ስያሜዎችና ትርጉሞች አሉት፡- 2 የክፍልፋዩ ላዕል ይባላል፡፡ ይህም የወሰደውን የክፍልፋይ መጠን ይገልፃል፡፡ 3 የክፍልፋዩ ታህት ይባላል፡፡ ይህም አንድ ሙሉ ነገር ከስንት እኩል ቦታ እንደተከፋፈለ ይገልፃል፡፡ አግድም ሰረዙ (–) የክፍልፋይ ሰረዝ ይባላል፡፡

### መልመጃ ሀ

1. የሚከተለው ምስል ከሦስት እኩል ቦታዎች የተከፈለ ነው፡፡ ምስሉን መሠረት በማድረግ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡
   ሀ. የተቀባውን የምስሉን ክፍል በአሀዝ (በክፍልፋይ) ግለፁ፡፡
   ለ. ያልተቀባውን የምስሉን ክፍል በክፍልፋይ ግለፁ፡፡



ሬክታንግል

2. ስንት $\frac{1}{3}$ አንድ ሙሉ ነገር ይሆናል;

## 3.2 ከ $\frac{1}{2}$ እስከ $\frac{1}{10}$ ያሉ አሀዳዊ ክፍልፋዮች

ምስሎችን በመጠቀም የተወሰኑ ክፍልፋዮች እንዴት እንደሚመሰረቱ ቀደም ሲል የተማራችሁትን አስታውሱ፡፡ ምስል በመጠቀም $\frac{1}{3}$ እንዴት እንደሚገለፅ ለጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

## ተግባር 3.2

**በተናጠል የሚሰራ።**

ከዚህ በታች በቀረበው የመጀመሪያ ምሳሌ መሠረት ሌሎቹን ጥያቄዎች ስሩ።

ሀ.



የክፋዮች ብዛት = 2
የተቀባው ክፍል ብዛት = 1
የተቀባው በክፍልፋይ ሲገለፅ = አንድ-ሁለተኛ

ለ.



የክፋዮች ብዛት = ________________
የተቀባው ክፍል ብዛት = ________________
የተቀባው በክፍልፋይ ሲገለፅ = ________________

ሐ.



የክፋዮች ብዛት = ________________
የተቀባው ክፍል ብዛት = ________________
የተቀባው በክፍልፋይ ሲገለፅ = ________________

መ.



የክፋዮች ብዛት = ________________
የተቀባው ክፍል ብዛት = ________________
የተቀባው በክፍልፋይ ሲገለፅ = ________________

ሠ.



የክፋዮች ብዛት = ________________
የተቀባው ክፍል ብዛት = ________________
የተቀባው በክፍልፋይ ሲገለፅ= ________________

**ማስታወሻ**
ላዕላቸው 1 የሆኑ ክፍልፋዮች ሁሉ አሀዳዊ ክፍልፋዮች ይባላሉ።

## መልመጃ ለ

ከዚህ በላይ ባያችሁት አሰራር መሠረት ምስሎችን በመሳል እና እኩል ቦታ በመከፋፈል አንድ-ስድስተኛን፣ አንድ-ስምንተኛን እና አንድ-ዘጠነኛን አመልክቱ።

### ከ $\frac{1}{2}$ እስከ $\frac{1}{10}$ ያሉ አሀዳዊ ክፍልፋዮችን በአሀዝ መግለፅ

ከ$\frac{1}{2}$ እስከ $\frac{1}{10}$ ያሉ አሀዳዊ ክፍልፋዮችን በምስሎች አማካኝነት መግለፅ እንደሚቻል ከዚህ በፊት ተምራችኋል። እነኝህን አሀዳዊ ክፍልፋዮች በአሀዝ መግለፅ ከዚህ ቀጥሎ ትማራላችሁ።

## ተግባር 3.3

**ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚሰራ፡፡**

1. አሀዳዊ ክፍልፋዮች የሚባሉት ምን አይነት ክፍልፋዮች ናቸው?
2. ከዚህ በፊት የተማራችሁትን በማስታወስ ሁለት አሀዳዊ ክፍልፋዮችን በአሀዝ ፃፉ፡፡
3. አሰገደች አንዱን ሙሉ ዳቦ ከሦስት እኩል በመክፈል ለሦስት ልጆች እኩል አከፋፈለቻቸው፡፡ የአንደኛውን ልጅ ድርሻ በክፍልፋይ ፃፉ፡፡

ምስሎችን በመጠቀም አሀዳዊ ክፍልፋዮች በቃላት እንዴት እንደሚገለጹ ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ እነኚህ አሀዳዊ ክፍልፋዮች በአሀዝ እንዴት እንደሚፃፉ ትማራላችሁ፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡትን ምስሎች ተመልከቱ፡፡ የተቀቡት ክፍሎች (ክፍልፋዮች) በአሀዝ ተገልፀዋል፡፡

$\frac{1}{2}$

$\frac{1}{3}$

$\frac{1}{4}$

$\frac{1}{5}$



### ማስታወሻ

- አንድ-ሁለተኛ በአሀዝ $\frac{1}{2}$ ተብሎ ይፃፋል
- አንድ-ሦስተኛ በአሀዝ $\frac{1}{3}$ ተብሎ ይፃፋል
- አንድ-አራተኛ በአሀዝ $\frac{1}{4}$ ተብሎ ይፃፋል
- አንድ-አምስተኛ በአሀዝ $\frac{1}{5}$ ተብሎ ይፃፋል
- አንድ-ስድስተኛ በአሀዝ $\frac{1}{6}$ ተብሎ ይፃፋል

## መልመጃ ሐ

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ክፍልፋዮች በተሰጠው ክፍት ቦታ በአሀዝ ፃፉ፡፡

   ሀ. አንድ-ሰባተኛ = ____________ ሐ. አንድ-ዘጠነኛ = ____________

   ለ. አንድ-ስምንተኛ= ____________ መ. አንድ-አስረኛ = ____________

2. ምስሎችን በመጠቀም አሀዳዊ ክፍልፋዮችን $\frac{1}{6}$፣ $\frac{1}{7}$፣ $\frac{1}{8}$፣ $\frac{1}{9}$ እና $\frac{1}{10}$ አመልክቱ፡፡

**ማስታወሻ**

**የተወሰኑ አሀዳዊ ክፍልፋዮች የተለመደ አጠራር አላቸው እነሱም፡-**

- $\frac{1}{2}$ ግማሽ ይባላል፡፡
- $\frac{1}{3}$ ሲሶ ይባላል፡፡
- $\frac{1}{4}$ ሩብ ይባላል፡፡
- $\frac{1}{5}$ አምሾ ይባላል፡፡
- $\frac{1}{10}$ አስራት ይባላል፡፡

## 3.3 የሙሉ ቁጥሮች ግማሽ እና ሩብ

### የ2 ብዜቶችን ግማሽ መለየት

ግማሽ ወይም $\frac{1}{2}$ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተምራችኋል፡፡ የ2 ብዜቶችን ግማሽ እንዴት መፈለግ እንደሚቻል ከዚህ በታች ያለውን አሰራር ተመልከቱ፡፡



ጠቅላላ የኳሶች ብዛት= 2

እኩል ኳሶችን የያዙ ክፍሎች ብዛት = 2

በአንዱ ክፍል ውስጥ ያለ ኳስ ብዛት = 1 = 2÷2

ይህ ማለት የ2 ግማሽ 1 ነው ማለት ነው፡፡



ጠቅላላ የጠጠሮች ብዛት = 4

እኩል ጠጠሮችን የያዙ ክፍሎች ብዛት = 2

በአንዱ ክፍል ውስጥ ያሉ ጠጠሮች ብዛት = 2 = 4÷2

ይህ ማለት የ4 ግማሽ 2 ነው ማለት ነው፡፡



ጠቅላላ የሙዞች ብዛት = 12

እኩል ሙዞችን የያዙ ክፍሎች ብዛት = 2

በአንዱ ክፍል ውስጥ ያሉ ሙዞች = 6 =12÷2

ይህ ማለት የ12 ግማሽ 6 ነው ማለት ነው፡፡

**ማስታወሻ**

**የ2 ብዜት የሆነን ሙሉ ቁጥር ለ2 በማካፈል የሚገኘው ውጤት የሙሉ ቁጥሩ ግማሽ ነው፡፡**

**ምሳሌ 3.1** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ግማሽ ፈልጉ፡

ሀ. 16 ለ. 24

**መፍትሔ፡-**

ሀ. የ16 ግማሽ =16 ÷ 2 = 8

ለ. የ24 ግማሽ = 24 ÷ 2 = 12

## መልመጃ መ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ግማሽ ፈልጉ፡፡

   ሀ. 14 ለ. 18 ሐ. 28 መ. 36
2. ዓለሚቱ 3 ኪሎ ግራም ብርቱካን ገዛች፡፡ የአንዱ ኪሎ ግራም ብርቱካን ዋጋ 8 ብር ነው፡፡ በጠቅላላ 3 ኪሎ ግራም ብርቱካን ለመግዛት ካወጣችው ብር ውስጥ ግማሹ ስንት ነው?
3. የትህትና ቁመት 1ሜ ከ40 ሳ.ሜ ነው፡፡ የህፃን ትግስቱ ቁመት የትህትናን ቁመት ግማሽ ያህል ነው፡፡ የትግስቱ ቁመት ስንት ሳ.ሜ ነው?

### የ4 ብዜቶችን ሩብ መለየት

ሩብ ማለት $\frac{1}{4}$ እንደሆነ ቀደም ሲል ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ የአራት ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን ሩቦች በቀላሉ እንዴት እንደሚፈለጉ ትማራላችሁ፡፡



ጠቅላላ የጠጠሮች ብዛት = 8

እኩል ጠጠሮችን የያዙ ክፍሎች ብዛት = 4

በአንዱ ክፍል ውስጥ ያሉ ጠጠሮች ብዛት = 2 = 8÷4

ይህ ማለት የ 8 ሩብ 2 ነው ማለት ነው፡፡



ጠቅላላ የቅጠሎች ብዛት = 12

እኩል ቅጠሎችን የያዙ ክፍሎች ብዛት = 4

በአንዱ ክፍል ውስጥ ያሉ ቅጠሎች ብዛት = 3 = 12÷4

ይህ ማለት የ12 ሩብ 3 ነው ማለት ነው፡፡

> **ማስታወሻ**
>
> አንድ የ 4 ብዜት የሆነን ቁጥር ለ 4 በማካፈል የሚገኝ ውጤት የቁጥሩ ሩብ ይባላል፡፡

**ምሳሌ 3.2** የሚከተሉትን ቁጥሮች ሩብ ፈልጉ፡፡

ሀ. 16 ለ. 24

**መፍትሔ**

ሀ. የ16 ሩብ = 16 ÷ 4 = 4

ለ. የ24 ሩብ = 24 ÷ 4= 6

**መልመጃ ሠ**

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ሩብ ፈልጉ፡፡

   ሀ. 28 ለ. 32 ሐ. 44

2. አንድ መምህር 48 ደብተሮችን ለ4 ጎበዝ ተማሪዎች እኩል ቢያከፋፍል፣ የአንዱ ተማሪ ድርሻ ስንት ደብተሮች ይሆናል?



ደብተሮች

3. ለይኩን 76 የዛፍ ችግኞችን በአራት የችግኝ መደቦች እኩል ከፍሎ ተክሏቸዋል፡፡ በአንዱ የችግኝ መደብ የተተከሉት ችግኞች ስንት ናቸው?



ችግኞች

## 3.4 ቀላል ክፍልፋዮችን ማወዳደር

ከ $\frac{1}{2}$ እስከ $\frac{1}{10}$ ያሉ የአንድ ክፍልፋዮችን በምስል መግለፅ እንደሚቻል ተምራችኋል፡፡ ቀጥሎ ምስሎችን ተጠቅማችሁ የተጠቀሱትን የአንድ ክፍልፋዮች ታወዳድራላችሁ፡፡

## ተግባር 3.4

**በቡድን የሚሠራ**

ከዚህ በታች ያሉ ምስሎች እያንዳንዳቸው እኩል በሆኑ ክፍሎች ተከፍለዋል፡፡ የተቀቡትን ክፍሎች ተመልከቱና የተጠቀሱትን አሀዳዊ ክፍልፋዮች፡- የ $>$ ወይም $<$ ምልክት በመጠቀም አወዳድሩ፡፡

ሀ. $\frac{1}{2}$ ______ $\frac{1}{3}$    $\frac{1}{2}$ 

ለ. $\frac{1}{3}$ ______ $\frac{1}{4}$    $\frac{1}{3}$ 

ሐ. $\frac{1}{5}$ ______ $\frac{1}{4}$    $\frac{1}{4}$ 

መ. $\frac{1}{5}$ ______ $\frac{1}{3}$    $\frac{1}{5}$ 

ከእያንዳንዱ ምስል የተቀቡ ክፍሎችን ተመልክታችሁ ክፍልፋዮችን በቀላሉ አወዳደራችሁ? በጣም ጥሩ፡፡ ሌሎች አሀዳዊ ክፍልፋዮችን ማለትም $\frac{1}{6}$፣ $\frac{1}{7}$፣ $\frac{1}{8}$፣ $\frac{1}{9}$ እና $\frac{1}{10}$ በተመሳሳይ መንገድ አወዳድሩ፡፡

## መልመጃ ረ

በተግባር 3.4 እንደተመለከተው ምስሎችን በመደርደርና በማጥቆር

1. ክፍሎችን በማጥቆር $\frac{1}{6}$፣ $\frac{1}{7}$፣ $\frac{1}{8}$፣ $\frac{1}{9}$ እና $\frac{1}{10}$ ን አመልክቱ፡፡
2. የ $>$ ወይም $<$ ምልክት በመጠቀም የሚከተሉትን አወዳድሩ፡፡

   ሀ. $\frac{1}{6}$ ______ $\frac{1}{7}$

   ለ. $\frac{1}{7}$ ______ $\frac{1}{8}$

   ሐ. $\frac{1}{8}$ ______ $\frac{1}{9}$

   መ. $\frac{1}{10}$ ______ $\frac{1}{9}$

   ሠ. $\frac{1}{8}$ ______ $\frac{1}{6}$

# የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ

- አንድ ሙሉ ነገር ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ እኩል ክፍሎች ሲከፋፈል ክፍልፋይ ይባላል፡፡
- “ሀ” እና “ለ” ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑና ለ ከዜሮ የተለየ ቁጥር ቢሆን በክፍልፋይ $\frac{ሀ}{ለ}$ አፃፃፍ የሚከተሉት ስያሜዎችና ትርጉሞች ተሰጥተዋል፡፡ “ሀ” የክፍልፋዩ ላዕል ይባላል፣ አግድም ሰረዙ “–” የክፍልፋይ ሰረዝ ይባላል፡፡ እንዲሁም “ለ” የክፍልፋዩ ታህት ይባላል፡፡

  “ሀ” - የክፍልፋዩን መጠን ይገልፃል፣

  “ለ” - አንድ ሙሉ ነገር ከስንት እኩል ቦታ እንደተከፋፈለ ይገልፃል፡፡
- ላዕላቸው 1 የሆኑ ክፍልፋዮች ሁሉ አህዳዊ ክፍልፋዮች ይባላሉ፡፡
- በተለምዷዊ አጠራር ግማሽ ማለት $\frac{1}{2}$፣ ሲሶ ማለት $\frac{1}{3}$፣ ሩብ ማለት $\frac{1}{4}$፣ አምሽ ማለት $\frac{1}{5}$ እና አስራት ማለት $\frac{1}{10}$ እንደሆኑ ተገንዘቡ፡፡
- የ2 ብዜት የሆነን ሙሉ ቁጥር ለ2 በማካፈል (ሁለት እኩል ቦታ መክፈል) የሚገኘው ውጤት የሙሉ ቁጥሩ ግማሽ ይባላል፡፡
- አንድ የ”4” ብዜት የሆነን ሙሉ ቁጥር ለ “4” በማካፈል (አራት እኩል ቦታ በመክፈል) የሚገኝ ውጤት የሙሉ ቁጥሩ “ሩብ” ይባላል፡፡
- ታህቱ ትንሽ የሆነ አህዳዊ ክፍልፋይ ታህቱ ትልቅ ከሆነ አህዳዊ ክፍልፋይ ይበልጣል፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. አንድ ነጭ ወረቀት ከሦስት እኩል ቦታ ክፈሉ፡፡ የላይኛውን ክፍል አረንጓዴ ቀለም ቀቡ፣ መካከለኛውን ክፍል ቢጫ ቀለም ቀቡ፣ የታችኛውን ክፍል ቀይ ቀለም ቀቡ፡፡




   ሀ. ቀይ የተቀባው ክፍል በክፍልፋይ ሲፃፍ =____________

   ለ. ብጫ የተቀባው ክፍል በክፍልፋይ ሲፃፍ =____________

   ሐ. አረንጓዴና ብጫ የተቀቡት ክፍሎች በክፍልፋይ ሲፃፍ = ____________

2. አሰገደች ለምሳ ከተሰጣት አንድ ሙሉ እንጀራ $\frac{2}{3}$ ኛውን በላች። አሰገደች ያልበላችውን እንጀራ በክፍልፋይ ግለፁ።
3. አዜብ በልብስ መሸጫ ሱቋ 18 ሱሪዎች ነበራት። የበዓል ሰሞን ግማሾቹን ብትሸጥ ያልተሸጡት ሱሪዎች ስንት ናቸው?
4. በ3ኛ ክፍል ውስጥ 56 ተማሪዎች አሉ። ከክፍሉ ጠቅላላ ተማሪዎች ሩብ የሚሆኑት የተሰጣቸውን የሂሳብ ፈተና ደፍነዋል። ፈተናውን የደፈኑ ተማሪዎች ቁጥር ስንት ነው?



ተማሪዎች

5. 6 ብርቱካኖች ለአራት ልጆች እኩል ቢካፈሉ እያንዳንዱ ልጅ ምን ያህል ብርቱካን ይደርሰዋል?
6. የሚከተሉትን የተለመዱ የአሃዳዊ ክፍልፋዮች በምሳሌው መሰረት ስያሜያቸውን ስጡ።

| ክፍልፋይ | ስያሜ |
|---|---|
| $\frac{1}{2}$ | ግማሽ |
| $\frac{1}{3}$ | ______ |
| ______ | ሩብ |
| $\frac{1}{5}$ | ______ |
| $\frac{1}{10}$ | ______ |

**7. 1 ኪሎ ግራም ስኳር ለ5 ሰዎች እኩል ቢካፈል እያንዳንዱ ሰው ምን ያህል ይደርሰዋል?**

**8. የሚከተሉትን በአሃዝ ግለጽ፡፡**

ሀ) አንድ አስራ ሶስተኛ

ለ) አምስት ዘጠነኛ

ሐ) አስር አስራ ሰባተኛ

**9. የሚከተሉትን በቃላት ግለጽ፡፡**

ሀ) $\frac{36}{126}$

ሐ) $\frac{294}{218}$

ለ) $\frac{112}{157}$

መ) $\frac{617}{266}$

**10. ለሚከተሉት ምስሎች የተቀባውን እና ያልተቀባውን የምስሉ ክፍሎች በአሃዝ ግለፁ፡፡**

ሀ)



የተቀባው ________

ያልተቀባው________

ለ)



የተቀባው ________

ያልተቀባው________

ሐ)



የተቀባው ________

ያልተቀባው________

# ምዕራፍ አራት

# እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ

**የመማር ማስተማር ውጤቶች፡-**

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር፡፡
- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ፡፡
- መደመር እና መቀነስ ስሌትን በመጠቀም የቃላት ፕሮብሌም መፍታት፡፡

## 4.1 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር በምዕራፍ አንድ ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ የ1000 ብዜቶችን በቃል መደመር ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 4.1

**በግል የሚሠራ**

1. እስከ 10,000 የሚደርሱ የ1000 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡
2. ትንሹ የ1000 ብዜት ሙሉ ቁጥር ስንት ነው?
3. የ1000 ብዜት የሆነ የ10,000 ቀዳማይ ሙሉ ቁጥር ስንት ነው?
4. የ1000 ብዜት የሆነ የ9000 ተከታይ ሙሉ ቁጥር ማነው?

**ማስታወሻ**

ሁለት ከ10,000 የሚያንሱ የ1000 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በቃል ስትደምሩ፡-
በሺ ቤት የሚገኙትን ሆሄዎች ደምራችሁ በቀኝ በኩል ሦስት ዜሮዎችን መፃፍ ነው፡፡

## ተግባር 4.2

ከ1,000 እስከ 10,000 ያሉ የ1000 ብዜቶችን የመደመር ሠንጠረዥ ሠርታችሁ ደምሩ፡፡

### ምሳሌ 4.1

1. 3000ን እና 4000ን በቃል ደምሩ፡፡

**መፍትሔ:-**

በ3000 ውስጥ በ ሺ ቤት የሚገኘው ሆሄ 3 ነው፡፡

በ4000 ውስጥ በ ሺ ቤት የሚገኘው ሆሄ 4 ነው፡፡

በ ሺ ቤት የሚገኙት ሆሄያት ድምር 7 በመሆኑ፡- የ3000 እና የ4000 ድምር 7000 ነው፡፡

2. ከዚህ በታች ያሉት የመደመር ግድግዳዎች ከመሠረቱ ጀምሮ የ1000 ብዜቶችን በቃል እየደመሩ ወደ ላይ መውጣትን ያሳያሉ፡፡







## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቃል ደምሩ፡፡

   ሀ. 1000 እና 3000　　　　ሐ. 3000 እና 4000

   ለ. 2000 እና 4000　　　　መ. 3000 እና 6000

2. የሚከተሉትን የመደመር ግድግዳዎች በቃል በመደመር ክፍት ቦታዎችን ሙሉ፡፡







3. ትምህርት ቤታችሁ በግቢው ውስጥ የሚገኘውን ሳር በመሸጥ 6000 ብር አገኘ፡፡ እንዲሁም የተወሰኑ ዛፎችን በመሸጥ 4000 ብር አገኘ፡፡ ትምህርት ቤታችሁ ሳርና ዛፎችን ሽጦ ያገኘው ብር በጠቅላላው ስንት ነው?

## ባለሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለሦስት ሆሄ ቁጥር ጋር መደመር

ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች እና ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ምን አይነት ቁጥሮች እንደሆኑ ከዚህ በፊት በነበራችሁ የሂሳብ ትምህርት ተገንዝባችኋል፡፡ ሁለቱን አይነት ቁጥሮች ወደ ጎንና ወደ ቁልቁል መደመር አሁን ትማራላችሁ፡፡

### ምሳሌ 4.2

1. የሚከተሉትን ወደ ጎን ደምሩ፡፡

   ሀ. 453 + 34      ለ. 609 + 92

2. የሚከተሉትን ቁልቁል ደምሩ፡፡

   ሀ. $\begin{array}{r} 269 \\ +\ \ 30 \\ \hline \end{array}$      ለ. $\begin{array}{r} 376 \\ +\ \ 29 \\ \hline \end{array}$

### መፍትሔ፡-

1. ሀ. 453 + 34 = (400 + 50 + 3 + 30 + 4)
   = 400 + 80 + 7
   = 487

   ለ. 609 + 92 = 600 + 9 + 90 + 2
   = 600+90+11
   = 600+90+10+1
   = 600+100+1
   = 701

2. ሀ. $\begin{array}{r} 269 \\ +\ \ 30 \\ \hline 299 \end{array}$

   ለ. $\begin{array}{r} 376 \\ +\ \ 29 \\ \hline 405 \end{array}$

አሰራሩ፡- ከአንድ ቤት በመጀመር ሆሄዎችን መደመር፡፡ በአለኝታ የሚደመሩ ከሆነ አለኝ የሚባለውን ቁጥር ከሚቀጥለው ትልቁ ቁጥር ቤት ሆሄዎች ጋር መደመር

## መልመጃ ለ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወደ ጎን ደምሩ፡፡

   ሀ. 243 + 30    ለ. 515 + 23    ሐ. 647 + 56    መ. 721 + 89

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ቁልቁል ደምሩ፡፡

   ሀ. $\begin{array}{r} 384 \\ +\ \ 13 \\ \hline \end{array}$    ለ. $\begin{array}{r} 469 \\ +\ \ 57 \\ \hline \end{array}$    ሐ. $\begin{array}{r} 606 \\ +\ \ 75 \\ \hline \end{array}$    መ. $\begin{array}{r} 720 \\ +\ \ 80 \\ \hline \end{array}$

3. የትንሹ ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥርና የትንሹ ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ድምር ስንት ነው፧

4. ትልቁ ባለሁለት ሆሄና ትልቁ ባለሦስት ሆሄ ሲደመሩ መልሱ ስንት ይሆናል?

5. የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ።

| ወ | ቀ | ወ+ቀ |
|---|---|---|
| 866 | 33 | |
| 424 | 92 | |
| 666 | 38 | |

## ባለሦስት ሆሄ ቁጥሮችን ከባለአራት ሆሄ ቁጥሮች ጋር መደመር

ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር መደመር ከዚህ በፊት በነበረው ርዕስ ተምራችኋል። ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለአራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር መደመር በተመሳሳይ መንገድ ይሰራል።

### ምሳሌ 4.3

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወደ ጎን ደምሩ።

   ሀ. 3456 + 243  ለ. 7845 + 694

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ቁልቁል ደምሩ።

   ሀ. $\begin{array}{r} 7243 \\ +\ 346 \\ \hline \end{array}$  ለ. $\begin{array}{r} 8576 \\ +\ 495 \\ \hline \end{array}$

### መፍትሔ

1. ሀ. 3456 + 243 = 3400 + 50 + 6 + 200 + 40 + 3
   = 3400 + 200 + 50 + 40 + 6 + 3
   = 3600 + 90 + 9
   = 3699

   ለ. 7845 + 694 = 7800 + 40 + 5 + 600 + 90 + 4
   = 7800 + 600 + 40 + 90 + 9
   = 7800 + 600 + 100 + 30 + 9
   = 8500 + 30 + 9
   = 8539

2. ሀ. $\begin{array}{r} 7243 \\ +346 \\ \hline 7589 \end{array}$

   ቁልቁል የመደመር አሰራር፡- ሆሄዎችን በቤት በቤታቸው ከአንድ ቤት በመጀመር መደመር። በአለኝታ የሚደመሩ ከሆነ አለኝ የተባለውን ሆሄ ከሚቀጥለው ትልቅ የቁጥር ቤት ሆሄዎች ጋር መደመር።

   ለ. $\begin{array}{r} 8576 \\ +\ 495 \\ \hline 9071 \end{array}$

# መልመጃ ሐ

1. የሚከተሉትን ወደ ጎን ደምሩ።

ሀ. 4296 + 204　　ለ. 6789 + 210　　ሐ. 8476 + 624　　መ. 8499 + 873

2. የሚከተሉትን ቁልቁል ደምሩ።

ሀ. $\begin{array}{r} 4836 \\ +\ 234 \\ \hline \end{array}$　　ለ. $\begin{array}{r} 8660 \\ +\ 712 \\ \hline \end{array}$　　ሐ. $\begin{array}{r} 8099 \\ +\ 736 \\ \hline \end{array}$　　መ. $\begin{array}{r} 9483 \\ +\ 816 \\ \hline \end{array}$

3. የመጀመሪያውን የመደመር ግድግዳ ምሳሌ አድርጋችሁ የቀሩትን አሟሉ።

ሀ.

| | | |
|---|---|---|
| | 1415 | |
| 1011 | | 404 |
| 897 | 114 | 290 |

ለ.

| | | |
|---|---|---|
| | 2070 | |
| 1558 | | |
| | 458 | |

ሐ.

| | | |
|---|---|---|
| | 2745 | |
| | | 896 |
| | 394 | |

4. ሰንጠረዡን ሙሉ

| ሀ | ለ | ሀ + ለ |
|---|---|---|
| 4567 | 624 | |
| 864 | 4234 | |
| 7426 | 209 | |
| 8999 | 762 | |

## ድምራቸው እስከ 10,000 የሚደርሱ ባለ አራት ሆሄ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ቁጥሮች ጋር መደመር

ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር ያለ አለኝታ ስትደምሩ ቁጥሮችን በቤት በቤታቸው መደመር ተገቢ ነው። በአለኝታ የሚደመሩ ከሆነ ደግሞ፡- መጀመሪያ በአንድ ቤት ያሉትን ሆሄዎች መደመር። ቀጥሎ በ10 ቤት፣በ100 ቤት እና በ1000 ቤት ያሉ ሆሄዎች ይደመራሉ። በየደረጃው አለኝ የምንለውን በሚቀጥለው ትልቁ ቁጥር ቤት ካሉት ሆሄዎች ጋር መደመር።

**ምሳሌ 4.4** የሚከተሉትን ደምሩ።

ሀ. 3467 + 5202　　ለ. 4365 + 2946

**መፍትሔ፡-** መጀመሪያ ቁጥሮችን ቤታቸውን ጠብቆ ወደ ቁልቁል መደመር መቀየር፡- ቀጥሎ በየቤታቸው ሆሄዎችን መደመር።

ሀ. $\begin{array}{r} 3467 \\ +\ 5202 \\ \hline 8669 \end{array}$　　ለ. $\begin{array}{r} 4365 \\ +\ 2946 \\ \hline 7311 \end{array}$

## መልመጃ መ

1. የሚከተሉትን ደምሩ።

ሀ. $\begin{array}{r} 4353 \\ +\,3432 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 3117 \\ +\,3662 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 5203 \\ +\,4230 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 7623 \\ +\,2016 \\ \hline \end{array}$

ሠ. $\begin{array}{r} 4606 \\ +\,2584 \\ \hline \end{array}$ ረ. $\begin{array}{r} 1652 \\ +\,7788 \\ \hline \end{array}$ ሰ. $\begin{array}{r} 1323 \\ +\,8484 \\ \hline \end{array}$ ሸ. $\begin{array}{r} 6950 \\ +\,2269 \\ \hline \end{array}$

2. ሰንጠረዡን ሙሉ

| ሀ | ለ | ሀ+ለ |
|---|---|---|
| 6029 | 1999 | |
| 3892 | 4484 | |
| 2566 | 3563 | |
| 3534 | 6337 | |
| 3646 | 3555 | |

### የቃላት ፕሮብሌሞች

**ማስታወሻ**

የቃላት ፕሮብሌሞችን ለመፍታት ወይም መፍትሔ ለማግኘት የሚከተሉትን የአሰራር ደረጃዎች መከተል ይገባል።

1ኛ፡- ፕሮብሌሙን ደጋግሞ አንብቦ መረዳት።

2ኛ፡- የተሰጡትንና የሚፈለጉትን መለየት።

3ኛ፡- የሚፈለገውን ሰርቶ ማግኘትና መልሱን ማረጋገጥ።

**ምሳሌ 4.5**

አንድ አርሶ አደር ሁለት የእርሻ በሬዎችን በ8376 ብር ገዛ። ሁለት በጎችን ደግሞ በ1000 ብር ገዛ። ሁለቱን በሬዎችና ሁለቱን በጎች ለመግዛት በጠቅላላው ስንት ብር አወጣ?



በሬዎች



በጎች

**መፍትሔ፡-**

ሁለቱን በሬዎች ለመግዛት ያወጣው 8376 ብር ፤ ሁለቱን በጎች ለመግዛት ያወጣው 1000 ብር ነው። ሁለቱን በሬዎች ና ሁለቱን በጎች ለመግዛት በጠቅላላ ያወጣውን ብር ለማግኘት ሁለቱን ወጪዎች መደመር ይሆናል።

$$\begin{array}{r} 8376 \\ +\ 1000 \\ \hline 9376 \end{array}$$

ስለዚህ አርሶ አደሩ ያወጣው ጠቅላላ 9376 ብር ነው።

## መልመጃ ሠ

*ከዚህ በታች ለቀረቡት የቃላት ፕሮብሌሞች መፍትሔ ፈልጉ።*

1. በአንድ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ ወንድ ተማሪዎች 1225 ሲሆኑ ሴት ተማሪዎች ደግሞ 988 ናቸው። በጠቅላላ በት/ቤቱ የሚማሩ ተማሪዎች ስንት ናቸው?



ተማሪዎች

2. አንድ የሳሙና ፋብሪካ በመጀመሪያ ቀን 4809 ሳሙናዎችን አመረተ። በሁለተኛው ቀን ደግሞ 4927 ሳሙናዎችን አምረተ። ፋብሪካው በሁለቱ ቀናት ያመረታቸው ሳሙናዎች ስንት ናቸው?
3. የአንድን ት/ቤት አጥር ለማሰራት ከወላጆች 7545 ብር ተሰበሰበ፤ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ደግሞ 2125 ብር ተሰበሰበ። በጠቅላላ የተሰበሰበው ብር ስንት ነው?



የት/ቤት አጥር

4. አንድ የችግኝ ጣቢያ 6474 የተለያዩ ሀገር በቀል ችግኞቹን እና 2546 የተለያዩ የፍራፍሬ ችግኞችን ለአካባቢው ህብረተሰብ አካፋፈለ። ጣቢያው በጠቅላላ ያከፋፈላቸው ችግኞች ብዛት ስንት ናቸው?

5. አንድ የሻማ ፋብሪካ በመጀመሪያው ቀን 4944 ሻማዎችን አመረተ። በሁለተኛው ቀን ደግሞ 5000 ሻማዎችን አመረተ። ፋብሪካው በሁለቱ ቀናት ውስጥ ያመረታቸው ሻማዎች ብዛት ስንት ነው?

## 4.2 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

በሁለተኛ ክፍል ስለመቀነስ የተማራችሁትን መሠረት በማድረግ ከባለ 3 ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ 2 ሆሄ ቁጥር መቀነስ ከዚህ ቀጥሎ ትማራላችሁ።

### ተግባር 4.3

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን መፍትሔ ፈልጉ።

1. ካሣሁን ቤት ለመገንባት 350 ብሎኬቶችን ገዛ። ከዚህ ውስጥ 50 ብሎኬቶች ቢሰበሩበት ስንት ብሎክቶች ይቀሩታል?
2. በትምህርት ቤታችሁ 460 ተማሪዎች ተመዝግበዋል። ከተመዘገቡት ውስጥ 60 ተማሪዎች ቢቀሩ ስንት ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ?

**ማስታወሻ**

ከባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ያለብድር መቀነስ በሁለት መንገድ ሊሰራ ይችላል፦
አንደኛው አሰራር ቁጥሮችን ተንትኖ መቀነስ ሲሆን፤
ሁለተኛው አሰራር ቁጥሮቹን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል ፅፎ። ሆሄያትን በየቤታቸው መቀነስ ነው።

### ምሳሌ 4.6

የተሰጡትን ቁጥሮች በመተንተንና በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመፃፍ የሚከተሉትን ቀንሱ።

ሀ. 576 - 43 ለ. 648 - 35

**መፍትሔ፡** ቁጥሮችን በመተንተን መቀነስ

ሀ. $576 - 43 = 500 + 70 + 6 - (40 + 3)$
$= 500 + (70 - 40) + (6 - 3)$
$= 500 + 30 + 3 = 533$

ለ. $648 - 35 = 600 + 40 + 8 - (30+5)$
$= 600 + (40 - 30) + (8-5)$
$= 600 + 10 + 3 = 613$

ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመፃፍ ሲሰላ በሚከተለው መንገድ ይሆናል፡፡

ሀ. $\begin{array}{r} 576 \\ -\ 43 \\ \hline \end{array}$

- መጀመሪያ በአንድ ቤት ያሉትን መቀነስ 6 – 3 = 3 እና ውጤቱን "3" በአንድ ቤት ስር መፃፍ
- ቀጥሎ በአስር ቤት ያሉትን መቀነስ 7 – 4 = 3፡- ከዚያም ውጤቱን "3" በአስር ቤት ስር መፃፍ
- በመቶ ቤት ያለውን ሆሄ "5" እንዳለ በመቶ ቤት ስር መፃፍ፡፡

ስለዚህ $\begin{array}{r} 576 \\ -\ 43 \\ \hline 533 \end{array}$ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ለ. $\begin{array}{r} 648 \\ -\ 35 \\ \hline \end{array}$

- መጀመሪያ በአንድ ቤት ያሉትን መቀነስ 8 – 5 = 3 እና ውጤቱን "3" በአንድ ቤት ስር መፃፍ
- ቀጥሎ በአስር ቤት ያሉትን መቀነስ 4 – 3=1 እና ውጤቱን "1" በአስር ቤት ስር መፃፍ
- በመቶ ቤት ያለውን "6" እንዳለ በመቶ ቤት ስር መፃፍ፡፡

ስለዚህ $\begin{array}{r} 648 \\ -\ 35 \\ \hline 613 \end{array}$ ይሆናል፡፡

**ማስታወሻ**

ሀ፣ ለ እና መ ሙሉ ቁጥሮች ሆነው፣ ሀ > ለ ቢሆን

ሀ – ለ = መ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ "ሀ" ዋና፣ "ለ" ተቀናሽ እና "መ" ልዩነት ይባላል፡፡

## መልመጃ ረ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. 373 - 72 | ሐ. 467 - 67 | ሠ. 752 - 50 |
| ለ. 598 - 5 | መ. 674 - 74 | ረ. 877 - 75 |
| ሰ. $\begin{array}{r} 976 \\ -\ 55 \\ \hline \end{array}$ | ሸ. $\begin{array}{r} 879 \\ -\ 69 \\ \hline \end{array}$ | ቀ. $\begin{array}{r} 577 \\ -\ 52 \\ \hline \end{array}$ |

2. የማርታ እናት 185 ብር ይዘው ወደ ገበያ ሄዱ፡፡ በ75 ብር ለልጃቸው ጫማ ገዝተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡ የማርታ እናት ወደ ቤት ስንት ብር ይዘው ተመለሱ?

3. ሙስጠፋ ከገበያ 145 እንቁላሎችን ገዝቶ ሲመጣ 15 እንቁላሎች ተሰበሩበት። ሙስጠፋ ስንት እንቁላሎች ይቀሩታል?



እንቁላሎች

**ማስታወሻ**

**ከባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በመበደር መቀነስ ይቻላል። አሰራሩም በመተንተን እና በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመፃፍ ይሆናል።**

**ምሳሌ 4.7** የሚከተሉትን ቀንሱ።

ሀ. 674 - 89 ለ. $\begin{array}{r} 513 \\ -84 \\ \hline \end{array}$

**መፍትሔ:-**

ሀ. 674-89 = 600 + 70 + 4 – 80 - 9

= 600 + 60 – 80 + 14 – 9 → ከ70 ላይ አንድ 10 ወስዶ ከ4 ጋር መደመር

= 580 + 80 – 80 + 5 → ከ600 ላይ ሁለት 10 ወስዶ ከ60 ጋር መደመር።

= 580 + 0 + 5

= 585

ለ. $\begin{array}{r} 513 \\ -84 \\ \hline 429 \end{array}$ - በአንድ ቤት ያሉትን ሆሄያት ስናወዳድር 3 < 4። ስለዚህ ከ10 ቤት አንድ 10 ወስዶ ከ"3" ጋር መደመርና መቀነስ።

10 + 3 = 13 – 4 = 9። ውጤቱን "9" በአንድ ቤት ስር መፃፍ።

- ከዋናው በ10 ቤት የቀረን "0" ነው። ከመቶ ቤት አንድ አስር ወስዶ ከ "0" ጋር መደመርና መቀነስ:- 10 – 8 = 2። ውጤቱን "2" በአስር ቤት ስር መፃፍ።
- ከዋናው በመቶ ቤት የቀረውን "4"ን በመቶ ቤት ስር መፃፍ።

ስለዚህ $\begin{array}{r} 513 \\ -84 \\ \hline 429 \end{array}$ ይሆናል ማለት ነው።

## መልመጃ ሰ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 250 – 35 ሐ. 760 – 36 ሠ. 953 – 81

ለ. 480 – 66 መ. 844 – 73 ረ. 865 – 76 በ. $\begin{array}{r} 743 \\ -45 \\ \hline \end{array}$

ሰ. $\begin{array}{r} 670 \\ -68 \\ \hline \end{array}$ ሸ. $\begin{array}{r} 675 \\ -68 \\ \hline \end{array}$ ቀ. $\begin{array}{r} 435 \\ -46 \\ \hline \end{array}$

2. የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ፡፡

| ዋና | ተቀናሽ | ልዩነት |
|---|---|---|
| 572 | 67 | |
| 433 | 44 | |
| 525 | 28 | |
| 618 | 29 | |

## ባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ

ስለመቀነስ እስከ አሁን የተማራችሁትን በማስታወስ ባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ ትችላላችሁ፡፡ ቁጥሮቹን በቁጥር ቤት ዋጋቸው በመተንተን እና በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል ዕፎ በቤት በቤታቸው በመቀነስ ይሰራል፡፡ ባለ 3 ሆሄን ከባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ስትቀንሱ ውጤቱ ሁልጊዜ ሙሉ ቁጥር መሆን ይኖርበታል፡፡

### ተግባር 4.4

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ፡፡

1. የ376 እና የ175 ልዩነት ስንት ነው?
2. ከ426 ላይ 217 ብትቀንሱ መልሱ ስንት ይሆናል?
3. አቶ አለሙ 365 ብር፤ ወ/ሮ ትርንጎ ደግሞ 275 ብር አላቸው፡፡ የአቶ አለሙ ብር ከወ/ሮ ትርንጎ ብር በስንት ይበልጣል?

የሁለት ሙሉ ቁጥሮች **ልዩነት** የሚፈለገው ከትልቁ ቁጥር ላይ ተንሹን በመቀነስ ይሆናል፡፡ አንድ ሙሉ ቁጥር ከሌላው ሙሉ ቁጥር በስንት እንደሚበልጥ ወይም እንደሚያንስ የሚታወቀው ከትልቁ ላይ ትንሹን በመቀነስ ይሆናል፡፡

## ምሳሌ 4.8

1. የ465 እና የ218 ልዩነት ስንት ነው?
2. 527 ከ463 በስንት ይበልጣል?

## መፍትሔ:-

1. 465 - 218 = 400 + 60 + 5 - 200 -10 - 8
   = 400 - 200 + 60 - 10 + 5 - 8
   = 200 + 50 -10 + 15 - 8
   = 200 + 40 + 7
   = 247

   **ስለዚህ የ465 እና የ218 ልዩነት 247 ነው።**

2. $\begin{array}{r} 527 \\ -\underline{463} \\ 64 \end{array}$

   **ስለዚህ 527 ከ463 በ64 ይበልጣል።**

## መልመጃ ሸ

1. የሚከተሉትን አስሉ።

   ሀ. 227 – 127 ሐ. 597 – 389 ሠ. 706 – 288

   ለ. 465 – 213 መ. 646 – 478 ረ. 800 – 14

2. የሚከተሉትን አስሉ። መልሳችሁንም በመደመር አረጋግጡ።

   ምሳሌ:- ሀ. 347 – 152 = 195 ምክንያቱም 347 = 195 + 152

   ለ. 308 – 215 መ. 651 – 324

   ሐ. 423 – 309 ሠ. 744 – 555

3. የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ።

| ዋና | ተቀናሽ | ልዩነት |
|---|---|---|
| 542 | 425 | |
| 673 | | 342 |
| | 304 | 56 |

## ባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ

ባለ 3 ሆሄ ቁጥሮችን ከባለ 3 ሆሄ ቁጥሮች ላይ መቀነስ ከዚህ በፊት ተምራችኋል፡፡ ከባለ 4 ሆሄ ላይ ባለ 3 ሆሄን መቀነስ በተመሳሳይ መንገድ ይሰራል፡፡ መጀመሪያ ከዚህ በፊት የተማራችሁትን በማስታወስ የተግባር 4.4 ጥያቄዎችን ስሩ፡፡

### ተግባር 4.5

በግል የሚሰራ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

   ሀ. 7435 – 435 ለ. 6347 – 758

2. ዋናው 4573 እና ተቀናሹ 648 ቢሆን ልዩነቱ ስንት ይሆናል?

ባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ በመተንተንና ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመፃፍ ሆሄዎችን በቤት በቤታቸው በመቀነስ ይሰራል፡፡

### ምሳሌ 4.9

**የሚከተሉትን አስሉ፡፡**

ሀ. 5647 - 647 ለ. $\begin{array}{r} 7863 \\ -396 \\ \hline \end{array}$

**መፍትሔ:-**

ሀ. 5647 - 647 = 5000 + 647 - 647

= 5000

ለ. $\begin{array}{r} 7863 \\ -396 \\ \hline 7467 \end{array}$ መጀመሪያ በአንድ ቤት ያሉትን፣ ቀጥሎ በ10 ቤት ያሉትን፣ ከዚያም በመቶ ቤት ያሉትን መቀነስ፡፡ በየቤቱ ያሉ የላይኛው ቁጥር ሆሄዎች ታችኛው ካሉት የሚያንሱ ከሆነ እየተበደሩ የመቀነስ አሰራርን መከተል፡፡

### መልመጃ ቀ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

   ሀ. 1465 – 342 ለ. 3781 – 679 ሐ. 6477 – 829 መ. 7184 – 625

2. ከዚህ በታች የተሰጠውን ሰንጠረዥ አሟሉ፡፡

| ዋና | ተቀናሽ | ልዩነት |
|---|---|---|
| 8667 | 721 | |
| | 548 | 3311 |
| 5678 | | 4802 |

## ባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ

ባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ ተምራችኋል። ይህን እውቀታችሁን ተጠቅማችሁ ባለ 4 ሆሄ ቁጥሮችን ከባለ 4 ሆሄ ቁጥሮች ላይ መቀነስ በተመሳሳይ የአሰራር መንገዶች መስራት ትችላላችሁ።

### ተግባር 4.6

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግል ስሩ።

1. የ4356 እና የ3240 ልዩነት ስንት ነው?
2. ዋናው 5620፤ ልዩነቱ 3160 ቢሆኑ ተቀናሹ ስንት ይሆናል?

**ማስታወሻ**

ባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ የመቀነስ አሰራር ዘዴ፡- ቁጥሮችን በመተንተን እና በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመፃፍ በቤት በቤታቸው በመቀነስ ይሆናል። ባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ከባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ላይ ሲቀነስ ሁልጊዜ ልዩነቱ ሙሉ ቁጥር መሆን ይኖርበታል።

### ምሳሌ 4.10

የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 5643 – 3432

ለ. $\begin{array}{r} 7284 \\ -5165 \\ \hline \end{array}$

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 5643 - 3432 = 5643 – 3000 - 432
= 2643 – 432
= 2000 + 600 + 40 + 3 – 400 – 30 - 2
= 2000 + (600 - 400) + (40 - 30) + (3 - 2)
= 2000 + 200 + 10 + 1
= 2211

ስለዚህ 5643 — 3432 = 2211

ለ. $\begin{array}{r} 7284 \\ -5165 \\ \hline 2119 \end{array}$

- በአንድ ቤት ያሉት ሆሄያት ሲወዳደሩ፡- 4 < 5። ስለዚህ ከአስር ቤት አንድ አስር ተበድሮ ከ4 ጋር መደመርና “5”ን መቀነስ። 14 – 5 = 9 ልዩነቱን “9”ን በአንድ ቤት ስር መፃፍ።
- የቀሩትን በቤት በቤታቸው ቀንሶ ልዩነቱን ማስቀመጥ።

## መልመጃ በ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡
   ሀ. 1578 –1378　　ሐ. 5342 – 3259　　ሠ. 6352 – 6134
   ለ. 4657 – 2657　　መ. 7481– 4693　　ረ. 6500 – 5900
2. ዋናው 8645፣ ልዩነት 3678 ቢሆን ተቀናሹ ስንት ይሆናል?
3. ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ዋና | ተቀናሽ | ልዩነት |
|---|---|---|
| 4300 | 2300 | |
| 5471 | | 1646 |
| | 2435 | 2353 |
| 6678 | 3488 | |

## 4.3 መደመርና መቀነስ የያዙ የቃላት ጥያቄዎች

ባለፉት ሁለት ምዕራፎች እስከ 10,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች መደመርና መቀነስ ተምራችኋል፡፡ ይህን እውቀታችሁን መሠረት በማድረግ በመደመርና በመቀነስ ሊሰሩ የሚችሉ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትፈታላችሁ፡፡

### ተግባር 4.7

**በጋራ የሚሰሩ ጥያቄዎች**

1. አንድ ጎበዝ ተማሪ ከክፍሉ ተማሪዎች 1ኛ በመውጣቱ ት/ቤቱ 550 ብር፣ መምህራን ደግሞ 250 ብር ሸለሙት፡፡ ጎበዙ ተማሪ ከተሸለመው ብር በ200 ብር መፅሐፍ ቢገዛ ስንት ብር ይቀረዋል?
2. የአንድ ት/ቤት መዝናኛ ክበብ በጥቅምት ወር 3500 ብር፣ በህዳር ወር 3585 ብር ትርፍ አገኘ፡፡ ክበቡ ካገኘው ትርፍ ለተቸገሩ 12 ተማሪዎች በ1500 ብር ሸሚዞች ገዝቶ አከፋፈለ፡፡ ክበቡ በሁለቱ ወሮች ካገኘው ትርፍ የቀረው ብር ስንት ነው?

### ምሳሌ 4.11

በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በተደረገ የስፖርት ውድድር ትምህርት ቤቱ ከትኬት ሽያጭ 4685 ብር፣ ከለስላሳ ሽያጭ 1545 ብር ገቢ አገኘ፡፡ ትምህርት ቤቱ ከገቢው ውስጥ 3475 ብር ወጪ በማድረግ የተለያዩ ኳሶችን ገዛ፡፡ በውድድሩ ከተገኘው ቀሪ ብር ስንት ነው?

**መፍትሔ፡-** በውድድሩ ወቅት የተገኘ ጠቅላላ ብር 4685 + 1545 = 6230
ኳሶችን ለመግዛት ወጪ የተደረገ ብር = 3475
በውድድሩ ከተገኘው ቀሪ ብር = 6230 – 3475 = 2755

## መልመጃ ተ

1. በአንድ ት/ቤት የሚገኙ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ባለፈው አመት 2160 ችግኞችን ተክለዋል፡፡ በዚህ አመት ደግሞ 876 ችግኞችን ተከሉ፡፡ ከተተከሉ ችግኞች ውስጥ 125 አልፀደቁም፡፡ በሁለቱ አመታት ከተተከሉት ውስጥ የፀደቁት ችግኞች ስንት ናቸው?
2. አንድ የሱቅ ባለቤት ከሁለት የእንቁላል ነጋዴዎች እንቁላል ገዛ፡፡ ከመጀመሪያው 676፣ ከሁለተኛው 548 እንቁላሎችን ገዛ፡፡ ከተገዙት እንቁላሎች 108 የተበላሹ ሆነው ተገኙ፡፡ ያልተበላሹ እንቁላሎች ብዛት ስንት ነው?
3. አንድ በእንጨት ስራ የተደራጀ ማህበር ባለፈው አመት 3475 ብር፣ በዚህ አመት ደግሞ 4765 ብር ትርፍ አገኘ፡፡ ማህበሩ ከትርፉ ለአባላት 5420 ብር አካፋፈለ፡፡ ማህበሩ በሁለት አመት ስራው ለአባላት ያላከፋፈለው ትርፍ ስንት ብር ነው?
4. በአንድ ወረዳ ውስጥ በመንግስትና በግል ስራ የሚተዳደሩ 4560 ወንዶች እና 4500 ሴቶች አሉ፡፡ በግል ስራ የሚተዳደሩ 3540 ሰዎች ቢሆኑ፤ በመንግስት ስራ የሚተዳደሩ ስንት ሰዎች ይሆናሉ?
5. በመስከረምና ጥቅምት ወራት የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቦታዎች ለመጎብኘት 3456 ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ ገቡ፡፡ በህዳርና ታህሳስ ወራቶች ደግሞ 4635 ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል፡፡ ከቱሪስቶቹ መካከል 5150 ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የመጡ ናቸው፡፡ ከአፍሪካ ውጪ የመጡ ቱሪስቶች ስንት ናቸው?


አፄ ፋሲል ግንብ


አክሱም ሀውልት


የላሊበላ ህንፃ

### የመቀነስ ውጤትን በመደመር ማረጋገጥ

እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ ቀደም ባሉ ንዑስ ምዕራፎች ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ ከአንድ ሙሉ ቁጥር ላይ ሌላ ሙሉ ቁጥር በመቀነስ የሚገኘን መልስ በመደመር ማረጋገጥ ትማራላችሁ፡፡

## ተግባር 4.8

**ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚሰራ::**

1. ከበደ ወደ ሱቅ 370 ብር ይዞ ሄደ። ከበደ በ170 ብር አንድ ሱሪ ቢገዛ፤ ስንት ብር ይቀረዋል? የመልሳችሁን ትክክለኛነት አረጋግጡ።
2. ወርቅነሽ 250 ብር ይዛ ወደ መደብር ሄደች። ከመደብሩ በ65 ብር ዘይት፣ በ25 ብር ሸንኩርትና በ100 ብር ስጋ ብትገዛ፤
   ሀ. በጠቅላላ ስንት ብር አወጣች?
   ለ. ስንት ብር ይቀራታል?

**ምሳሌ 4.12፡-** **የሚከተሉትን አስሉና መልሱን አረጋግጡ።**

ሀ. 3500 – 2900

ለ. የአህመድ የወር ደሞወዝ 2000 ብር ነው። ለቤት ኪራይ 350 ብር፣ ለምግብ 1400 ብር ቢያወጣ ስንት ብር ይቀረዋል?

**መፍትሔ፡-**

**ሀ. 3500 – 2900 = 600 ምክንያቱም 3500 = 600 + 2900 ስለሆነ**

**ለ. የአህመድ የወር ደሞወዝ = 2000 ብር**

**የአህመድ ጠቅላላ ወጪ = 350 + 1400 ብር = 1750 ብር**

**ከወጪ ቀሪ = 2000 – 1750 = 250 ብር**

**ምክንያቱም 2000 = 250 + 1750 ብር ስለሆነ**

## መልመጃ ቸ

1. የሚከተሉትን አስሉና መልሱን አረጋግጡ።
   ሀ. 347 – 57 ለ. 463 – 249 ሐ. 2465 - 65 መ. 5843 – 695
2. አንድ አርሶ አደር 7000 ብር ይዞ ወደ ገበያ ወጣ። በ1200 ብር ማዳበሪያና በ5000 ብር ሁለት በሬዎችን ገዝቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ።
   ሀ. በጠቅላላ ስንት ብር አወጣ?
   ለ. ስንት ብር ቀረው? መልሳችሁን አረጋግጡ።
3. ዋናው 5000፣ ልዩነቱ 0 ቢሆን፤ ተቀናሹ ስንት ይሆናል? መልሳችሁን አረጋግጡ?

# የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

- ሁለት የ1000 ብዜቶችን በቃል ለመደመር በሺ ቤት የሚገኙ ሆሄዎችን ደምሮ ከውጤቱ በስተቀኝ ሦስት ዜሮዎችን መፃፍ፡፡
- ባለ 2 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር ያለ አለኝታና በአለኝታ መደመር ይቻላል፡፡ ቀላሉ የአደማመር ስልት ቁጥሮቹን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመፃፍ ሆሄያቶችን በየቤታቸው መደመር ነው፡፡

  መጀመሪያ በ1 ቤት ያሉትን፣ ቀጥሎ በ10 ቤት ያሉትን እየደመሩ በየቤቱ ስር መፃፍ፡፡ ድምሩ ያለ አለኝታ ድምር በሚሆንበት ጊዜ በመቶ ቤት የሚገኘውን ሆሄ እንዳለ በቤቱ ስር መፃፍ፡፡

  በአለኝታ በሚደመርበት ጊዜ፡- ከአንድ ቤት በመጀመር በየቤቱ የሚገኙትን ደምሮ "አለኝ" የሚባለውን ከሚቀጥለው የቁጥር ቤት ሆሄዎች ጋር መደመር፡፡
- ለቃላት ፕሮብሌሞች መፍትሔ ሲፈለግ፡- መጀመሪያ ጥያቄውን ደጋግሞ አንብቦ መረዳት፡፡ ቀጥሎ የተሰጠውንና የሚፈለገውን መለየት፡፡ በመጨረሻ መልሱን በስራ ማግኘት እና ማረጋገጥ፡፡
- ከባለ 3 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለ 2 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ለመቀነስ ልክ እንደ መደመሩ በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል መፃፍ፡፡ ከዚያም በቤት በቤታቸው መቀነስና ውጤቱን በየቤቱ ስር መፃፍ፡፡ (በብድር ወይም ያለ ብድር ሊሆን ይችላል)
- ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን በመደመር የሚገኝ መልስ በመቀነስ ይረጋገጣል፡፡ ከአንድ ሙሉ ቁጥር ላይ ሌላ ሙሉ ቁጥር በመቀነስ የሚገኝ መልስ በመደመር ይረጋገጣል፡፡
- ባለ 3 ሆሄን ከባለ 3 ሆሄ ስትቀንሱ መልሱ ሁልጊዜ ሙሉ ቁጥር መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ ማለት ዋናው ከተቀናሹ ማነስ የለበትም ማለት ነው፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ደምሩ፡፡

ሀ. $+\begin{array}{r}574\\ \underline{24}\end{array}$ ለ. $+\begin{array}{r}835\\ \underline{65}\end{array}$ ሐ. $+\begin{array}{r}4273\\ \underline{314}\end{array}$

መ. $+\begin{array}{r}5678\\ \underline{331}\end{array}$ ሠ. $+\begin{array}{r}3435\\ \underline{4353}\end{array}$ ረ. $+\begin{array}{r}6305\\ \underline{1725}\end{array}$

2. የሚከተሉትን ቀንሱ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r} 364 \\ -\ \ 52 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 525 \\ -\ \ 64 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 548 \\ -\ 235 \\ \hline \end{array}$

መ. $\begin{array}{r} 647 \\ -\ 266 \\ \hline \end{array}$ ሠ. $\begin{array}{r} 5637 \\ -\ 1324 \\ \hline \end{array}$ ረ. $\begin{array}{r} 7534 \\ -\ 2375 \\ \hline \end{array}$

3. አንድ የገበሬዎች ስራ ማህበር ከጤፍ ሽያጭ 3470 ብር እና ከስንዴ ሽያጭ 2550 ብር አገኘ፡፡ ማህበሩ በጠቅላላ ስንት ብር አገኘ?
4. አንድ የስኳር ፋብሪካ በሁለት ተከታታይ ቀናት 4500 ኩንታልና 3900 ኩንታል ስኳር አመረተ፡፡ በሁለት ቀን ከተመረተው ስኳር ውስጥ 6300 ኩንታል ለተለያዩ ድርጅቶች ተሸጠ፡፡ ያልተሸጠው ስኳር ስንት ኩንታል ነው?
5. በአንድ ዓመት ውስጥ በአንድ ሆስፒታል ታመው ለምርመራ ከተመዘገቡ 5843 ሰዎች ውስጥ 1200 ሰዎች በሳንባ በሽታ የተያዙ ሲሆኑ 450 በኤች አይ ቪ ቫይረስ የተያዙ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ደግሞ በወባ በሽታ የተያዙ ናቸው፡፡ በወባ በሽታ የተያዙት ሰዎች ስንት ናቸው?
6. ባለፈው አመት በአንድ ወረዳ 9824 ኩንታል ስንዴ፣ 8992 ኩንታል በቆሎ እና 10,000 ኩንታል ጤፍ ተመረተ፡፡ በአጠቃላይ በወረዳው ስንት ኩንታል ምርት ተመረተ?
7. የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ፡፡

| ጠ | ቀ | ጠ + ቀ |
|---|---|---|
| 9866 | 8834 | |
| 4289 | 5884 | |
| 3886 | 1725 | |

8. ከዚህ በታች የተሰጠውን ሰንጠረዥ አሟሉ፡፡

| ዋና | ተቀናሽ | ልዩነት |
|---|---|---|
| 10,000 | 9,000 | |
| | 648 | 3844 |
| 6788 | | 4788 |

# ምዕራፍ አምስት

# እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛትና ማካፈል

**የመማር ማስተማር ውጤቶች፡-**

- የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት፡፡
- የ1,000 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት፡፡
- የማባዛት ውጤታቸው ከ10,000 ያልበለጡ የሙሉ ቁጥሮችና የባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች ብዜት መፈለግ፡፡
- እስከ 10,000 ያሉ የ10 እና የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር እና በ10 ማካፈል፡፡
- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር እና በ10 በቀሪ እና ያለቀሪ ማካፈል፡፡
- የማባዛትና የማካፈል ስሌቶችን በመጠቀም የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት፡፡

## 5.1 የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት

የሙሉ ቁጥሮችን የ100 ብዜት ማግኘት በምዕራፍ አንድ ተምራችኋል፡፡ የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ1 ሆሄ ቁጥሮች ማባዛት ደግሞ ቀጥሎ ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 5.1

**በግል የሚሠራ**

1. በዜሮና በ1200 መካከል የሚገኙ የ100 ብዜቶችን በቅደም ተከተል ዘርዝሩ፡፡
2. "ሀ" የ100 ብዜት ሙሉ ቁጥር ቢሆን፤ ሀ × 1 ምን አይነት ሙሉ ቁጥር ይሆናል?

## የቡድን ስራ 1

1. የሚከተሉትን አባዙ፡፡

   ሀ. 200 × 3    ለ. 500 × 4    ሐ. 400 × 4

2. የማባዛት ውጤቱን በአጭሩ ለማግኘት ምን አይነት የአስራር ስልት ተጠቀማችሁ?

## ምሳሌ 5.1

የሚከተሉትን አባዙ፡፡

ሀ. 600 × 4    ለ. 700 × 5

### መፍትሔ

ሀ. 600 × 4 ይህን ማባዛት ለመስራት 6ን በ4 አባዝቶ ከውጤቱ በስተቀኝ ሁለት ዜሮዎችን መፃፍ

600 × 4 = (6 × 4) × 100 → መጀመሪያ ቅንፍ ውስጥ ያለውን ማባዛት

= 24 × 100 = 2400

ስለዚህ 600 × 4 = 2400

ለ. 700 × 5 የዚህን ውጤት ለማግኘት 7 ን በ 5 ማባዛት ማለትም 7 × 5 = 35 ከውጤቱ ከ35 በስተቀኝ ሁለት ዜሮዎችን መፃፍ፡፡

ስለዚህ 700 × 5 = 3500

**ማስታወሻ**

የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ስታባዙ የሚከተለውን አሰራር ተከተሉ፡፡

ከተሰጠው የመቶ ብዜት ቁጥር ዜሮ ያልሆነው ሆሄ ከባለ አንድ ሆሄ ጋር አባዝቶ ከውጤቱ በስተቀኝ ሁለት ዜሮዎችን መጻፍ፡፡

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

   ሀ. 1 × 800
   ለ. 2 × 900
   ሐ. 3 × 600
   መ. 4 × 700
   ሠ. 5 × 900
   ረ. 6 × 500
   ሰ. 900 × 7
   ሸ. 700 × 7
   ቀ. 500 × 8
   በ. 800 × 9

2. የሚከተለውን የአብዥ ሰንጠረዥ አሟሉ፡፡

| × | 100 | 200 | 300 | 400 | 500 | 600 | 700 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | 300 | | 500 | | 700 |
| 2 | | 400 | | 800 | 1000 | | |
| 3 | | | | | | | |
| 4 | 400 | | 1200 | | 2000 | | |
| 5 | | 1000 | | 2000 | | | 3500 |
| 6 | 600 | | 1800 | | 3000 | | |
| 7 | | 1400 | | 2800 | | 4200 | |
| 8 | | | 2400 | | 4000 | | 5600 |
| 9 | 900 | | | 3600 | | | 6300 |

## 5.2 የ1000 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት

የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ1 ሆሄ ቁጥሮች ማባዛት በንዑስ ምዕራፍ አንድ ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ከ 10,000 ያነሱና የ1000 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 5.2

**ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚሰራ፡፡**

1. እስከ 10,000 የሚደርሱ የ1000 ብዜቶችን በቅደም ተከተል ዘርዝሩ፡፡
2. የ100 ብዜቶች ሁሉ የ1000 ብዜቶች ሊሆኑ እንደማይችሉ ምሳሌዎችን በመመስረት ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡
3. የ1000 ብዜቶች ሁሉ የ100 ብዜቶች ናቸው፡፡ ለምን?
4. የሚከተሉትን አባዙ፡፡

   ሀ. $2000 \times 3$ ለ. $3000 \times 4$
5. በተራ ቁጥር 4 የቀረቡትን ጥያቄዎች ስታባዙ ምን አይነት ቀላል መንገድ ተጠቀማችሁ?

**ምሳሌ 5.2** የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. $2 \times 4000$ ለ. $3 \times 3000$

**መፍትሄ**

ሀ. $4000 \times 2 \rightarrow$ በ ሺ ቤት የሚገኘውን 4ን በ2 ማባዛት፤ $4 \times 2=8$ ከዚያም ከውጤቱ በስተቀኝ ሦስት ዜሮዎች መፃፍ፡፡

ይህ ማለት $2\times4000 = 2 \times 4 \times 1000 = (2\times4) \times1000$

$= 8 \times 1000 \rightarrow$ መጀመሪያ ቅንፍ ውስጥ ያለው በመባዛቱ ምክንያት

$= 8000$

ስለዚህ $2 \times 4000 = 8000$

ለ. $3000 \times 3 = (3 \times 3) \times 1000$ → በሺ ቤት የሚገኘውን መጀመሪያ ማባዛት

$= 9 \times 1000$

$= 9000$

**ማስታወሻ**

ከ 10,000 ያነሱና የ1000 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በቀላሉ አባዝቶ ውጤቱን ለማግኘት፤

በሺ ቤት የሚገኘውን ሆሄ በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር አባዝቶ ከሚገኘው ውጤት በስተቀኝ ሦስት ዜሮዎችን መፃፍ ነው፡፡

## መልመጃ ለ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. $2 \times 2000$ ለ. $3 \times 2000$ ሐ. $2 \times 3000$

መ. $2 \times 5000$ ሠ. $1 \times 7000$ ረ. $1 \times 8000$

2. የሚከተለውን የአብዥ ሰንጠረዥ አሟሉ፡፡

| × | 6 | 7 | 8 | 9 |
|---|---|---|---|---|
| 1000 | | | | 9000 |

3.የሚከተሉትን የአብዥ ሰንጠረዦች አሟሉ፡፡

ሀ.

| × | 5 | 4 |
|---|---|---|
| 1000 | | |
| 2000 | | |

ለ.

| × | 3 |
|---|---|
| 1000 | |
| 2000 | |
| 3000 | |

ሐ.

| × | 2 |
|---|---|
| 1000 | |
| 2000 | |
| 3000 | |
| 4000 | |
| 5000 | |

## 5.3 የማባዛት ውጤታቸው ከ10,000 ያልበለጡ የሙሉ ቁጥሮችና የባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች ብዜት

የ100 ብዜቶችንና የ1000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥር ማባዛት ቀደም ባሉት ምዕራፎች ተምራችኋል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ባለ 2 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥር ማባዛትን ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 5.3

**የሚከተሉትን አባዙ፡፡**

ሀ. $33 \times 3$ ለ. $45 \times 2$

ከላይ የተሰጡትን የማባዛት ጥያቄዎች በተለያዩ መንገዶች ሞክራችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ባለሁለት ሆሄ ቁጥሮቹን ደጋግሞ በመደመር ወይም ሆሄዎችን በቤት በቤታቸው አባዝቶ ውጤቱን በመፃፍ ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ምሳሌና ማስታወሻ ሆሄዎችን በቤት በቤታቸው አባዝቶ ውጤት ማግኘትን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

## ምሳሌ 5.3

**የሚከተሉትን አስሉ፡፡**

ሀ. $\begin{array}{r} 23 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 42 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$

**መፍትሄ፡-**

ሀ. $\begin{array}{r} 23 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ - መጀመሪያ የአንድ ቤት ሆሄውን 3ን በ3 ማባዛትና ውጤቱን በአንድ ቤት ስር መፃፍ፡-

$3 \times 3 = 9$

- ከዚያም የ10 ቤት ሆሄውን ማባዛትና ውጤቱን በ10 ቤት ስር መፃፍ፡- $3 \times 2 = 6$

ስለዚህ $\begin{array}{r} 23 \\ \times 3 \\ \hline 69 \end{array}$ ይሆናል፡፡

ለ. $\begin{array}{r} 42 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$ - መጀመሪያ የአንድ ቤት ሆሄውን 2 ን በ 4 ማባዛትና ውጤቱን በአንድ ቤት ስር መፃፍ፡-

$4 \times 2 = 8$

- ከዚያም የ10 ቤት ሆሄውን ማባዛትና ውጤቱን በ10 እና በ100 ቤት ስር መፃፍ፡- $4 \times 4 = 16$

ስለዚህ $\begin{array}{r} 42 \\ \times 4 \\ \hline 168 \end{array}$ ይሆናል፡፡

**ማስታወሻ**

ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ሲባዙ (አለኝታ የሌለበት)

- መጀመሪያ የአንድ ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤት በ1 ቤት መፃፍ፡-
- ቀጥሎ የ10 ቤት ሆሄን አባዝቶ ውጤቱን በ10 ቤት ወይም በ10 እና በ100 ቤቶች መፃፍ፡፡

## መልመጃ ሐ

**የሚከተሉትን አባዙ፡፡**

ሀ. $\begin{array}{r} 24 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 33 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 44 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 22 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$

ሠ. $\begin{array}{r} 53 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ረ. $\begin{array}{r} 74 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ሰ. $\begin{array}{r} 82 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ ሸ. $\begin{array}{r} 31 \\ \times 5 \\ \hline \end{array}$

ቀ. $\begin{array}{r} 62 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$ በ. $\begin{array}{r} 93 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ተ. $\begin{array}{r} 81 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$ ቸ. $\begin{array}{r} 73 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$

**ማስታወሻ**

**ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር በአለኝታ ሲባዙ፡-**

- **የአንድ ቤት ሆሄን አባዝቶ ከሚገኘው ውጤት የአንድ ቤት ሆሄውን በአንድ ቤት ፅፎ የ10 ቤት ሆሄውን አለኝ ብሎ ማቆየት፡፡**
- **ቀጥሎ የ10 ቤት ሆሄውን አባዝቶ ውጤቱን አለኝ ከተባለው ጋር መደመር እና መልሱን በ10 ቤት ስር ወይም በ10 እና በ100 ቤት ስር መፃፍ፡፡**

**ምሳሌ 5.4፡-** የሚከተሉትን አባዙ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r} 24 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 34 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$

**መፍትሄ፡-**

ሀ. $\begin{array}{r} 24 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ - መጀመሪያ የአንድ ቤት ሆሄውን ማባዛት፡- 4 ×3=12 “2”ን በአንድ ቤት ስር ፅፎ፤ የ10 ቤት ሆሄውን “1”ን አለኝ ብሎ ማቆየት፣

- ቀጥሎ የ10 ቤት ሆሄውን 2ን በ3 ማባዛት፡- 2 ×3=6 ውጤቱን “6”ንና አለኝ ያልነውን መደመር፡- 6+1=7 - ይህንንም በ10 ቤት መፃፍ፡፡

ስለዚህ $\begin{array}{r} 24 \\ \times 3 \\ \hline 72 \end{array}$ ይሆናል፡፡

ለ. $\begin{array}{r} 34 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$ - መጀመሪያ የአንድ ቤት ሆሄውን 4ን በ4 ማባዛት፡- 4 ×4=16 “6”ን በአንድ ቤት ስር መፃፍ፤ የ10 ቤት ሆሄውን “1”ን ደግሞ አለኝ ብሎ ማቆየት፣

- ቀጥሎ የ10 ቤት ሆሄውን 3ን በ4 ማባዛት፡- 3 × 4=12 ውጤቱን “12”ንና አለኝ ያልነውን መደመር፡- 12+1=13 - ይህንንም በ10 ቤትና በ100 ቤት ስር መፃፍ፡፡

ስለዚህ $\begin{array}{r} 34 \\ \times 4 \\ \hline 136 \end{array}$ ይሆናል፡፡

## መልመጃ መ

የሚከተሉትን አባዙ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r} 26 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 36 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 45 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 53 \\ \times 5 \\ \hline \end{array}$

ሠ. $\begin{array}{r} 67 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ረ. $\begin{array}{r} 59 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ ሰ. $\begin{array}{r} 88 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ ሸ. $\begin{array}{r} 76 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$

ቀ. $\begin{array}{r} 47 \\ \times 7 \\ \hline \end{array}$ በ. $\begin{array}{r} 56 \\ \times 8 \\ \hline \end{array}$ ተ. $\begin{array}{r} 65 \\ \times 9 \\ \hline \end{array}$ ቸ. $\begin{array}{r} 93 \\ \times 6 \\ \hline \end{array}$

## ሦስት ሆሄ ያላቸውን ሙሉ ቁጥሮች አንድ ሆሄ ካላቸው ሙሉ ቁጥሮች ጋር ማባዛት

ከዚህ በፊት ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት ተምራችኋል፡፡ የተማራችሁትን መሠረት በማድረግ ባለሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለአንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት ደግሞ አሁን ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 5.4

**ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ፡፡**

1. ትንሹ ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ5 ሲባዛ ውጤቱ ስንት ይሆናል?
2. የሚከተለውን የማባዛት ሂደት ተመልከቱና ለመጨረሻው መልስ ዒፉ፡፡

$$7 \times 5 = 35$$
$$70 \times 5 = 350$$
$$700 \times 5 = ?$$

**ማስታወሻ**

ሦስት ሆሄ ያላቸው ሙሉ ቁጥሮች አንድ ሆሄ ካላቸው ሙሉ ቁጥሮች ጋር ያለ አለኝታ ሲባዙ አሰራሩ ፡- በቤት በቤታቸው ማባዛትና ውጤቱንም በቤት በቤታቸው ስር መፃፍ ነው፡፡

**ምሳሌ 5.5፡-** የሚከተሉትን አባዙ፡-

ሀ. $\begin{array}{r} 232 \\ \times \ \ 2 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 432 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$

**መፍትሔ**

ሀ. $\begin{array}{r} 232 \\ \times \ 2 \\ \hline \end{array}$ በቤት በቤታቸው አባዝቶ ውጤቱንም በየቤታቸው ስር መፃፍ፡-

$2 \times 2 = 4$ ----------- 4ን በ1 ቤት መፃፍ

$2 \times 3 = 6$ ----------- 6ን በ10 ቤት መፃፍ

$2 \times 2 = 4$ -----------4ን በ100 ቤት መፃፍ

ስለዚህ $\begin{array}{r} 232 \\ \times \ \ 2 \\ \hline 464 \end{array}$ ይሆናል፡፡

ለ. $\begin{array}{r} 432 \\ \times\ 3 \\ \hline \end{array}$ በየቤታቸው ማባዛትና ውጤቱንም በየቤታቸው ስር መፃፍ፡-

3 x2 = 6 ----------- 6ን በ1 ቤት ስር መፃፍ

3 x3 = 9 ----------- 9ን በ10 ቤት ስር መፃፍ

3 x4=12 ----------- 12ን በ100 ቤትና በሺ ቤቶች መፃፍ

ስለዚህ $\begin{array}{r} 432 \\ \times\ 3 \\ \hline 1296 \end{array}$ ይሆናል።

## መልመጃ ሠ

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. $\begin{array}{r} 434 \\ \times\ 2 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 321 \\ \times\ 3 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 142 \\ \times\ 2 \\ \hline \end{array}$ ሰ. $\begin{array}{r} 813 \\ \times\ 3 \\ \hline \end{array}$

መ. $\begin{array}{r} 711 \\ \times\ 5 \\ \hline \end{array}$ ሠ. $\begin{array}{r} 633 \\ \times\ 3 \\ \hline \end{array}$ ረ. $\begin{array}{r} 521 \\ \times\ 4 \\ \hline \end{array}$

2. ትንሹ ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ9 ሲባዛ የሚገኘው ውጤት ስንት ነው?

**ማስታወሻ**

ሦስት ሆሄ ያላቸውን ሙሉ ቁጥሮች አንድ ሆሄ ካላቸው ሙሉ ቁጥሮች ጋር በአለኝታ ስታባዙ፡-

- የአንድ ቤት ሆሄን አባዝቶ ከሚገኘው ውጤት የአንድ ቤት ሆሄውን በአንድ ቤት ስር ፅፎ በ10 ቤት የሚገኘውን ሆሄ አለኝ ብሎ ማቆየት፣
- ቀጥሎ የ10 ቤት ሆሄውን ማባዛት። ውጤቱን "አለኝ" ከተባለው ጋር መደመር። ከተደመረ በኂላ የተገኘውን ውጤት በ10 ቤት ስር መፃፍ፣
- በመጨረሻ የ100 ቤት ሆሄውን ማባዛት። በአለኝታ የቆየ ካለ ከውጤቱ ጋር ደምሮ በ100 ቤት ወይም በ100 ቤትና በ1000 ቤት ስር መፃፍ።

**ምሳሌ 5.6፡-** የሚከተሉትን አባዙ።

ሀ. $\begin{array}{r} 126 \\ \times 5 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 653 \\ \times\ 4 \\ \hline \end{array}$

**መፍትሄ፡-**

ሀ. $\begin{array}{r} 126 \\ \times\ 5 \\ \hline \end{array}$ - እንደሚከተለው በቤት በቤታቸው ማባዛት፡-

5 ×6=30 → "0"ን በ1 ቤት ስር ፅፎ "3"ን በአለኝ ታ ወይም በተሸጋሪነት ማቆየት፣

5 ×2=10 → "10"ን አለኝ ካልነው ከ3 ጋር መደመር፡- 10+3=13 "3"ን በ10 ቤት ስር መፃፍና "1"ን በአለኝ ማቆየት፣

5 ×1=5 → "5"ን በአለኝታ ካቆየነው ከ "1" ጋር መደመር 5+1= 6 ስለሆነም "6"ን በመቶ ቤት ስር መፃፍ።

ስለዚህ $\begin{array}{r} 126 \\ \times\ 5 \\ \hline 630 \end{array}$ ይሆናል።

ለ. $\begin{array}{r} 653 \\ \times\ 4 \\ \hline \end{array}$ - እንደሚከተለው በቤት በቤታቸው አባዝቶ በአለኝታ የሚቆዩትን ሆሄዎች መደመርና መልሱን ማግኘት፡-

4 ×3=12 → "2"ን በ1 ቤት ስር መፃፍና "1"ን በአለኝ ማቆየት፣

4×5=20 → "20"ን ከ"1" ጋር መደመር፡- 20+1=21 "1"ን በ10 ቤት ስር ፅፎ "2"ን በአለኝ ማቆየት፣

4 ×6=24 → "24"ን በአለኝታ ካቆየነው ከ "2" ጋር መደመር 24+2=26 "6"ን በ100 ቤትና "2"ን በ1000 ቤት ስር መፃፍ።

ስለዚህ $\begin{array}{r} 653 \\ \times 4 \\ \hline 2612 \end{array}$ ይሆናል።

## መልመጃ ረ

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. $\begin{array}{r} 375 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 406 \\ \times\ 3 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 527 \\ \times\ 4 \\ \hline \end{array}$ ሰ. $\begin{array}{r} 348 \\ \times\ 9 \\ \hline \end{array}$

መ. $\begin{array}{r} 626 \\ \times\ 5 \\ \hline \end{array}$ ሠ. $\begin{array}{r} 723 \\ \times\ 6 \\ \hline \end{array}$ ረ. $\begin{array}{r} 127 \\ \times\ 8 \\ \hline \end{array}$

2. ትልቁ ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ7 ሲባዛ ውጤቱ ስንት ይሆናል?

### ማባዛትን የያዙ ቀለል ያሉ የቃላት ኘሮብሌሞችን መፍታት

እስከ አሁን የተማራችሁትን የማባዛት አሰራር ተጠቅማችሁ ለቃላት ፕሮብሌሞች መፍትሔ መፈለግ ቀጥሎ ትማራላችሁ።

## ተግባር 5.5

**ለሚከተሉት የቃላት ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን መፍትሔ ፈልጉ።**

1. የአንድ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ለ4 ኅበዝ ሴት ተማሪዎች ደብተር መሸለም ፈለገ። ለእያንዳንዳቸው 15 ደብተሮችን ለመስጠት ርዕሰ መምህሩ ስንት ደብተሮች ያስፈልጉታል?

2. ይልማ አምስት የማንጎ ችግኝ መደቦች አሉት። በእያንዳንዱ መደብ 23 ችግኞች አሉ። ይልማ በጠቅላላው ስንት የማንጎ ችግኝ አሉት?



የማንጎ ችግኝ መደብ

**ማስታወሻ**

**ለቃላት ፕሮብሌሞች መፍትሔ ስትፈልጉ ከዚህ በፊት እንደተማራችሁት፡- መጀመሪያ ጥያቄዎችን ደጋግሞ በማንበብ መረዳት ያስፈልጋል። ቀጥሎ በጥያቄው ውስጥ የተሰጡትን መረጃዎች ተጠቅሞ የተጠየቀውን መፈለግ። በመጨረሻ የተገኘውን መልስ ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል።**

## መልመጃ ሰ

**የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች መፍትሔ ፈልጉ።**

1. አበበ ኮትና ሱሪ ለማሰፋት 3 ሜትር ጨርቅ ያስፈልገዋል። የአንዱ ሜትር ጨርቅ ዋጋ 120 ብር ነው። አበበ ሶስት ሜትር ጨርቅ ለመግዛት ስንት ብር ያስፈልገዋል?



በሜትር የሚሸጡ ጥቅል ጨርቅ

2. ለአንድ ትምህርት ቤት ቤተ-መፅሐፍ አገልግሎት የሚውሉ 6 የሂሳብ መፅሐፎች ተገዝተዋል። የአንዱ መፅሐፍ ዋጋ 115 ብር ቢሆን የስድስቱ መፅሐፎች ጠቅላላ ዋጋ ስንት ይሆናል?
3. አቶ አህመድ የቡና ነጋዴ ናቸው። ሰኞ 4 ኩንታል ቡና ሸጡ። የአንዱ ኩንታል ቡና ዋጋ 850 ብር ነው። አቶ አህመድ 4ቱን ኩንታል ቡና ሲሸጡ በጠቅላላው የሚያገኙት ስንት ብር ነው?
4. አንድ የእግር ኳስ ቡድን 5 ኳሶችን ለመግዛት ይፈልጋል። የአንዱ እግር ኳስ ዋጋ 240 ብር ቢሆን 5 ኳሶችን ለመግዛት ስንት ብር ያስፈልጋል?
5. አንድ ባለሀብት በ8 ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ረዳት ለሌላቸው ተማሪዎች ደብተሮች ገዝተው ለማከፋፈል ፈለጉ። ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት 320 ደብተሮች ቢሰጡ፤ በጠቅላላ ስንት ደብተሮችን ይሰጣሉ?

## 5.4 እስከ 10,000 ያሉ የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮችና በ10 ማካፈል

በምዕራፍ አንድ እስከ 100 ያሉ ሙሉቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማካፈል ተምራችኋል። **በተካፋይ፣ አካፋይና ድርሻ** መካከል ያለውን ዝምድናም ታስታውሳላችሁ። አሁን ደግሞ እስከ 10,000

ያሉ የ10 እና የ100 ብዜት ቁጥሮችን በ10 ማካፈል ትማራላችሁ።

### ተግባር 5.6

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ።**

1. 50 ጠጠሮች በ10 እኩል ቦታ ቢመደቡ በእያንዳንዱ ምድብ ስንት ጠጠሮች ይኖራሉ?
2. አንድ ትምህርት ቤት በሽልማት ወቅት 160 ደብተሮችን ለ10 ጎበዝ ተማሪዎች እኩል ቢያካፍላቸው፤ ለእያንዳንዳቸው ስንት ስንት ደብተሮች ይደርሳቸዋል?
3. አንድ የህብረት ስራ ማህበር 300 እንቁላል ጣይ ዶሮዎችን ገዝቶ ለ10 የማህበሩ አባላት እኩል አከፋፈለ። ለአንዱ የማህበር አባል ስንት ዶሮዎች ደረሱት?

የተግባሩን ሦስት ጥያቄዎች ስትሰሩ ምን አይነት አጭር የአሰራር ስልት አገኛችሁ? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተጨማሪ ውይይት በማድረግ የምትደርሱበትን ስምምነት ለመምህራችሁ ተናገሩ።

**ምሳሌ 5.7፡-** የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 80 ÷10 ለ. 3600 ÷10 ሐ. 3040÷10

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 80 ÷10 = 8 ምክንያቱም 80 የ10 ብዜት ነው። 80ን ለ10 አካፍለን የምናገኘው ውጤት ከ80 ላይ “0”ን በመተው የምናገኘው ቁጥር ነው።

ለ. 3600 የ100 ብዜት ነው። 3600ን ለ10 አካፍለን የምናገኘው ውጤት ከ3600 በአንድ ቤት የሚገኘውን “0” በመተው ነው።

ስለዚህ 3600 ÷10 = 360 ይሆናል።

ሐ. 3040 ÷ 10 = 304 ምክንያቱም 3040 = 304 x 10

**ማስታወሻ**

የ10 ወይም የ100 ብዜት የሆነን ቁጥር ለ10 በማካፈል የሚገኘው ውጤት የቁጥሩን የ1 ቤት ሆሄ “0”ን በመተው የሚገኘው ቁጥር ነው። በማካፈል የሚገኘን ውጤት በማባዛት ማረጋገጥ ይቻላል።

# መልመጃ ሸ

**የሚከተሉትን አካፍሉና፤ መልሳችሁን በማባዛት አረጋግጡ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. 10 ÷10 = ______ | ለ. 100 ÷10 = ______ | ሐ. 150 ÷10 = ______ |
| 20 ÷10 = ______ | 300 ÷10 = ______ | 550 ÷10 = ______ |
| 30 ÷10 = ______ | 400 ÷10 = ______ | 870 ÷10 = ______ |
| 50 ÷10 = ______ | 600 ÷10 = ______ | 4300 ÷10 = ______ |
| 70 ÷10 = ______ | 800 ÷10 = ______ | 8080 ÷10 = ______ |
| 80 ÷10 = ______ | 900 ÷10 = ______ | 9900 ÷10 = ______ |
| 90 ÷10 = ______ | | |

## እስከ 10,000 ያሉ የ10 እና የ100 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር በቀሪና ያለ ቀሪ ማካፈል

እስከ 10,000 ያሉ የ10 እና የ100 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በ10 ማካፈል ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር በቀሪና ያለቀሪ ማካፈል ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 5.7

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ፡፡ መልሳችሁንም አረጋግጡ፡፡**

ሀ. 30 ጠጠሮች ስድስት ቦታ እኩል ቢመደቡ፤ በእያንዳንዱ ምድብ ስንት ጠጠሮች ይኖራሉ?

ለ. 300 ጠጠሮች ስድስት እኩል ቦታ ቢመደቡ፤ በእያንዳንዱ ምድብ ስንት ጠጠሮች ይኖራሉ?

ሐ. 3000 ጠጠሮች ስድስት እኩል ቦታ ቢመደቡ፤ በእያንዳንዱ ምድብ ስንት ጠጠሮች ይኖራሉ?

የ “ሀ”ን፣ የ “ለ”ን እና “ሐ”ን ጥያቄዎች ስትመልሱ የተጠቀማችሁበት ቀላል መንገድ ካለ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

**ማስታወሻ**

ሀ፣ ለ እና መ ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑና ሀ ÷ ለ = መ እውነት ከሆነ

ሀ = መ × ለ ሁልጊዜ እውነት ነው፡፡

“ሀ” ተካፋይ፣ “ለ” አካፋይ፣ “መ” ድርሻ ይባላሉ፡፡

ተካፋይ = (ድርሻ) × (አካፋይ)

**ምሳሌ 5.8፡-** የሚከተሉትን አስሉ፡፡ መልሳችሁንም በማባዛት አረጋግጡ፡፡

ሀ. 80÷4 ለ. 300÷5

**መፍትሔ:-**

ሀ. 80 ÷4 = 20 ምክንያቱም 80 = 20 × 4 በመሆኑ ነው። ስለዚህ ተካፋይ = 80፣ አካፋይ = 4 እና ድርሻ = 20 ናቸው።

ለ. 300 ÷ 5 = 60 ምክንያቱም 300 = 60 x 5። ተካፋይ = 300፣ አካፋይ = 5 እና ድርሻ=60 ናቸው።

የማካፈል ውጤት በማባዛት ይረጋገጣል። ስለዚህ ማካፈል የማባዛት ግልብጥ ስሌት ነው ይባላል። እንዲሁም ማባዛት የማካፈል ግልብጥ ስሌት ነው ይባላል።

## መልመጃ ቀ

1. የሚከተሉትን አስሉ። መልሳችሁን በማባዛት አረጋግጡ።

ሀ. 70 ÷7 ለ. 90 ÷3 ሐ.120 ÷4

መ. 150 ÷5 ሠ. 400 ÷8 ረ. 660 ÷6

ሰ. 7200 ÷9 ሸ. 4500 ÷3

2. የሚከተሉትን አስሉ። ለእያንዳንዳቸው ተካፋዮችን፣ አካፋዩን እና ድርሻውን ለይታችሁ በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

ሀ. 720÷8 ለ. 210÷3 ሐ. 2700÷9

መ. 5400÷5 ሠ. 3500÷7 ረ. 480÷6

**ማስታወሻ**

ሀ፣ለ፣መ እና በ ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑና ሀ ÷ ለ = መ ሆኖ ቀሪ በ ከሆነ ሀ= ለ × መ + በ ሁልጊዜ እውነት ነው።

**ምሳሌ 5.9:-** የሚከተሉትን አስሉ። መልሱንም አረጋግጡ።

ሀ. 80 ÷ 3 = 26 ቀሪ 2 ምክንያቱም 80 = 26 × 3 + 2 ነው።

ለ. 120 ÷ 7=17 ቀሪ 1 ምክንያቱም 120 = 17 × 7 + 1 ነው።

ሐ. 115 ÷ 9 = 12 ቀሪ 7 ምክንያቱም 115 = 12 × 9 + 7 ነው።

## መልመጃ በ

1. የሚከተሉትን አስሉ። መልሳችሁን በማባዛት አረጋግጡ።

ሀ. 50 ÷ 6 ሐ. 250 ÷ 3 ሠ. 8000 ÷ 9

ለ. 90 ÷ 4 መ. 400 ÷ 7 ረ. 700 ÷ 8

2. አንድ ሙሉ ቁጥር ለ 6 ሲካፈል ድርሻው 83 ቀሪው ደግሞ 2 ነው። ቁጥሩ ስንት ነው?

## 5.5 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች እና በ10 በቀሪና ያለቀሪ ማካፈል

ስለ ማካፈል እስከ አሁን የተማራችሁትን መሠረት በማድረግ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች ማካፈል ትማራላችሁ። መጀመሪያ ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ቀጥሎ ደግሞ ባለ 3 እና ባለ 4 ሆሄ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች ማካፈል ትማራላችሁ።

### ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ያለ ቀሪ ማካፈል

**ተግባር 5.8**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ስሩ።**

1. 35 ጠጠሮችን 7 እኩል ቦታ መድቡ። በአንዱ ምድብ የሚገኙ ጠጠሮች ስንት ናቸው?



2. 54 ብርቱካኖችን ዘጠኝ ልጆች እኩል ቢካፋፈሉ፤ የአንዱ ልጅ ድርሻ ስንት ብርቱካኖች ይሆናል?



**ምሳሌ 5.10፡-** **የሚከተሉትን ምሳሌዎች አሠራር ተመልክታችሁ በተመሳሳይ መንገድ የመልመጃ ጥያቄዎችን ሥሩ።**

**ሀ.** $48 \div 6 = (30+18) \div 6$
$= [30 \div 6] + [18 \div 6]$
$= 5+3$
$= 8$
ስለዚህ $48 \div 6 = 8$

**ለ.** $54 \div 9 = (45+9) \div 9$
$= 45 \div 9 + 9 \div 9$
$= 5+1$
$= 6$
ስለዚህ $54 \div 9 = 6$

## መልመጃ ተ

በምሳሌ 5.10 መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ።

ሀ. 26÷2 ለ. 36÷3 ሐ. 42÷2 መ. 48÷3

ሠ. 44÷4 ረ. 64÷4 ሰ. 75÷5 ሸ. 66÷6

ቀ. 96÷8 በ. 84÷7 ተ. 99÷9

## ቀሪ የሚያስከትሉ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማካፈል

### ተግባር 5.9

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ሥሩ።

1. 19 እርሳሶችን 3 ልጆች እኩል ቢካፈሉ ለእያንዳንዳቸው ስንት እርሳሶች ይደርሳቸዋል?



2. አንድ የህብረት ስራ ማህበር 32 የወተት ላሞችን ለ6 የማህበሩ አባላት እኩል አከፋፈለ።
   ሀ. እያንዳንዱ የማህበር አባል ስንት ላሞች ይደርሱታል?
   ለ. ሳይከፋፈሉ የሚቀሩ ላሞች ስንት ናቸው?

**ማስታወሻ**

ቀሪ የሚያስከትሉ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በባለ 1 ሆሄ ቁጥር ሲካፈሉ ድርሻውንና ቀሪውን በቀላሉ ለማወቅ፡-

ተካፋዮን በአካፋዩ ብዜት እና ከአካፋዩ በሚያንስ ሙሉ ቁጥር ድምር መግለፅ፣ ከዚያም የማካፈሉን ስራ በመቀጠል ድርሻና ቀሪውን ማግኘት።

**ምሳሌ 5.11፡-** የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 27÷4 ለ. 32÷5

**መፍትሄ፡-**

ሀ. 27 ÷ 4 = (24+3) ÷4 → “27”ን በ4 ብዜትና ከ4 በሚያንስ ሙሉ ቁጥር ድምር መግለፅ።

= (24÷4) + (3÷4)

= 6+(3÷4) → “3” ከ4 ስለሚያንስ “3”ን ለ4 ማካፈል ተግባራዊ አይሆንም፣

= 6 ቀሪ 3

ስለዚህ 27 ÷ 4 = 6 ቀሪ 3

ለ. 32÷5 = (30+2) ÷5→ በምሳሌ "ሀ" አሰራር መሠረት ሲሰራ
= (30÷5)+(2÷5)
= 6+(2÷5)
= 6 ቀሪ 2 ስለዚህ 32 ÷ 5 = 6 ቀሪ 2

## መልመጃ ቸ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 12÷5 ለ. 16÷3 ሐ. 17÷2 መ.19÷4

ሠ. 22÷6 ረ. 29÷7 ሰ. 45÷8 ሸ. 58÷9

2. አንድ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ለ7 ሲካፈል ድርሻው 8 ቀሪው ደግሞ 3 ቢሆን ቁጥሩ ስንት ነው?

## ባለ 3 እና ባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች ማካፈል

ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማካፈል ተምራችኋል፡፡ በማካፈል የሚገኘን ውጤት በማባዛት ማረጋገጥ ትችላላችሁ፡፡ አሁን ደግሞ ሌላ የማካፈል አሰራር ትማራላችሁ፡፡

**ምሳሌ 5.12** የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 246÷2 ለ. 563÷5

**መፍትሄ፡-**

ሀ. 246÷2 →የሚለውን አፃፃፍ 2⟌246 አድርጎ መፃፍ ይቻላል፡፡
የማካፈል ስራ የሚጀምረው ከተካፋዩ ቁጥር በስተግራ ካለው ሆሄ ነው፡፡

```
   123
2⟌ 246   - 2 ለ2 ሲካፈል ድርሻው 1 ነው፡፡ "1"ን ከምልክቱ ላይኛው ቦታ መፃፍ፡፡
  -2     - "1"ን በ2 አባዝቶ ከ2 ግርጌ መፃፍና መቀነስ፡፡ 2-2=0
    4    - ከቀነስን በኋላ "4"ን በቤቱ ከመስመሩ በታች መፃፍ
   -4    - "4"ን ለ2 ማካፈልና ድርሻውን ከውጤት መፃፊያው ከ "1" በስተቀኝ መፃፍ
     6   - "2"ን በ2 አባዝቶ ከ4 ላይ መቀነስ 4-(2x2)=0 = 4-4 =0
    -6   - ከተካፋዩ ያለውን "6"ን ከመስመሩ በታች በቤቱ አውርዶ መፃፍ፡፡
     0   - "6"ን ለ2 ማካፈልና ድርሻውን ከውጤት መፃፊያ ቦታ ላይ ከ "12" በስተቀኝ
           መፃፍ፡፡ 6÷2=3
         - "3"ን በ2 አባዝቶ ከ6 ላይ መቀነስ 6-6=0
```

ስለዚህ 246÷2=123

ለ. 563÷5

```
   112
5 |563   አሰራሩ እንደ ምሳሌ 5.12 “ሀ” ነው፡፡
  -5
   6
  -5
   13
  -10
    3   በመጨረሻ ተቀንሱ የተገኘው ውጤት “3” ከ5 ስለሚያንስ “3” ቀሪ ይሆናል፡፡
```

ስለዚህ 563 ÷ 5 =112 ቀሪ 3

## መልመጃ ነ

**የሚከተሉትን አስሉ፡፡ መልሳችሁንም አረጋግጡ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. 695 ÷ 2 | መ. 364 ÷ 5 | ሰ. 672 ÷ 8 |
| ለ. 343 ÷ 3 | ሠ. 585 ÷ 6 | ሸ. 815 ÷ 9 |
| ሐ. 252 ÷ 4 | ረ. 667 ÷ 7 | ቀ. 3232 ÷ 3 |

## እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማካፈል የያዙ የቃላት ኘሮብሌሞችን መፍታት

እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥር ማካፈል ተምራችኋል፡፡ በተማራችሁት የማካፈል አሰራር ሊፈቱ የሚችሉ የቃላት ፕሮብሌሞችን አሁን ትማራላችሁ፡፡

**ምሳሌ 5.13 ፡-** ለሚከተሉት የቃላት ኘሮብሌሞች መፍትሄ ፈልጉ፡-

1. 30 ብርቱካኖችን 6 ልጆች እኩል ቢካፈሉ፤ እያንዳንዳቸው ስንት ብርቱካኖች ይደርሳቸዋል?
2. 5 ሰራተኞች በጋራ የቀን ስራ ሰርተው ያገኙትን 565 ብር እኩል ቢካፈሉ፤ ስንት ስንት ብር ይደርሳቸዋል?

**መፍትሔ፡-**

1. 30 ÷ 6 = 5 ስለዚህ እያንዳንዳቸው 5 ብርቱካኖች ይደርሳቸዋል፡፡
2. 565 ÷ 5 =113

## መልመጃ ኘ

**ከዚህ በታች ለቀረቡት የቃላት ኘሮብሌሞች መፍትሔ ፈልጉ፡፡**

1. 63 ከረሜላዎች ለ7 ልጆች እኩል ቢከፋፈል ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?
2. አንድ ነጋዴ 567 ደብተሮችን በ5 ካርቶኖች ውስጥ እኩል ከፋፍሎ ማሸግ ፈልጓል፡፡

   ሀ. በእያንዳንዱ ካርቶን ውስጥ ስንት ደብተሮች ታሽገዋል?

   ለ. ያልታሸጉ (የተረፉ) ደብተሮች ስንት ናቸው?
3. የአንድ ሳሙና ዋጋ 5 ብር ነው፡፡ በ315 ብር ስንት ሳሙናዎች መግዛት ይቻላል?
4. በአንድ ፓኬት ውስጥ 6 ሻማዎችን ብቻ ማሸግ ይቻላል፡፡ 726 ሻማዎችን በስንት የሻማ ፓኬቶች ውስጥ ማሸግ ይቻላል?
5. በአንድ የችግኝ መደብ 8 ችግኞችን ብቻ መትከል ይቻላል፡፡ 776 ችግኞችን ለመትከል ስንት የችግኝ መደቦች ያስፈልጋሉ?

## የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ

- ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በ “0” ሲባዛ ውጤቱ “0” ነው፡፡ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በ “1” ሲባዛ ውጤቱ ራሱ ቁጥሩ ይሆናል፡፡
- ባለ ሁለት ወይም ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር በአለኝታና ያለአለኝታ ሲባዙ፡-
  - ✓ ከአንድ ቤት ሆሄው በመጀመር በቤት በቤታቸው ማባዛት
  - ✓ የተገኘውን ውጤት በቤት በቤት አድርጎ መፃፍ፡፡ አለኝታ ያለው ከሆነ “አለኝ” የሚባለውን ቁጥር ከሚቀጥለው የቁጥር ቤት ሆሄ ብዜት ጋር መደመር፡፡
- የ10 ወይም የ100 ብዜት ቁጥርን ለ10 ለማካፈል በአጭሩ በቁጥሩ የ1 ቤት የሚገኘውን “0” መተው ነው፡፡
- በማካፈል የሚገኝን ውጤት በማባዛት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

   ሀ. የ100 ብዜት የሆነን ሙሉ ቁጥር በ "0" በማባዛት የሚገኘው ውጤት የ100 ብዜት ነው፡፡

   ለ. ትንሹን ባለ ሦስት ሆሄ የ100 ብዜት በ 9 በማባዛት የሚገኘው ውጤት ባለ አራት ሆሄ ነው፡፡

   ሐ. የ1000 ብዜቶች ሁሉ የ100 ብዜቶች ናቸው፡፡

   መ. ትንሹ ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ 6 ሲባዛ ውጤቱ 600 ነው፡፡

   ሠ. ትልቁ ባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ 6 ሲባዛ ውጤቱ 4500 ነው፡፡

   ረ. አንድ ሙሉ ቁጥር ለ 5 ሲካፈል ድርሻው 35 ሆኖ ቀሪው 3 ከሆነ፤ ቁጥሩ 175 ነው፡፡

   ሰ. ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር "ሀ"፣ ሀ÷1=ሀ

   ሸ. 35 ለ10 ያለ ቀሪ ይካፈላል፡፡

2. የሚከተሉትን አባዙ፡፡

   ሀ. 900 × 9    መ. 85 × 6    ለ. 9000 × 1

   ሠ. 844 × 2    ሐ. 91 × 7    ረ. 543 × 7

3. የሚከተሉትን አካፍሉ፡፡

   ሀ. 200 ÷ 10    ሐ. 880 ÷ 10    ሠ. 170 ÷ 6

   ለ. 700 ÷ 10    መ. 500 ÷ 5    ረ. 85 ÷ 5

4. አንድ አርሶ አደር 7 ኩንታል ኑግ ገበያ አውጥቶ ሸጠ፡፡ የአንዱ ኩንታል ዋጋ 600 ብር ቢሆን፤ በጠቅላላው ኑጉን ሸጦ ያገኘው ብር ስንት ነው?

5. በአንድ ማሸጊያ ካርቶን ውስጥ 4 መፅሐፍቶችን ብቻ ማሸግ ይቻላል፡፡ 343 መጽሐፎችን ለማሸግ

   ሀ. ስንት ካርቶኖች ያስፈልጋሉ?    ለ. ስንት መጽሐፎች ሳይታሸጉ ይቀራሉ?

6. በኢትዮጵያ የቀናት አቆጣጠር አንድ ወር 30 ቀናች አሉት፡፡ አንድ ዓመት 12 ወሮች አሉት፡፡ ስለዚህ በ4 ዓመት ውስጥ ስንት ቀናች ይኖራሉ?

7. በአንድ ሆቴል ውስጥ የሚሠራ አንድ አሥተናጋጅ በቀን 10 ብር ጉርሻ ያገኛል፡፡ ሁለት ወር ቢሠራ በጠቅላላው ስንት ብር ያገኛል?

8. አንድ ጫማ ፋብሪካ በቀን 340 ጥንድ ጫማዎችን ያመርታል፡፡ ይህ ፋብሪካ በሶስት ወር ውስጥ ስንት ጥንድ ጫማዎችን ያመርታል፡፡

9. የሚከተሉትን የአብዥ ሰንጠረዦች አሟሉ፡፡

ሀ)

| × | 8 | 7 | 9 | 6 |
|---|---|---|---|---|
| 8200 | | | | |
| 3498 | | | | |
| 9987 | | | | |

ለ)

| × | 9 |
|---|---|
| 1000 | |
| 2000 | |
| 3000 | |
| 4000 | |
| 5000 | |
| 6000 | |
| 7000 | |
| 8000 | |
| 9000 | |

# ምዕራፍ ስድስት

# መስመሮችና ቀላል ምስሎች

**የመማር ማስተማር ውጤቶች፡-**

- ተቋራጭ መስመሮችን፣ ትይዩ ቀጥታ መስመሮችን እና ቀጤነክ መስመሮችን መለየት፣ ማስላት፡፡
- ሬክታንግል፣ ካሬ፣ ፓራሌሎግራምና ትራፒዚየም ምስሎችን መለየት፣ መሣል፡፡
- ክብን መሳል፡፡

## 6.1 ተቋራጭ፣ ትይዩና ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮች

በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርታችሁ ስለ ነጥብ፣ ስለ ነጥብ አሰያየም፣ ስለቀጥታ መስመር እና ስለቀጥታ መስመር አሰያየም ተምራችኋል፡፡አሁን ደግሞ ስለ ተቋራጭ፣ ትይዩ እና ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮችን ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 6.1

**በጋራ የሚሰሩ ጥያቄዎች**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥንድ ጥንድ መስመሮች ተመልክታችሁ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡




ሀ. ትይዩ ጥንድ ቀጥታ መስመሮች የትኞቹ ናቸው?

ለ. ተቋራጭ ጥንድ መስመሮች የትኞቹ ናቸው?

ሐ. ቀጤነክ ተቋራጭ ጥንድ መስመሮች የትኞቹ ናቸው?

## ትርጓሜ 6.1

1. ሁለት ቀጥታ መስመሮች የጋራ ነጥብ የሚኖራቸው ከሆነ **ተቋራጭ** መስመሮች ይባላሉ።
2. ሁለት የተለያዩ ቀጥታ መስመሮች ተቋራጭ ካልሆኑ **ትይዩ ቀጥታ** መስመሮች ይባላሉ።
3. ሁለት ተቋራጭ መስመሮች ሲቋረጡ እና አንዱ ለሌላው ቋሚ ከሆነ **ቀጤነክ** ተቋራጭ መስመሮች ይባላሉ።

## ምሳሌ 6.1

1. ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{ሀለ}}$ እና ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{መሠ}}$ ተቋራጭ መስመሮች ናቸው።




2. ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{ጠየ}}$ እና ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{ሸቀ}}$ ትይዩ መስመሮች ናቸው።




3. ቀጥታ መስመሮች $\overleftrightarrow{\text{ከአ}}$ እና $\overleftrightarrow{\text{ተቸ}}$ ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮች ናቸው።




## መልመጃ ሀ

1. የሚከተለውን ምስል ተመልከቱና የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልሱ።

   ሀ. ተቋራጭ ቀጥታ መስመሮች የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

   ለ. ትይዩ ቀጥታ መስመሮች የሆኑት የትኞቹ ናቸው?




2. ተቋራጭ ቀጥታ መስመሮችና ቀጤነክ ተቋራጭ ቀጥታ መስመሮች የሚመሳሰሉት በምንድን ነው?
3. የተቋራጭ ቀጥታ መስመሮችና የቀጤነክ ተቋራጭ ቀጥታ መስመሮች ልዩነት ምንድን ነው?

እስከ አሁን ስለትይዩና ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮች ተምራችኋል፡፡ ቀጥሎ የተማራችሁትን መሠረት በማድረግ በአካባቢያችሁ የሚገኙ ትይዩና ቀጤነክ መስመሮችን ትለያላችሁ፡፡

## ተግባር 6.2

**ጥንድ ጥንድ በመሆን ከመማሪያ ክፍል ውስጥና ውጪ ያሉ ነገሮችን ተመልከቱ፡፡ ከዚያም**

ሀ. ትይዩ መስመሮችን የሚያሳዩ የትኞቹ እንደሆኑ ተወያዩ፡፡

ለ. ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮችን የሚያሳዩ የትኞቹ እንደሆኑ ተወያዩ፡፡ በመጨረሻም ለክፍል መምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ከተመለከታችኋቸው ነገሮች መካከል፤

**ሀ. ትይዩ መስመሮችን ሊያሳዩ የሚችሉ፦ ለምሳሌ**

1. የወረቀት ሁለት የማይገናኙ ጠርዞች



ወረቀት

2. የጥቁር ሰሌዳ የላይኛውና የታችኛው ጠርዞች፡፡



ጥቁር ሰሌዳ

3. ሁለቱ ቋሚ የበር ጠርዞች እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ለ. ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮችን ሊያሳዩ የሚችሉ፡፡**

የመማሪያ ክፍሉ በር ቋሚና አግዳሚ ጠርዞች



የክፍል በር

## 6.2 ተቋራጭ፣ ትይዩና ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮችን መሳል

ቀደም ሲል ተቋራጭ፣ ትይዩና ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮች ምን አይነት መስመሮች እንደሆኑ ተመልክታችኋል፡፡ ቀጥሎ በቅርብ የምታገኟቸውን እቃዎች ተጠቅማችሁ መስመሮችን ትስላላችሁ፡፡

## ተግባር 6.3

**በግል የሚሰሩ**

የመጽሐፍ ጠርዝ ወይም ማስመሪያ በመጠቀም የሚከተሉትን ስሩ፡፡

1. ሁለት ተቋራጭ መስመሮችን በደብተራችሁ ላይ ሳሉ፡፡ የሚገናኙበትን ቦታና መስመሮችን በፊደል ሰይሟቸው፡፡
2. ሁለት ትይዩ መስመሮችን በደብተራችሁ ላይ ሳሉ፡፡
3. ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮችን በደብተራችሁ ላይ ሳሉ፡፡

## በተሰጠ ነጥብ ላይ የሚያልፍ ቀጤነክ መስመርን መሳል

### ቀጤነክ ቀጥታ መስመሮችን የመስራት ደረጃዎች

**ደረጃ 1፡-**




ቀጥታ መስመር "$\overleftrightarrow{ሀጠ}$"ን ሳሉ፡፡ በመስመሩ ላይ ነጥብ "ለ"ን አመልክቱ፣

**ደረጃ 2፡-** በቀጥታ መስመሩ ላይ የጎነ ሦስት መሳያውን አጭር ጠርዝ አስተካክሎ ማስቀመጥ




**ደረጃ 3፡-** የጎነ ሦስት መሳያው ሁለተኛው አጭር ጠርዝ ነጥብ "ለ" ን እስከሚነካ ድረስ መስመሩ ላይ ማንሸራተት፡፡




በጎነ ሦስት መሳያው አማካኝነት በነጥብ "ለ" ላይ የሚያልፍ ቀጥታ መስመር "$\overleftrightarrow{መሠ}$"ን መሳል፡፡

**ደረጃ 4፡-**




ቀጥታ መስመር "$\overleftrightarrow{መሠ}$" ለቀጥታ መስመር "$\overleftrightarrow{ሀጠ}$" ቀጤነክ መስመር ነው፡፡

## መልመጃ ለ

1. ቀጥታ መስመር ሀለን ሳሉ፡፡ ከቀጥታ መስመሩ ወጪ ነጥብ “ወ”ን አመልክቱ፡፡ በነጥብ “ወ” የሚያልፍ ለቀጥታ መስመር ሀለ ቀጤነክ የሆነ መስመር ስሩ፡፡

## በሁለት ትይዩ መስመሮች መካከል ያለው ርቀት ሁለቱ መስመሮች ላይ ያለ ቀጤ መስመር መሆኑን መግለፅ

ሁለት ቀጥታ መስመሮች ትይዩ ቀጥታ መስመሮች የሚባሉት ምንጊዜም የማይገናኙ ከሆነ ነው፡፡ በሁለቱ ትይዩ ቀጥታ መስመሮች መካከል ያለውን ርቀት ለማወቅ ከዚህ በታች የቀረበውን በቡድንና በተናጠል ደጋግማችሁ ስሩ፡፡

### ተግባር 6.4

**ከዚህ በታች በቀረበው ምስል ላይ ተመስርታችሁ ጥያቄዎችን ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ፡፡**




ቀጥታ መስመር ሀጠ እና ለአ ትይዩ ቀጥታ መስመሮች ናቸው፡፡

1. ከሁለቱ ትይዩ ቀጥታ መስመሮች ሀጠ እና ለአ ጋር ማዕዘናዊ አንግል የሚሰራ ቀጥታ መስመር መጨን ጎነ-ሦስት መሳያ በመጠቀም በደብተራችሁ ላይ ስሩ፡፡ ቀጥታ መስመር “መጨ” ሁለቱን ትይዩ መስመሮች የሚያቋርጥበትን ቦታ “ሰ” እና “ሸ” ብላችሁ ሰይሙ፡፡
2. ከሁለቱ ትይዩ ቀጥታ መስመሮች ሀጠ እና ለአ ጋር ማዕዘናዊ አንግል የሚሰራ ሌላ ቀጥታ መስመር ሠደን ጎነ ሦስት መሳያ በመጠቀም ስሩ፡፡ መገናኛ ቦታዎችንም “ቀ” እና “በ” ብላችሁ ሰይሙ፡፡
3. ማስመሪያ በመጠቀም የውስን ቀጥታ መስመር “ሰሸ”ን እና የውስን ቀጥታ መስመር “ቀበ”ን ርዝመት አወዳድሩ፡፡

   ስታወዳድሩ የሁለቱ ውስን ቀጥታ መስመሮች ርዝመት እኩል ከሆነ የሰራችሁት ትክክል ነው”

**ማስታወሻ፡-** ቀጥታ መስመር መጨ ከትይዩ መስመሮች ሀጠ እና ለአ ጋር ቀጤነክ ተቋራጭ ቀጥታ መስመር ነው፡፡ ተቋራጭ የሆኑባቸው ቦታዎች “ሰ” እና “ሸ” ላይ ነው፡፡ የውስን ቀጥታ መስመር “ሰሸ” ርዝመት በትይዩ ቀጥታ መስመሮች ሀጠ እና ለአ መካከል ያለው ርቀት ነው፡፡

## መልመጃ ሐ

### ሀ. ማስመሪያና ጎነ ሦስት መሳያ ተጠቅማችሁ

1. ሁለት ትይዩ ቀጥታ መስመሮች $\overleftrightarrow{ተቸ}$ እና $\overleftrightarrow{ጠደ}$ን በደብተራችሁ ላይ ስሩ፡፡
2. ለትይዩ መስመሮች $\overleftrightarrow{ተቸ}$ እና $\overleftrightarrow{ጠደ}$ ቀጤነክ ተቋራጭ ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{ጠየ}$ን ስሩ፡፡
3. በትይዩ ቀጥታ መስመሮች $\overleftrightarrow{ተቸ}$ እና $\overleftrightarrow{ጠደ}$ መካከል ያለውን ርቀት ለክታችሁ ውጤቱን ፃፉ፡፡

## 6.3 ሬክታንግል፣ ካሬ፣ ፓራሌሎግራምና ትራፒዚየም

በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርታችሁ ስለተወሰኑ ጎነ አራት ምስሎች የተማራችሁትን አስታውሱና ተግባር 6.5ን ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ፡፡

### ተግባር 6.5

በየቀኑ ከምትጠቀሙባቸውና ከምታዩዋቸው ነገሮች የካሬ፣ የሬክታንግል፣ የፓራሌሎግራም እና የትራፒዚየም ምሳሌዎችን ፃፉ፡፡ ምሳሌዎቹን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለጎነ አራቶቹ የሰጣችኋቸው ምሳሌዎች ቅርፃቸው የሚከተሉትን ይመስላል፡፡



ካሬ ሬክታንግል ፓራሌሎግራም ትራፒዚየም

በአካባቢያችሁ በየቀኑ የምትጠቀሙባቸውንና የምታዩዋቸውን ሬክታንግል፣ ካሬ እና ፓራሌሎግራም ምሳሌዎች ከዚህ በፊት ተመልክታችኋል፡፡ አሁን ደግሞ ስለ ባህሪያቸው ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 6.5

ጥንድ ጥንድ በመሆን ረዘም ያለ ገመድ አዘጋጁ፡፡ የገመዱን ሁለት ጫፎች አገናኝታችሁ እሰሩና በሁለት እጃችሁ ገመዱን በመያዝ፦

- የካሬ
- ሬክታንግል
- ፓራሌሎግራም
- ትራፒዚየም ምስሎችን ስሩ፡፡

**ማስታወሻ፡-**

1. ሁለቱ ጥንድ ተቃራኒ ጎኖቹ ትይዩ የሆኑ ጎነ አራት ምስል ፓራሌሎግራም ይባላል፡፡
2. ሁሉም የፓራሌሎግራም አንግሎች ማዕዘናዊ ከሆኑ የፓራሌሎግራም ምስሉ ሬክታንግል ይባላል፡፡
3. ሁሉም ጎኖቹ እኩል የሆኑ ጎነ አራት ካሬ ይባላል፡፡

## መልመጃ መ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. ሁሉም አንግሎቹ ማዕዘናዊ የሆኑና የሁሉም ጎኖች ርዝመት እኩል የሆነ ፓራሌሎግራም ____________ ይባላል።
2. ማንኛውም ሬክታንግል ________________ሊሆን ይችላል።
3. ማንኛውም ካሬ ________________ሊሆን ይችላል።

### ፓራሌሎግራምን መሳል

ስለፓራሌሎግራም ባህሪያት ከዚህ በፊት ተምራችኋል። ባህሪያቱን በመጠቀም የፓራሌሎግራምን ምስል አሳሳል ቀጥሎ ትመለከታላችሁ።

## ተግባር 6.7

**በግል የሚሰራ**

ነጠብጣቦችን በማገናኘት የፓራሌሎግራሙን ምስል በደብተራችሁ ላይ ሳሉ።



**ማስታወሻ፡-** ፓራሌሎግራም ምን አይነት ጎነ አራት ምስል እንደሆነ ታውቃላችሁ። የፓራሌሎግራም ምስል ከዚህ ቀጥሎ ባለው መንገድ ይሰራል።

- ሁለት ጥንድ ተቋራጭ ትይዩ ቀጥታ መስመሮችን መሳል።
- ሁለቱ ጥንድ ተቋራጭ ትይዩ ቀጥታ መስመሮች ፓራሌሎግራም ይመሰርታሉ።
- የፓራሌሎግራሙ መቋረጫ ነጥቦች (መለያያ ነጥቦች) ሀ፣ ለ፣ መ እና ሠ ናቸው።




- ውስን ቀጥታ መስመሮች ሀለ፣ ለመ፣ መሠ እና ሠሀ የፓራሌሎግራሙ ጎኖች ይባላሉ።
- የተቀባው (የጠቆረው) የፓራሌሎግራሙ ወለል ይባላል።




## መልመጃ ሠ

**ሀ. ማስመሪያ ተጠቅማችሁ በደብተራችሁ ላይ፡-**

1. ፓራሌሎግራም ስሩ።
2. የፓራሌሎግራሙን መለያያዎች ሰይሙ።

3. የፖራሌሎግራሙን ተቃራኒ ጎኖች ርዝመት በመለካት አወዳድሩ፡፡
4. የፖራሌሎግራሙን ወለል በመቀባት አመልክቱ፡፡

## ትራፒዚየምን መሳልና ባህሪያቱን መለየት

የሬክታንግል ምስል የሆነውን ትራፒዚየም መሳልና ባህሪያቱን መዘርዘር ከዚህ ቀጥሎ ትማራላችሁ፡፡

## ተግባር 6.8

**በግል የሚሰራ**

ነጠብጣቦችን በማገናኘት የትራፒዚየሙን ምስል በደብተራችሁ ላይ ሳሉ፡፡



ማስታወሻ፡- አንድ ጥንድ ተቃራኒ ጎኖቹ ብቻ ትይዩ የሆነ ጎነ አራት ምስል ትራፒዚየም ይባላል፡፡ የትራፒዚየም ምስል በሚከተለው አይነት መንገድ ይሳላል፡፡

- ሁለት ትይዩ ቀጥታ መስመሮች “ሰሸ” እና “ቀበ”ን መሳል፤
- ቀጥታ መስመሮች “ቀሰ” እና “በሸ”ን መስራት፡፡ እነኝህ ሁለት መስመሮች ከትይዩ መስመሮች ጋር ተቋራጭ ናቸው፡፡ የሚቋረጡባቸው ነጥቦች ሰ፣ሸ፣ ቀ እና በ ናቸው፡፡
- ውስን ቀጥታ መስመሮች ሰሸ፣ ሸበ፣ በቀ እና ቀሰ ጎኖቹ የሆነ ጎነ አራት ምስል ተመስርቷል፣ ምስሉም ትራፒዚየም ይባላል፡፡
- የተቀባው (የጠቆረው) ጎነ-አራት ምስል ሰሸበቀ የትራፒዚየሙ ወለል ይባላል፡፡







## መልመጃ ረ

1. የሬክታንግልና የካሬን ልዩነት ግለፁ፡፡
2. የፖራሌሎግራምንና የሬክታንግል ልዩነት አብራሩ፡፡
3. የፖራሌሎግራምና የትራፒዚየምን ልዩነት አብራሩ፡፡
4. ሁሉንም ጎነ-አራቶች (ሬክታንግል፣ ካሬ፣ ፓራሌሎግራምና ትራፒዚየም) ሊሆን የሚችለው ጎነ አራት ምስል ማነው?

## 6.4 ክብ

### የክብ እምብርት፣ ሬዲየስ፣ ዲያሜትርና አውታር

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ስለ ክብ እምብርት፣ ሬዲየስ፣ ዲያሜትርና አውታር ትርጉም ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 6.9

ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚሰራ፡-

1. የክብ ቅርፅ ያላቸው እቃዎችን በመጠቀም አንድ ክብ ሳሉ፡፡ የክቡን እምብርትም አመልክቱ፡፡
2. እስክርቢቶ፣ ክርና እርሳስ ተጠቅማችሁ አንድ ክብ ስሩ፡፡ ከዚያም የክቡን እምብርት በፊደል ሰይማችሁ አመልክቱ፡፡





እስክርቢቶ፣ ክርና እርሳስ ተጠቅማችሁ ክብ ስትሰሩ የተከተላችሁት መንገድ እንደሚከተለው ከሆነ ትክክል ነው፡-

- ክሩን እስክርቢቶውና እርሳሱ ጫፎች ላይ ማሰር፡-
- እርሳሱን ወረቀቱ መሀል ላይ ወግቶ መያዝ፡-
- እስክርቢቶውን ከተነሳችሁበት ቦታ እስከምትደርሱ ማዞር፡-

በዚህ መሠረት የተሰራው ምስል **ክብ** ይባላል፡፡ የእርሳሱ ጫፍ ያረፈበት ቦታ የክቡ **እምብርት** ነው፡፡

**ማስታወሻ፡-** የአንድ ክብ እምብርት “ወ” ቢሆን፤ ሀ፣ ለ፣ መ፣ ሠ እና ረ በክቡ ላይ ያሉ ነጥቦች ቢሆኑ፡-




- በክቡ ላይ ያሉ ማንኛውም ነጥቦች ከክቡ እምብርት “ወ” ያላቸው ርቀት እኩል ነው፡፡ ይህ ርቀት **ሬዲየስ** ይባላል፡፡

ስለዚህ ውስን ቀጥታ መስመሮች ወሀ፣ ወለ፡ ወመ፣ ወሠ እና ወረ የክቡ ሬዲየስ ናቸው፡፡

- በክቡ እምብርት ላይ የሚያልፍ እና ማንኛውንም ሁለት የክቡን ነጥቦች የሚያገናኝ ውስን ቀጥታ መስመር **ዲያሜትር** ይባላል፡፡ ስለዚህ ውስን ቀጥታ መስመሮች ሀሠ እና መረ የክቡ ዲያሜትሮች ናቸው፡፡
- የክቡን ማንኛውም ሁለት ነጥቦች የሚያገናኝ ውስን ቀጥታ መስመር **የክቡ አውታር** ይባላል፡፡ በመሆኑም ውስን ቀጥታ መስመሮች ሀሠ፣ መሠ እና መረ አውታሮች ናቸው፡፡

## መልመጃ ሰ

1. **የሚከተሉትን እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ፡፡**
   ሀ. አንድ ክብ አንድ እምብርት ብቻ ይኖረዋል፡፡
   ለ. አንድ ክብ ሦስት ሬዲየሶች ብቻ ይኖሩታል፡፡
   ሐ. አንድ ክብ ከአንድ በላይ ዲያሜትሮች ሊኖሩት ይችላል፡፡
   መ. አንድ ክብ ከአንድ በላይ አውታሮች ሊኖሩት ይችላል፡፡
   ሠ. ሁለት የተለያዩ ሬዲየሶች ያሏቸው ሁለት ክቦች አንድ አይነት እምብርት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

2. **ምስሉን በመመልከት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡**
   "ቀ" የክቡ እምብርት ነው፡፡
   ሀ. በክቡ ላይ የሚታዩትን ሁሉንም ሬዲየሶች ዘርዝሩ፡፡
   ለ. በክቡ ላይ የሚታዩትን ሁሉንም ዲያሜትሮች ዘርዝሩ፡፡
   ሐ. በክቡ ላይ የሚታዩትን ሁሉንም አውታሮች ዘርዝሩ፡፡




## የተለያዩ የክብ አውታሮችን ማወዳደር

አንድ ክብ ከአንድ በላይ አውታሮች ሊኖሩት እንደሚችል ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ በአንድ ክብ የተለያዩ አውታሮችን መጠን ማወዳደር ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 6.10

**ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚሰራ**

በምስሉ ላይ "አ" የክቡ እምብርት ነው፡፡




1. በማስመሪያ ሁሉንም አውታሮች ለኩና ውጤቱን መዝግቡ፡፡
   ትልቁ አውታር የትኛው ነው?
2. ዲያሜትሩንና ሬዲየሱን በማስመሪያ ለኩ፡፡ በዲያሜትሩ ርዝመትና በሬዲየሱ ርዝመት ምን አይነት ዝምድና አገኛችሁ?
3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከዚህ በታች የተሰጠውን የክብ ምስል በመመልከት መልሱ፡፡
   ወ የክቡ እምብርት ነው፡፡
   ሀ) ሶስት ሬዲየሶችን ስም ጥሩ፡፡
   ለ) ዲያሜትሩን ለዩ፡፡
   ሐ) የሬዲየሱንና የዲያሜትሩን ዝምድና አብራሩ፡፡
   መ) የክቡን ወለል በማጥቆር አሳዩ፡፡




### መልመጃ ሸ

1. የተሰጡትን ሬዲየሶች ተጠቅማችሁ ክቦችን በደብተራችሁ ላይ ሳሉ፡፡
   የክቦችን ትልቅ አውታር አመልክቱ፡፡
   ሀ. 3 ሴ.ሜ  ለ. 4 ሴ.ሜ  ሐ. 2 ሴ.ሜ
2. ከዚህ በታች ለተሰጡት የክብ ዲያሜትሮች፤ ሬዲየሳቸውን ፈልጉ፡፡
   ሀ. 6 ሴ.ሜ  ለ. 8 ሴ.ሜ  ሐ.10 ሴ.ሜ

# የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ

- ሁለት ቀጥታ መስመሮች የጋራ ነጥብ የሚኖራቸው ከሆነ ተቋራጭ መስመሮች ይባላሉ። ተቋራጭ ካልሆኑ ግን ትይዩ ቀጥታ መስመሮች ይባላሉ።
- ሁለት ተቋራጭ መስመሮች ሲቋረጡ አንዱ ለሌላው ቋሚ ከሆነ ቀጤነክ ተቋራጭ መስመሮች ይባላሉ።
- ሁለት ጥንድ ተቃራኒ ጎኖቹ ትይዩ የሆኑ ጎነ-አራት ምስል ፓራሌሎግራም ይባላል።
- የፓራሌሎግራም ሁሉም አንግሎቹ ማዕዘናዊ ከሆኑ ሬክታንግል ይባላል።
- ሁሉም ጎኖቹ እኩል የሆኑ ሬክታንግል ካሬ ይባላል።
- አንድ ጥንድ ተቃራኒ ጎኖቹ ትይዩ የሆነ ጎነ-አራት ምስል ትራፒዚየም ይባላል።
- አንድ ክብ አንድ እምብርት ብቻ ይኖረዋል።
- የአንድ ክብ ሬዲየስ የዲያሜትሩ ግማሽ ነው። ወይም ዲያሜትሩ የሬዲየሱ እጥፍ ነው።
- የአንድ ክብ ትልቁ አውታር የክቡ ዲያሜትር ነው።

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ።

   ሀ. ማንኛውም ሬክታንግል ፓራሌሎግራም ነው።

   ለ. ማንኛውም ፓራሌሎግራም ትራፒዚየም ይሆናል።

   ሐ. ማንኛውም ካሬ ሬክታንግል ይሆናል።

   መ. ማንኛውም ካሬ ትራፒዚየም ይሆናል።

   ሠ. አንድ ክብ ከአንድ በላይ እምብርት ሊኖረው ይችላል።

   ረ. የአንድ ክብ ሬዲየስ የዲያሜትሩ እጥፍ ነው።

   ሰ. የክቡን ማንኛውም ሁለት ነጥቦች የሚያገናኝ ውስን ቀጥታ መስመር የክቡ ሬዲየስ ይባላል።
2. ዲያሜትሩ 12 ሳ.ሜ የሆነ ክብ በደብተራችሁ ላይ ሳሉ።
3. የሬክታንግልና የትራፒዚየምን ልዩነት አብራሩ።
4. በጠለል ውስጥ ከአንድ ከተሰጠ ነጥብ በተወሰነ ርቀት ላይ የሚገኙ የነጥቦች ስብስብ ______ ተብሎ ይጠራል።
5. በክቡ እምብርት የሚያልፍ አውታር ______________ ይባላል።
6. የፓራሌሎግራምን ባህርያት ግለፁ።
7. የካሬን ባህርያት ግለፁ።
8. የትራፒዚየምን ባህርያት ግለፁ።
9. በራሳችሁ የአረዳድ ስልት የሚከተሉትን ቃላት ትርጓሜ ስጡ።

   - ሬዲየስ - ዲያሜትር - አውታር - ክብ

# ምዕራፍ ሰባት

# ገንዘብ

**የመማር ማስተማር ውጤቶች፡-**

- የኢትዮጵያን ሳንቲሞችና ብሮች መመንዘር፡፡
- የኢትዮጵያ ገንዘብን የሚመለከቱ የቃላት ኘሮብሌሞችን መፍታት፡፡

## 7.1 የገንዘብ ኖቶችን መዘርዘር (መቀየር)

ከቤተሰቦቻችሁ የተለያዩ የኢትዮጵያ የብር ኖቶች እና ሳንቲሞች ተመልክታችሁ ይሆናል፡፡ የተለያዩ ነገሮችን ለመግዛትም ሲጠቀሙባቸው ተመልክታችኋል፡፡ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ የብር ኖቶችን ከትልቁ ወደ ትንሹ መዘርዘር ትማራላችሁ፡፡

### ተግባር 7.1

**የቡድን ስራ**

1. የተለያዩ የኢትዮጵያን የብር ኖቶችና ሳንቲሞች ዘርዝሩ፡፡
2. የተለያዩ የብር ኖቶችንና ሳንቲሞችን ዝምድና ተወያይታችሁ ውጤቱን በፅሑፍ ግለፁ፡፡

**ከዚህ በታች የቀረቡት የኢትዮጵያ የብር ኖቶች እና ሳንቲሞች ምስሎች ናቸው፡፡**



ባለ 1 ብር ባለ 5 ብር ባለ 10 ብር ባለ 50 ብር ባለ 100 ብር

የኢትዮጵያ የብር ኖት ምስሎች



የኢትዮጵያ የሳንቲም ዲናሮች ምስሎች

**ማስታወሻ፡- በብር ኖቶችና ሳንቲም ዲናሮች መካከል ያለ ዝምድና፡-**

1 ባለ መቶ ብር = 2 ባለ ሃምሳ ብሮች
1 ባለ ሃምሳ ብር = 5 ባለ 10 ብሮች
1 ባለ አስር ብር = 2 ባለ 5 ብሮች
1 ባለ አምስት ብር = 5 ባለ 1 ብሮች
1 ብር = 2 ባለ 50 ሳንቲሞች
1 ባለ 50 ሳንቲም = 2 ባለ 25 ሳንቲሞች

በማስታወሻ ከተገለፀው ዝምድና ውጪ ከትልቁ የብር ኖት ወደ ትንሹ መቀየር ይቻላል፡፡ እንዲሁም ከትልቁ ሳንቲም ወደ ትንሹ መቀየር ይቻላል፡፡

**ምሳሌ 7.1፡-**

ሀ. 1 መቶ ብር = 10 ባለ 10 ብሮች

ለ. 1 ብር = 10 ባለ 10 ሳንቲሞች

## መልመጃ ሀ

1. ክፍት ቦታዎችን በትክክለኛው ዋጋ ሙሉ፡፡
   - ሀ. 1 መቶ ብር = _________ ባለ 5 ብር ኖቶች፡፡
   - ለ. 1 መቶ ብር = _________ ባለ 1 ብር ኖቶች፡፡
   - ሐ. 1 ሃምሳ ብር = _________ ባለ 5 ብር ኖቶች፡፡
   - መ. 1 አስር ብር = _________ ባለ 1 ብር ኖቶች፡፡
   - ሠ. 1 ባለ 50 ሳንቲም = _________ ባለ 10 ሳንቲሞች፡፡
2. ክፍት ቦታውን ሙሉ፡፡
   - ሀ. 1 መቶ ብር = 1 ባለ 50 ብር + _________ ባለ 10 ብር፡፡
   - ለ. 1 መቶ ብር = _________ ባለ 10 ብር + 10 ባለ 5 ብር፡፡
   - ሐ. 1 ሃምሳ ብር = 2 ባለ 10 ብር + _________ ባለ 1 ብር፡፡

## ከተሰጠ ገንዘብ ጋር እኩል የሆኑ ሳንቲሞችን ወይም ብሮችን መፈለግ

ስለተለያዩ የኢትዮጵያ የብር ኖቶችና ሳንቲም ዲናሮች ከዚህ በፊት በቀረበው ትምህርት ተረድታችኋል፤ ዝምድናቸውንም ተገንዝባችኋል፡፡ ይህን እውቀታችሁን በመጠቀም ከአንድ ከተሰጠ ገንዘብ ጋር እኩል የሆኑ ሳንቲሞችን ወይም ብሮችን መፈለግ ትማራላችሁ፡፡

**ተግባር 7.2**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተናጠል ስሩ፡፡**

1. 4 ብር ስንት ሳንቲሞች ይሆናል?
2. 3 ብር ስንት 50 ሳንቲሞች ይሆናል?

**ማስታወሻ፡- ከብር ወደ ሳንቲም ለመቀየር የተሰጠውን ብር በ100 ማባዛት ሲሆን፡**
**- ከሳንቲም ወደ ብር ለመቀየር የተሰጠውን ሳንቲም በ100 ማካፈል ይሆናል፡፡**

**ምሳሌ 7.2**

ሀ. 2 ብር= 2×100=200 ሳንቲም

ለ. 600 ሳንቲም= 600 ÷100=6 ብር

ሐ. 3 ብር ከ50 ሳንቲም= 3×100+50=350 ሳንቲም

### መልመጃ ለ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. በ350 ብር ውስጥ ስንት ባለ 50 ብር ኖቶች አሉ?
2. በ25 ብር ውስጥ ስንት ባለ 5 ብር ኖቶች አሉ?
3. በ1000 ብር ውስጥ ስንት ባለ 100 ብር ኖቶች አሉ?
4. በ5 ብር ውስጥ ስንት ባለ 25 ሳንቲሞች አሉ?
5. 8000 ሳንቲሞች ስንት ብር ይሆናሉ?
6. 35 ብር ስንት ሳንቲሞች ይሆናል?
7. 8 ብር ከ60 ሳንቲም= _______________ ሳንቲም፡፡
8. 690 ሳንቲም= _______________ ብር ከ90 ሳንቲም፡፡

## 7.2 የኢትዮጵያን የገንዘብ ምንዛሪ የያዙ የቃላት ኘሮብሌሞች

የብር ኖቶችንና ሳንቲሞችን ዝምድና በመጠቀም ከአንድ ከተሰጠ ገንዘብ ጋር እኩል የሆኑ ብሮችንና ሳንቲሞችን መፈለግ ቀደም ሲል ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ ከገንዘብ ጋር የተያያዙ የቃላት ኘሮብሌሞች መፍታት ትማራላችሁ፡፡

**ተግባር 7.3**

**በግል የሚሰራ**

ክፍል ውስጥ የተዘጋጀውን የሱቅ ህግ በመጠቀም እቃዎችን በየተራ ግዙ፡፡

1. የአንድ ሳሙና ዋጋ 4 ብር ቢሆን ለሦስት ሳሙናዎች ስንት ብር ትከፍላላችሁ?
2. ሦስት ሻማዎችን በ6 ብር ብትገዙ፤ የአንዱ ሻማ ዋጋ ስንት ነው?
3. የሦስት እቃዎችን ዋጋ ጠይቁ፡፡ የ1 ኪሎ ስኳር ዋጋ 18 ብር፣ የ1 ደብተር ዋጋ 5 ብር እና የ1 እስክርቢቶ ዋጋ 3 ብር ነው፡፡ 2 ኪሎ ስኳር፣ 3 ደብተርና 2 እስኪርቢቶ ለመግዛት ስንት ብር ያስፈልጋል?

የቃላት ኘሮብሌሞችን ለመፍታት ከዚህ በፊት እንደተማራችሁት ሁሉ መጀመሪያ ጥያቄዎችን ደጋግሞ በማንበብ መረዳት፡፡ ቀጥሎ ለጥያቄዎቹ መልስ መፈለግ እና መልሱን ማረጋገጥ ነው፡፡

**ምሳሌ 7.3** አሰገደች 150 ብር ይዛ ወደ ገበያ ወጣች። በ36 ብር 2 ኪሎ ስኳር፣ በ60 ብር ዘይት እና በ20 ብር ሳሙና ገዛች።

ሀ. በጠቅላላው ስንት ብር አወጣች? ለ. የተረፋት ብር ስንት ነው?

**መፍትሄ፡-** ሀ. ሦስቱን እቃዎች ለመግዛት ያወጣችው ብር

36 ብር + 60 ብር + 20 ብር = 116 ብር ነው።

ለ. የተረፋት ብር = 150 ብር − 116 ብር = 34 ብር

**ምሳሌ 7.4** ሀ. 53 ብር ወደ ሳንቲም ሲቀየር

53 ብር = 53 × 100 ሳንቲም = 5300 ሳንቲም

ለ. 7400 ሳንቲም ወደ ብር ሲቀየር

7400 ሳንቲም=7400÷100 ብር =74 ብር

## መልመጃ ሐ

**ለሚከተሉት የቃላት ፕሮብሌሞች መፍትሔ ፈልጉ።**

1. የ1 ደብተር ዋጋ 5 ብር ቢሆን የ12 ደብተሮች ዋጋ ስንት ብር ይሆናል?




ደብተሮች

2. ጥላሁን ዳቦ በ6 ብር፣ ሙዝ በ5 ብር ከ50 ሳንቲም እና ብስኩት በ1 ብር ከ50 ሳንቲም ገዛ። በጠቅላላው ስንት ብር አወጣ?

3. ብሩክ 350 ብር ይዞ ወደ ከተማ ሄደ። በ160 ብር ሱሪ እና በ170 ብር ሸሚዝ ገዛ።
   ሀ. በጠቅላላው ስንት ብር አወጣ?
   ለ. ስንት ብር ተረፈው?

## የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ

- ብርን ወደ ሳንቲም ለመቀየር የተሰጠውን የብር መጠን በ100 ማባዛት፡፡
- ሳንቲምን ወደ ብር ለመቀየር የተሰጠውን የሳንቲም መጠን በ100 ማካፈል

ከገንዘብ ምንዛሪ ጋር የተያያዙ የቃላት ፕሮብሌሞችን ለመፍታት የአሰራር ቅደም ተከተሎችን በትክክል በመፈፀም መስራት ያስፈልጋል፡፡ የአሰራር ቅደም ተከተሎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ፕሮብሌሙን ደጋግሞ አንብቦ መረዳት፡፡
- በፕሮብሌሙ የተሰጡትን ተጠቅሞ የተጠየቀውን አስልቶ ማግኘት፡፡
- የተገኘውን መልስ ማረጋገጥ፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ፡፡
   ሀ. በ6 ብር ውስጥ ______________ ባለ 50 ሳንቲሞች አሉ፡፡
   ለ. 6500 ሳንቲም ______________ ብር ይሆናል፡፡
   ሐ. 34 ብር ______________ ሳንቲም ይሆናል፡፡
   መ. 7 ብር ከ50 ሳንቲም __________ ሳንቲም ይሆናል፡፡
2. ወንድሙ የወር ደመወዙ 900 ብር ነው፡፡ ደመወዙን እንደተቀበለ 50 ብር ለእናቱ ሰጠ፤ ለወር የሚጠቀምበትን የምግብ ወጪ 450 ብር አወጣ፤ እንዲሁም 330 ብር የቤት ኪራይ ከፈለ፡፡
   ሀ. በጠቅላላው ከደመወዙ ስንት ብር አወጣ?
   ለ. ስንት ብር ተረፈው?
3. ከሁሉም የብር ኖቶች አንድ አንድ በተናጠል ወስደን ብንደምራቸው በጠቅላላው ስንት ብር ይሆናል?
4. ከሁሉም የሣንቲም ዓይነቶች አንድ አንድ ወስደን ብንደምራቸው በጠቀላላው ስንት ይሆናል?
5. ባለ መቶ ብር ስንት ባለ ሃምሳ ብር ኖቶች ይሆናል?
6. 1 ባለ 50 ሳንቲም ስንት ባለ ሃያ አምስት ይሆናል?
7. 1 ባለ መቶ ብር ስንት ባለ 10 ብር ኖቶች ይሆናል?
8. ባለ 1 ብር፣ ባለ 5 ብር፣ ባለ 10 ብር፣ ባለ 50 ብር፣ ባለ 100 ብር የብር ኖቶች በምን በምን ይለያያሉ፡፡ አብራሩ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

# ጊዜ

**የመማር ማስተማር ውጤቶች፡-**

- በሰዓትና በደቂቃዎች መካከል ያለውን ዝምድና መግለፅ::
- የእጅ ሠዓትና የግድግዳ ሰዓት በሰዓትም በደቂቃም ማንበብ::
- ቀኖችን፣ ሳምንቶችን፣ ወሮችንና አመቶችን ማግኘት::
- ቀላል የቀን መቁጠሪያ ማንበብ::

## 8.1 የሰዓት አነባበብ

ጊዜን ለመለካት የምንጠቀምበት መሳሪያ ሰዓት ነው። በአብዛኛው የጊዜ ልኬት በሰዓትና በደቂቃዎች ይገለፃል።

በስተቀኝ ያለው የሰዓት ምስል ነው። በምስሉ መሠረት የሚከተሉትን አስተውሉ።

- በምስሉ አጠርና ወፈር ያለው አመልካች **ሰዓት ቆጣሪ** ይባላል::
- ከሰዓት ቆጣሪው በመጠኑ ረዘም ያለው አመልካች **ደቂቃ ቆጣሪ** ይባላል::



የግድግዳ ሰዓት

**የሰዓት አቆጣጠር** አቅጣጫ ከ12 በመጀመር ወደ ቀኝ በመዞር ይሆናል።

- ደቂቃ ቆጣሪው ከ12 ተነስቶ ተመልሶ 12 ሲደርስ (አንድ ሙሉ ዙር) 1 ሰዓት ይባላል።
- ደቂቃ ቆጣሪው ከ 12 ተነስቶ 1 ላይ ሲያመለክት 5 ደቂቃ፣ 2 ላይ ሲያመለክት 10 ደቂቃ፣ 3 ላይ ሲያመለክት 15 ደቂቃ፣ 8 ላይ ሲያመለክት 40 ደቂቃ ይባላል።

**ምሳሌ 8.1፡-** የሚከተሉትን ተመልክታችሁ ሰዓቱን አንብቡ፡፡




ሀ ለ ሐ መ

**መፍትሔ**

ሀ. 4 ሰዓት ከ5 ደቂቃ ተብሎ ይነበብ፡፡ ይህም 4:05 ተደርጎ ይፃፋል፡፡
ለ. 10 ሰዓት ከ10 ደቂቃ ተብሎ ይነበብ፡፡ ይህም 10:10 ተደርጎ ይፃፋል፡፡
ሐ. 6 ሰዓት ከ35 ደቂቃ ተብሎ ይነበብ፡፡ ይህም 6:35 ተደርጎ ይፃፋል፡፡
መ. 4 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ተብሎ ይነበብ፡፡ ይህም 4:45 ተደርጎ ይፃፋል፡፡

## የቡድን ስራ

ካርቶኖችን፣ ማርከር፣ ምስማር እና ሽቦ ተጠቅማችሁ የሰዓት ሞዴል ሰርታችሁ የተለያዩ ሰዓቶችን በማመልከት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

## መልመጃ ሀ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስሩ፡፡**

1. ቀጥሎ ያሉትን ጊዜዎች የሚያሳዩ የሰአት ሞዴሎችን ሳሉ፡፡

   ሀ. 4:30 ለ. 5:40 ሐ. 10:10

2. ምስሎችን ተመልክታችሁ ሰዓቱ የሚያሳየውን ጊዜ በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡



ሀ ለ ሐ መ

## 8.2 ሰዓትና ደቂቃ

ቀደም ሲል የሰዓቶችን አቆጣጠርና ሰዓቶችን ማንበብ ተምራችኋል። አሁን ደግሞ ሰዓትና ደቂቃ ያላቸውን ዝምድና ትማራላችሁ።

### ተግባር 8.1

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስሩ።**

1. በ3 ሰዓት ውስጥ ስንት ደቂቃዎች አሉ?
2. 120 ደቂቃ ስንት ሰዓት ነው?

**ማስታወሻ፦**

1 ሰዓት = 60 ደቂቃ

ሀ. ሰዓትን ወደ ደቂቃ ለመቀየር የተሰጠውን ሰዓት በ60 ማባዛት ሲሆን፤

ለ. ደቂቃዎችን ወደ ሰዓት ለመቀየር በ60፣በ60 መድቦ ምድቦችን መቁጠር ይሆናል።

**ምሳሌ 8.2:-**

2 ሰዓት = 2 × 60 ደቂቃዎች = 120 ደቂቃዎች

3 ሰዓት = 3 x 60 ደቂቃዎች = 180 ደቂቃዎች

120 ደቂቃዎች = ሁለት 60 ደቂቃዎች = 2 ሰዓት

### መልመጃ ለ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በደብተራችሁ ገልብጡና መልሳቸውን ጻፉ።**

1. በ4 ሰዓት ውስጥ ስንት ደቂቃዎች አሉ?
2. 180 ደቂቃ ስንት ሰዓት ነው?
3. የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ።

| ሰዓት | ደቂቃ |
|---|---|
| 5 | |
| | 240 |
| 6 | |
| | 300 |

### አንድ አይነት ምድብ ያላቸውን የጊዜ ልኬቶች መደመርና መቀነስ

ሰዓትና ደቂቃ ያላቸውን ዝምድና ተምራችኋል። በመሆኑም ከሰዓት ወደ ደቂቃ እንዲሁም ከደቂቃ ወደ ሰዓት መቀየር ተረድታችኋል። አሁን ደግሞ አንድ አይነት ምድብ ያላቸውን ሰዓቶች መደመርና መቀነስ ትማራላችሁ።

## ሀ. አንድ አይነት ምድብ ያላቸውን የጊዜ ልኬቶች መደመር

### ተግባር 8.2

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. በ25 ደቂቃ ላይ 50 ደቂቃ ቢጨመር ስንት ሰዓት ይሆናል?
2. ከሟቱ በ2 ሰዓት ተኩል የተጀመረ የፅዳት ስራ ለ1 ሰዓት ተኩል ያህል ከተፀዳ በኋላ የፅዳት ሥራው ተጠናቋል፡፡ የፅዳት ሰራው ከሟቱ በስንት ሰዓት ተጠናቀቀ?

> **ማስታወሻ፡-** የደቂቃዎች ድምር 60 ሲሞላ ወደ ሰዓት በመቀየር ጊዜው ሊሰላ ይችላል፡፡

### ምሳሌ 8.3

1. በ55 ደቂቃ ላይ 35 ደቂቃ ቢጨመር ስንት ሰዓት ይሆናል?
2. 1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ ላይ 45 ደቂቃ ቢደመር ስንት ሰዓት ይሆናል?

### መፍትሔ፡-

1. 55 ደቂቃ + 35 ደቂቃ= 90 ደቂቃ
   = 60 ደቂቃ + 30 ደቂቃ
   = 1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ ወይም 1 ሰዓት ተኩል

2. 1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ + 45 ደቂቃ = 1 ሰዓት + 30 ደቂቃ + 30 ደቂቃ + 15 ደቂቃ
   = 1 ሰዓት + 60 ደቂቃ + 15 ደቂቃ
   = 2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ
   = 2 ሰዓት ከሩብ ወይም 2፡15

## መልመጃ ሐ

1. **የሚከተሉትን አስሉ፡፡**

   ሀ. 25 ደቂቃ + 30 ደቂቃ

   ለ. 35 ደቂቃ + 25 ደቂቃ

   ሐ. 45 ደቂቃ + 35 ደቂቃ

   መ. 31 ደቂቃ + 59 ደቂቃ

   ሠ. 85 ደቂቃ + 35 ደቂቃ

   ረ. 90 ደቂቃ + 30 ደቂቃ

2. አንድ Wራተኛ የውሀ ቦይ ለመቆፈር 4 ሰዓት ይፈጅበታል፡፡ ቁፋሮውን ጧት በ2 ሰዓት ቢጀምር ከቀኑ በስንት ሰዓት ይጨርሳል?

## ለ. አንድ አይነት ምድብ ያላቸውን የጊዜ ልኬቶች መቀነስ

### ተግባር 8.3

**በግል የሚሰራ**

1. ከ55 ደቂቃ ላይ 25 ደቂቃ ሲቀነስ ልዩነቱ ስንት ይሆናል?
2. አንድ መንገደኛ በመኪናና በእግሩ በአንድ ቀን 6 ሰዓት ተጉዟል፡፡ በመኪና የተጓዘው 4 ሰዓት ተኩል ነው፡፡ በእግሩ የተጓዘው ስንት ሰዓት ነው?

**ማስታወሻ፡-** በሰዓትና በደቂቃ ከተገለፀው ጊዜ ላይ የደቂቃው መጠን የሚበልጥ ጊዜ ሲቀነስ ከመጀመሪያው አንዱን ሰዓት ወደ 60 ደቂቃ መቀየርና መቀነስ፡፡

### ምሳሌ 8.3

ሀ. 1 ሰዓት ከ25 ደቂቃ - 55 ደቂቃ = 85 ደቂቃ - 55 ደቂቃ

= 30 ደቂቃ ወይም ግማሽ ሰዓት

ለ. $\begin{array}{r} 150\text{ ደቂቃ} \\ -\ 80\text{ ደቂቃ} \\ \hline 70\text{ ደቂቃ} \end{array}$ ወይም 1 ሰዓት ከ10 ደቂቃ

### መልመጃ መ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡
   - ሀ. 120 ደቂቃ - 35 ደቂቃ
   - ሐ. 120 ደቂቃ - 40 ደቂቃ
   - ለ. 180 ደቂቃ - 125 ደቂቃ
   - መ. 165 ደቂቃ - 50 ደቂቃ
2. የሚከተሉትን ጊዜዎች አስሉ፡፡ መልሳችሁን በደቂቃ ፃፉ፡፡
   - ሀ. 1 ሰዓት ከ10 ደቂቃ - 25 ደቂቃ
   - ሐ. 1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ - 55 ደቂቃ
   - ለ. 1 ሰዓት ከ45 ደቂቃ - 55 ደቂቃ
   - መ. 1 ሰዓት ከ35 ደቂቃ - 45 ደቂቃ

## 8.3 ቀን፣ ሳምንት፣ ወርና አመት

### ተግባር 8.4

የሚከተሉትን በጋራ ሥሩ፡፡

1. 1 ቀን ስንት ሰዓቶች አሉት?
2. 1 ሳምንት ስንት ቀኖች አሉት?
3. 1 ወር ስንት ቀኖች አሉት?
4. 1 ዓመት ስንት ወሮች አሉት?
5. 1 ዓመት ስንት ቀኖች አሉት?

**ምሳሌ፡- 8.4**

1. በሦስት ወሮች ውስጥ ስንት ቀኖች አሉ?
2. በአንድ አመት ተኩል ውስጥ ስንት ወሮች አሉ?

**መፍትሔ፡-**

1. በአንድ ወር ውስጥ 30 ቀኖች አሉ። ስለዚህ በሦስት ወሮች ውስጥ 3 × 30 = 90 ቀኖች ይኖራሉ።
2. አንድ አመት 12 ወሮች አሉት። ግማሽ አመት ደግሞ 6 ወሮች አሉት። ስለዚህ አንድ አመት ተኩል 18 ወሮች ይኖሩታል።

## መልመጃ ሠ

1. **የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ።**

ሀ. 4 አመት= _______ ወሮች

ለ. 9 አመት= _______ ወሮች

ሐ. 4 ወር= _______ ሳምንት

መ. 8 ወር= _______ ሳምንት

ሠ. 3 ሳምንት= _______ ቀን

ረ. 10 ሳምንት= _______ ቀን

2. **የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ።**

| አመት | ወር | ሳምንት | ቀን |
|---|---|---|---|
| 5 | | | |
| | 36 | | |
| | | 336 | |

3. አንድ ወጣት ሁለት ተከታታይ የመረብ ኳስ ዳኝነት ስልጠናዎችን ሰልጥኗል። የመጀመሪያውን ስልጠና በ3 ሳምንት፤ ሁለተኛውን ስልጠና ደግሞ በሁለት ወር አጠናቀቀ። ሁለቱን ስልጠናዎች ለማጠናቀቅ ስንት ሳምንት ፈጀበት?
4. ሀና አሁን 9 አመቷ ነው። ከሦስት አመት በፊት እድሜዋ ስንት ነበር?

## 8.4 ቀላል የቀን መቁጠሪያ

**ተግባር 8.5**

አንድ የቀን መቁጠሪያ ምን ምን ነገሮችን እንደሚይዝ (እንደሚያካትት) ከቤተሰቦቻችሁ ጠይቃችሁ በመምጣት መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

> **ማስታወሻ፡-** አንድ የቀን መቁጠሪያ የሚይዛቸው ዘመኑን፣ ወራቶችን፣ ሳምንቶችንና ቀኖችን ነው። እንዲሁም የተለያዩ የበዓላት ቀኖችን ያመለክታል።

**ምሳሌ 8.5፡-** የሚከተለውን ካላንደር በመመልከት ጥያቄዎችን መልሱ

| ጥር | | | | | | 2003 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| እ | ሰ | ማ | ረ | ሐ | አ | ቅ |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | | | | | |

| የካቲት | | | | | | 2003 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| እ | ሰ | ማ | ረ | ሐ | አ | ቅ |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 27 | 28 | 29 | 30 | | | |

1. ጥር 11 ቀን (ጥምቀት) ምን ቀን ነበር የዋለው?
2. የጥር ወር የመጨረሻው ቅዳሜ ቀኑ ስንት ነበር?
3. የየካቲት ወር 2ኛው ሀሙስ ቀኑ ስንት ነበር?

**መፍትሔ፡-**

1. የቀን መቁጠሪያውን በመመልከት ጥር 11 ቀን (ጥምቀት) ረቡዕ ቀን ነበር የዋለው፡፡
2. የጥር ወር የመጨረሻ ቅዳሜ ቀኑ 28 ነበር፡፡
3. የየካቲት ወር 2ኛው ሀሙስ ቀኑ 10 ነበር፡፡

ከዚህ በፊት በተማራችሁት መሠረት በአንድ አመት 12 ወሮች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ወር መስከረም፣ ሁለተኛው ወር ጥቅምት፣እያለ ይቀጥልና፣ የመጨረሻው ወር ነሐሴ ነው፡፡ የአመቱን ወራቶች ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ ቀኖችን አሳጥረን መፃፍ እንችላለን፡፡

**ምሳሌ 8.6**

1. ህዳር 20 ቀን 2003 ዓ.ም የሚለውን በአጭሩ 20/3/2003 ብለን መፃፍ እንችላለን፡፡ ከምልክት "/" በፊት ያለው "20" ቀኑን በሁለቱ ምልክቶች መካከል ያለው "3" ሦስተኛ ወር መሆኑን እና ከምልክቱ በስተቀኝ ያለው "2003" ዓመት ምህረቱን ይገልፃል፡፡
2. የካቲት 15 ቀን 2003 ዓ.ም የሚለውን በአጭሩ 15/6/2003 ተብሎ ይፃፋል፡፡

## መልመጃ ረ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ስሩ፡፡

1. ክፍላችሁ ውስጥ ያለውን የቀን መቁጠሪያ ተጠቅማችሁ፤ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ
   ሀ. በዚህ አመት ህዳር 12 ምን ቀን ይውላል?
   ለ. በዚህ አመት ሚያዚያ 27 ምን ቀን ይውላል?
   ሐ. በዚህ አመት ግንቦት 20 ምን ቀን ይውላል?
2. ሚያዚያ ስንተኛው ወር ነው?
3. የሚከተሉትን ቀኖች በአጭሩ ፃፉ፡፡
   ሀ. ሚያዚያ 27 ቀን 2005 ዓ.ም
   ለ. ሰኔ 30 ቀን 2005 ዓ.ም

# የምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያ

- ጊዜን ለመቁጠር የምንጠቀምበት መሳሪያ ሰዓት ይባላል
- በሰዓትና በደቂቃ መካከል ያለው ግንኙነት:- 1 ሰዓት = 60 ደቂቃ
- የተሰጠን ሰዓት ወደ ደቂቃ ለመቀየር በ60 ማባዛት፡፡ ደቂቃን ወደ ሰዓት ለመቀየር፣ የተሰጠውን ደቂያ በ60፣ በ60 እየመደቡ ስንት ሰዓት እንደሆነ ማግኘት ይቻላል፡፡
- አንድ አይነት ምድብ ያላቸውን ሰዓቶች መደመርና መቀነስ ይቻላል፡፡
- 1 ቀን = 24 ሰዓት      1 ወር = 4 ሳምንት<br>1 ሳምንት = 7 ቀኖች      1 አመት = 12 ወር
- አንድ የቀን መቁጠሪያ የሚይዛቸው:- ዘመኑን (ዓመተ ምህረቱን)፣ ወራቶችን፣ ሳምንቶችንና ቀኖችን ነው፡፡ በተጨማሪም ብሔራዊና ዓለም አቀፍ በአላትን ያመለክታል፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ሰዓቶች የሚያሳዩ የሰዓት ሞዴሎችን በደብተራችሁ ላይ ሳሉ፡፡

   ሀ. 2:30     ለ. 6:00     ሐ. 9:15
2. በ7 ሰዓት ውስጥ ስንት ደቂቃዎች አሉ?
3. 480 ደቂቃ ስንት ሰዓት ይሆናል?
4. ለአንድ ፈተና የተሰጠው ጊዜ 3 ሰዓት ነው፡፡ ፈተናው ከጠዋቱ በ2:30 ቢጀምር ፈተናው ስንት ሰዓት ላይ ይጠናቀቃል?
5. መስከረም 30 ቀን 2003 ዓ.ም የሀብታም ዕድሜ 9 ዓመት ከ7 ወር ነበር፡፡ ሀብታም 10ኛ ዓመት ልደቷን ያከበረችው መቸ ነበር?
6. የሚከተሉትን በሰዓት የጊዜ መስፈሪያ ምድብ ግለጹ፡፡

   ሀ) 1 ሳምንት     ሐ) 3.5 ቀናት<br>ለ) 2 ሳምንት     መ) 5.5 ቀናት
7. አሁን ጊዜው 6 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ቢሆን ከ80 ደቂቃ በኋላ ስንት ሰዓት ይሆናል?
8. የሚከተሉትን ወደ ደቂቃ ለውጡ፡፡

   ሀ) 4 ቀን     ሐ) 2 ሳምንት<br>ለ) 3:45 ሰዓት     መ) 20 ሰዓት
9. የሚከተሉትን ወደ ሰዓት ለውጡ፡፡

   ሀ) 8400 ሴኮንድ     ለ) 590 ደቂቃ     ሐ) 2 ቀን ከ5600 ሴኮንድ
10. የሚከተሉትን ድምሮች በትንሹ ምድብ አስሉ፡፡

    ሀ) 37 ደቂቃ + 40 ስዓት     ሐ) 45 ደቂቃ + 60 ደቂቃ<br>ለ) 45 ደቂቃ + 60 ስዓት     መ) 4 ስዓት – 30 ደቂቃ

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# መረጃ አያያዝ

**የመማር ማስተማር ውጤቶች:-**

- መረጃዎችን መሠረት አድርገው ቀላል ግራፎችን ማንበብ::
- ከግራፎች መረጃዎችን ማንበብ::

## 9.1 ቀላል የምስል ግራፎች

### መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀትና ቀላል ግራፍ መሳል

**ተግባር 9.1**

1. በቤተሰቦቻችሁ ውስጥ ስንት ወንድ ልጆችና ስንት ሴት ልጆች እንዳሉ መዝግባችሁ አምጡ።
2. በክፍል ውስጥ የሚገኙ ጓደኞቻችሁ የሚወዱትን የምግብ አይነት ጠይቁና መዝግቡ።


ሙዝ


ብርቱካን


ወተት


ሻይ

3. ጥንድ ጥንድ በመሆን ሳንቲም 20 ጊዜ ወርውሩና የሚወጣውን ምስል መዝግቡ።
4. ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 የሰበሰባችሁትን መረጃ የምስል ግራፍ ተጠቅማችሁ ሳሉ።



**ማስታወሻ**

**ቀላል የምስል ግራፍ ተጠቅሞ ድርጊቶችን (ክስተቶችን) ለማሳየት መጀመሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ እና ማደራጀት ያስፈልጋል።**

- **ምስላዊ ግራፍ እውነታዎችን (ድርጊቶችን) በቀላሉ እንድንረዳ ያደርጋል።**
- **በምስላዊ ግራፍ አንድ ምስል የተለያዩ መጠን ያላቸውን ነገሮች ሊወክል ይችላል። አንድ ምስል 2፣ 5፣ 10 ወይም ሌሎች መጠኖችን ሊወክል ይችላል።**

**ምሳሌ 9.1.** የክፍል ጓደኞቻችሁ የሚወዷቸውን የምግብ ዓይነቶች ጠይቃችሁ ስትመዘግቡ፣ የሚከተለውን ውጤት አግኝታችሁ ይሆናል።

- ሻይ የሚወዱ 6 ልጆች
- ወተት የሚወዱ 6 ልጆች
- ሙዝ የሚወዱ 8 ልጆች
- ብርቱካን የሚወዱ 10 ልጆች

ይህን መረጃ ቀላል ግራፍ በመጠቀም በሚከተለው መንገድ ሊገለፅ ይችላል።

**ማሳሰቢያ፡-** አንዱ ምስል ሁለት ልጆችን ይወክላል።

| የምግብ አይነት | ምግቡን የሚወዱ ልጆች |
|---|---|
| ሻይ |  |
| ወተት |  |
| ሙዝ |  |
| ብርቱካን |  |

## መልመጃ ሀ

1. ጥንድ ጥንድ በመሆን አንድ ባለ 10 ሳንቲም 50 ጊዜ በመወርወር የመዘገባችሁትን መረጃ ቀላል የምስል ግራፍ በመሳል አሳዩ።
2. አንድ የመጽሐፍ መደብር ሰኞ 10 መጽሐፎችን፣ ማክሰኞ 15 መጽሐፎችን፣ ሐሙስ 25 መጽሐፎችን እና አርብ 20 መጽሐፎችን ሸጧል። መረጃውን ተጠቅማችሁ ቀላል የምስል ግራፍ ሳሉ። (አንድ ምስል 5 መጽሐፎችን እንደሚወክል አድርጋችሁ ተጠቀሙ)።

3. በአንድ የፍራፍሬ መሸጫ መደብር ውስጥ 36 ብርቱካኖች፣ 42 ሙዞች፣ 48 ማንጐዎች እና 60 ሎሚዎች አሉ። መረጃዎችን ተጠቅማችሁ ቀላል የምስል ግራፍ ሳሉ። (1 ምስል 6 ፍራፍሬዎችን እንደሚወክል አድርጋችሁ ተጠቀሙ)።

## 9.2 ግራፎችን መተርጐም

መረጃዎችን በምስል ግራፍ መግለጽ ቀደም ሲል ተምራችኋል። አሁን ደግሞ መረጃዎችን ከምስል ግራፍ መተርጐም ትማራላችሁ።

### ተግባር 9.2

ከዚህ በታች ያለውን ምስላዊ ግራፍ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተመልከቱና ጥያቄዎችን መልሱ። ምስላዊ ግራፉ በአንድ ወረዳ በአራት አካባቢዎች የተደረገ የዛፍ ቆጠራን ያሳያል። አንዱ የዛፍ ምስል 100 ዛፎችን ይወክላል።




ሀ. በአካባቢ 1 ስንት ዛፎች አሉ?

ለ. ከሁሉም አካባቢዎች የሚበልጡ ዛፎችን የያዘው አካባቢ የትኛው ነው? ስንት ዛፎች አሉት?

ሐ. እኩል የዛፍ ብዛቶችን የያዙ አካባቢዎች የትኞቹ ናቸው?

መ. በአራቱም አካባቢዎች ያሉ ዛፎች በጠቅላላ ስንት ናቸው?

በምስላዊ ግራፍ አማካኝነት የተመሠረቱ ጥያቄዎችን ለመመለስ፡-

- መጀመሪያ ምስላዊ ግራፉ በምን ጉዳይ ላይ እንደተዘጋጀ ደጋግሞ በማንበብ መረዳት ያስፈልጋል።
- አንዱ ምስል የሚወክለውን መጠን ማወቅ
- በመጨረሻ ለጥያቄዎቹ መልስ መስጠት።

## መልመጃ ለ

1. በስተቀኝ በኩል ያለው ምስላዊ ግራፍ 10 ሳንቲምን ወደ ላይ 50 ጊዜ በመወርወር የተገኘ ውጤትን የሚያሳይ ነው፡፡ አንዱ ምስል 10 አጋዘኖችን ወይም 10 አንበሳዎችን ይወክላል፡፡
   ሀ. በውርወራው አጋዘን የተገኘው ምን ያህል ጊዜ ነው?
   ለ. አንበሳ የተገኘው ምን ያህል ጊዜ ነው?
   ሐ. በከፍተኛ መጠን የተገኘው ምስል የትኛው ነው? ብልጫው በስንት ነው?

| ምስል | በመወርወር የተገኘ ውጤት |
|---|---|
| አጋዘን |  |
| አንበሳ |  |

2. አንድ የህብረት ስራ ማህበር የገዛቸውን ማዳበሪያ በሦስት ቀን ውስጥ ለአባሎቹ አከፋፈለ፡፡ በሦስቱ ቀን የተደረገው ክፍፍል መጠን ከዚህ በታች ባለው ምስላዊ ግራፍ ቀርቧል፡፡ አንዱ ምስል 20 ኩንታል ይወክላል፡፡

| | |
|---|---|
| ሰኞ |  |
| ማክሰኞ |  |
| ረቡዕ |  |

   ሀ. ብዙ ኩንታል ማዳበሪያ የተከፋፈለው መቼ ነው? ስንት ኩንታል ተከፋፈለ?
   ለ. 80 ኩንታል ማዳበሪያ የተከፋፈለው መቼ ነው?
   ሐ. ሰኞ እለት ስንት ኩንታል ማዳበሪያ ተከፋፈለ?

# የምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ

- ምስላዊ ግራፍ ለመሳል መጀመሪያ መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡
- ምስላዊ ግራፍ ድርጊቶችን (እውነታዎችን) በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል፡፡
- በምስላዊ ግራፍ አንድ ምስል የተለያዩ መጠኖችን ሊወክል ይችላል፡፡
- ምስላዊ ግራፍን ለመተርጐምና የተለያዩ ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲቻል፡፡
  - ✓ መጀመሪያ ምስላዊ ግራፉ በምን ጉዳይ ላይ ተመስርቶ እንደተዘጋጀ ደጋግሞ በማንበብ መረዳት፡፡
  - ✓ አንዱ ምስል የሚወክለውን መጠን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. በክፍል ውስጥ የሚገኙ ጓደኞቻችሁ በጣም የሚወዷቸውን የምግብ ዓይነቶች ጠይቁና መዝግቡ፡፡ ከዚያም የምስል ግራፍ ሳሉና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

   ሀ. ብዙ ተማሪዎች የሚወዱት የምግብ ዓይነት የትኛው ነው? (ካለ)

   ለ. ትንሽ ተማሪዎች የሚወዱት የምግብ ዓይነት የትኛው ነው?

2. በአንድ ትምህርት ቤት ከሚገኙ ተማሪዎች ውስጥ የተለያዩ ጨዋታዎችን ማየት የሚወዱ እንዳሉ ተጠየቁ፡፡ እግር ኳስ ጨዋታን ማየት የሚወዱ 250፣ መረብ ኳስ ጨዋታን ማየት የሚወዱ 150 እና የጠረጴዛ ቴኒስ ጨዋታን ማየት የሚወዱ 100 ተማሪዎች ተገኙ፡፡

   1 ምስል 50 ተማሪዎችን እንደሚወክል አድርጋችሁ ቀላል የምስል ግራፍ ሳሉ፡፡



የእግር ኳስ



የጠረጴዛ ቴኒስ ኳስ



የመረብ ኳስ

3. በአንድ ት/ቤት በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ 40 ተማሪዎች የፍራፍሬ ምርጫ ተጠይቀው 10 ተማሪዎች ፓፓያ የሚወዱ ቢሆኑ፣ 12 ደግሞ ሙዝ፣ የተቀሩት ደግሞ ብርቱካን የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ይህንን ሁኔታ ቀላል የምስል ግራፉ በመሳል አሳዩ፡፡
4. ጤናን አስመልክቶ መረጃ ከየት ከየት እንደሚሰበሰብ አብራሩ፡፡
5. በትምህርት ቤታችሁ ከሚገኙት ተማሪዎች ከ1ኛ - 6ኛ ያሉትን የሴትና የወንድ ተማሪዎች ብዛት በቀላል ምስል ግራፍ በመሳል አሳዩ፡፡